እንደሚገባ መመላለስ

ለክርስትና ህይወት መመሪያ

Translated and printed by MERF-Ethiopia Ministry Team

2012/2020,Ethiopia

+251911790701

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈዉ አዲስ ክርስቲያን ለሆኑ ሰዎች ነዉ፤ ይህ ማለት ለታዳጊ ወጣቶች ማለት አይደለም፤ የስልሳ አመት ሰዉና የአስራ ስድስት አመት ሰዉ ተመሳሳይ በሆነ ችግር ዉስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ለታዳጊ ወጣቶቹ ልዩ የሆነ ተግባር የሚያስፈልጋቸዉ ይሆናል፤ ርዕሰ ጉዳዩ በተለይ አዳዲስ ክርስቲያኖች ወዲያዉ እንደተለወጡ የሚገጥማቸዉን ተግዳሮቶች እንዴት መፍታት እንዳለባቸዉ የሚናገር መጽሐፍ ነዉ፡፡ መጽሐፉ ሲነበብ ለሁሉም ነገሮች አንድ ችግር ሲወጣ ሌላዉ እንዴት እንደሚከተል የሚያሳይና አንዳንዱ ነጥቦች ደግሞ የአሳታሚዉ ፈቃድ እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

ልክ እንደሌሎቹ መጋቢዎች ሐላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለብኝ ሁሉ ታዳጊ ወጣቶች እንዴት መመላለስ እንዳለባቸዉና ችግር ሲገጥማቸዉ እንዴት ማለፍ እንዳለባቸዉ ማሳየት አለብኝ፤ አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ሲኖረኝ ለእያንዳንዱ ወጣት መስጠትን እመኝ ነበር፤ ይህ መጽሐፍ በአገልግሎቴ የሚያስፈልገኝን ነገር ረድቶኛል፤ በርግጥ ልዩ እና የተመረጠ ብቸኛ አይደለም፤ ብዙ መጋቢዎች በዚህ ዙሪያ ጽፈዉታል፤ ነገር ግን ለብዙ ክርስቲያኖች ጠቃሚ መጽሐፍ ነዉ ብዬ እመሰክራለሁ፤ ‹‹*በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ››* *(ቆላ 1፡10)*

‹‹ እንደሚገባ መመላለስ›› የሚለዉ ይህ መጽሐፍ የታተመዉ ከሰላሳ አመታት በፊት ሲሆን ለእኔ የሚያስደንቅ ነዉ፤ በተለይ የአገራችን የስነመግባር ሁኔታ የተለወጠበት ዘመን ነበር በርግጥ ክርስትናንም እንዲሁ ሳይነካ አላለፈም፤ የወንጌላዉያን ባህሪም እንዲሁ የተለወጠበት ጊዜ ነበር፤ ከሰላሳ አመታት በፊት ይህ መጽሐፍ ሲጻፍ የመጽሐፍ ቅዱስን የስነምግባር ሕጎችን ያሟላ ነበር፤ አሁንም ከሰላሳ አመታት በኋላ ይህ ‹‹እንደሚገባ መመላለስ›› የሚለዉ መጽሐፍ እንደገና ሲታተም ሕጎቹን አልለወጠም በዚህም በሃያ አንደኛዉ ዘመን ላለ ትዉልድ ከጸሎት ጋር ቢቀርብ ጠቃሚ ነዉ ብዬ አሳስባለሁ፡፡

(ጴጥሮስ ጆፍሪ)

(2011)

መቅድም

አራተኛ ዕትም

የአራተኛዉ ዕትም መቅድም

ይህ ‹‹እንደሚገባ መመላለስ›› የሚለዉ መጽሐፍ የመጀመሪያዉ እትም ከሰላሳ አመታት በፊት የታተመ ሲሆን ለብዙ ጊዜ በመደጋገም ታትሟል፡፡ አራተኛዉ ዕትም የታተመዉ ከክርስቲያን ፎከስ እትም ብሪንቲሪዮን ጋር በመተባበር ሲሆን ሶስተኛዉ እትም መጠነኛ የሆነ ማስተካከያ ተደርጎበታል፡፡ ብዙ ምዕራፎች ተጨምረዉበታል ከአዳዲስ ርዕሶች ጋር ለምሳሌ እንደ ዉርጃዎችና ዕፆች ያሉ ሲሆን ከሰላሳ አመታት በፊት ዉርጃና ዕፅ ለወጣቶች ዋና ርዕሰ ጉዳይ አልነበረም፤

ጴጥሮስ ጀፍሪ

ጥር 2011

እየሆነ ያለ ነገር

ሰዎች ካላቸዉ ነገር ሁሉ ክርስቲያን መሆን ትልቅ መታደል ነዉ። ወይም ደግሞ በሌላ አገላለጽ ሰዎች ካላቸዉ ልምምድና እዉቀት ሁሉ የሚበልጠዉ የሐጢአትን ይቅርታ ማግኘትና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን መሆን ነዉ። ይህንን ከምንም ነገር ጋር ማወዳደር አንችልም። ሐዋርዉ ጳዉሎስ ስለዚህ ልምምድ ሲናገር ፊሊ. 3፡7-8 መመልከት ትችላላችሁ። ከቁ.9-14 ያለዉን ክፍል አንብቡ መለወጥ የመጀመሪያ ጉዳይ ነዉ። እግዚአብሔር እርሱን በማወቅ እንድናድግ ይፈልጋል።

የሐጢአትን ይቅርታ ማግኘትና ድነትን መቀበል ትልቁ ስጦታ ነዉ። ይህ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠዉ ስጦታ ብቻ አይደለም (ሮሜ 8፡32)። ሁሉም ነገር የሚለዉ ቃል ከክርስቶስ ጋር ያለንን ልምምድ የሚያሳይ ነዉ።

ከክርስቶስ ጋር መጓዝ ማለት

በመንፈሳዊ ነገር እናድጋለን 1ጴጥ 2፡2፣ 2ጴጥ 3፡18

ሩጫዉን በትዕግስት እንሮጣለን ዕብ 12፡1

ዉጊያዉን እንዋጋለን 1ጢሞ 6፡12

እንደሚገባ መመላለስ

ማደግ፣መሮጥ፣ መዋጋት አዲስ ኪዳን እነዚህን ቃላት ከክርስቶስ ጋር ስንጓዝ ማድረግ ያለብንን ነገር የሚያሳዩንና በክርትናችንም ልቀን እንድንገኝና እንድንጠነክር የሚመክሩን ራሳችንንም እንድንገዛ የሚያደርጉን ናቸዉ:: ካልበላን አናድግም፣በትክክል ራሳችንን ካላሰለጠንን ሩጫዉን አናሸንፍም። የአዛዣችንን ትዕዛዝ ካልተቀበልንን ዉጊያዉን አናሸንፍም እንደገና (1ጢሞ 6፡12) ፤አንብብ። በዚህ ጊዜ ግን ከቁ.11 ጀምርና እስከ ቁ.14 ድረስ አንብብ::

ከክርስቶስ ጋር መሆን ማለት በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ብዙ ነገር ማድረግ ማለት አይደለም። ብዙ ክርስቲያኖች ‹‹ስራ›› በሚባል መንፈሳዊ በሽታ ተለክፈዉ እየተሰቃዩ ነዉ::

የዚህ መንፈሳዊ በሽታ ምልክቱ ለእግዚአብሔር አልችልም (ቢዚ) ነኝ የሚል ነዉ። ሳምንቱን በሙሉ ብዙ ስብሰባዎችን ስለተካፈለ መንፈሳዊ የሆነ ይመስለዋል። ይህን ግልጽ ለማድረግ እዉነተኛ ክርስቲያኖች ቤተክርስቲያን መሄድን ይወድዳሉ።እሁድ ቤተክርስቲያን መሄድና በሳምንት መካከለኛዉ ቀን ላይ ጸሎት ፕሮግራምን መሳተፍ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ ነዉ። እነዚህን ሁሉ ማድረግ በጣም አስፈላጊና ከክርስቶስ ጋር ለመሆናችን ምልክት ነዉ።

እርሱን ማወቅና መዉደድ

ከክርስቶስ ጋር መራመድ ማለት እግዚአብሔር ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ እግዚአበሔር ለእናንተ ያደረገዉን ነገር መገንዘብ እና መለማመድ ማለት ነዉ። ክርስቶስን በዉል ሳትረዳዉ ከእርሱ ጋር መራመድ አትችልም።

እግዚአብሔር ለአንተ ያደረገዉን በቅጡ ስትረዳ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ በጥልቀት በማወቅ ታድጋለህ። ይህ የእድገት ዉጤት የሚመጣዉ በትጋት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የሚመጣ ነዉ።ታማኝ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎቶች ስር ሆኖ መገልገል ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የሚጠቅም ነዉ። በእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ በተጋን መጠን እን ምርጫ፣ጽድቅ እና ስርየት የተባሉ አስተምህሮች ግራ የሚያጋቡ ስለሆኑ መንፈስ ቅዱስ በሂደት ለነፍስ ብርሃን የሚሰጥ ነዉ። እነዚህ አስተምህሮቶች ልባችሁን ካላነቃቁትና ደስ ካላሰኛችሁ በሚገባ አልተረዳችሁም ማለት ነዉ። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ዋና አላማዉ የሰዎችን ጭንቅላት በዕዉቀት መሙላት ብቻ ሳይሆን ልብን በፍቅርና በአምልኮ መሙላት ነዉ።ትክክለኛ መረዳት ወደ አምልኮ የሚመራ ነዉ።

እግዚአብሔር ለእናንተ ያደረገዉን ነገር ስትረዱና ስትለማመዱት በሕይወታቸሁ ሁሉ የእርሱን ፍቅር ታጣጥማላችሁ።እርሱን ባወቃችሁት መጠን ትወዱታላችሁ፣ታምኑታላችሁ፣ ከዚያም በሕይወታችሁ የእርሱን ሐይል ታያላችሁ።

ለመንፈሳዊ ሕይወት እድገት የሚጠቅሙ ንጥረ ነገሮች ማስተዋል፣ፍቅር፣መታመንና ልምምድ ናቸዉ።

ክርስቲያን የሚበረታዉም ሆነ የሚደክመዉ ከእግዚአብሔር ጋር ባለዉ ግንኙነትና እዉቀት መጠን የሚለካ ነዉ። በክርስትና ሕይወት ማደግ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የግል ግንኙነትና እዉቀትና ልምምድ ጋር እኩል ነዉ። እንዲህ አይነት ልምምዶች ወደ እግዚአብሔር ለማደግ

ብዙ ጊዜን የሚፈልግ ቅዱስ የሆነ ስራን የሚፈልግ ነዉ ለእግዚአብሔር ጊዜ ስንሰጥ እግዚአብሔር ደስ ይሰኛል:: *(ኤ ደብሊዉ ቶዘር)*

እንደ አዲስ ክርስቲያን ማመን አለብህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዉድ አድርጎ ይገልጥልሃል፤ ከዚህ በታች ያለዉ ታሪክ የ15አመት ልጅ በእንግሊዝ አገር ዉስጥ የሚያስደንቅ ስራ የሰራዉን ሰባኪና ብዙዎችን ወደ ጌታ ያመጣ ከዚህ በፊት ታይቶ ያልታወቀዉን ሰዉ ነዉ::

እንደ አዲስ ክርስቲያን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለኝ እኔም በተደጋጋሚ አነበዋለሁ:: እርሱም ‹‹መስዋእቱን በመሰዊያዉ ቀንድ ላይ አኑረዉ›› የሚለዉ ሲሆን ይህም የክርስቶስን ሁለንተና እንደሆነ ተረዳሁ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ በጋብቻ ቃል ኪዳን ጊዜ ባል ለሙሽሪት የጣት ቀለበት በሙሽሪት ጣት ላይ ሲያደርግ ‹‹ አንቺ የኔ ነሽ›› ማለቱ ሲሆን ጣቱን ሳየዉና ሳስታዉሰዉ ዘላለማዊ እና መጨረሻ የሌለዉን ክርስቶስ ከእኔ ጋር ያለዉን ቃል ኪዳን አሰብኩ፤ በጣም የምንደሰትበት፣የተባረከ፣ ቀን አለ፤ ደስ የሚል፣ የደስታ ቀን፣ አለ፤ የእርሱ ምርጫ አሁን ታዉቆኛል፤ ያ የተባረከዉ የነፍስ ዕረፍት፣ የክርስቶስን ርስት ለመዉረስ መመኘት ሳይሆን ትልቅ ፍላጎት ነዉ፤ ጥቂት ጥሩ የሆኑ ሰዎች እንደሚድኑ አምናለሁ ለዚህ ጣፋጭ የሆነ እረፍት ባይታደሉም ማለት ነዉ፤ እንደሚያስቡትም ሲያረጁ፣ሲሞቱ፣ ነገር ግን ሙሉ የእምነት ዋስትና እና በግል ክርስቶስን የማወቅ ሲሆን እንዲህ ይላሉ ‹‹ወዳጄ የኔ ናት›› የሚለዉ ንግግር አደገኛ ነዉ፤ ይላሉ፤ የክርስትና ሕይወት የጀመርኩት በ15 አመቴ ነበር::

ለምንድን ነዉ ቻርልስ ስፐርጀንን እግዚአብሔር ለአገልግሎት የተጠቀመበት? ይህ የሆነበት ምክንያት በግሉ እግዚአብሔርን ስለሚያዉቀዉና በብዙ ስለሚወደዉ ነዉ፤በክርስትና ህይወት ዉስጥ ይህ በምንም የማይተካ ነዉ፤ አዲስ ክርስቲያን ብትሆንም ይህ የስፐርጀን ንግግር የሚያበረታታ ነዉ:: ‹‹ሙሉ የእምነት ዋስትና አላችሁ ምክንያቱም ክርስቶስን በግል ስለምታዉቁት ነዉ›› ያለዚህ በክርስቶስ ለማደግ አይታሰብም፤ የቀረዉ የመጽሐፉ ክፍል ክርስቲያን ድነቱን እንዳይጠብቀዉና እንዳይለማመደዉ እንቅፋቶችን ያወሳል::

ጽድቅና ቅድስና

ከክርስቶስ ጋር ስንመላለስ ማስተዋል ያለብን ጉዳይ ጌታ ለአንተ ያደረገዉን ነገር በተለይም ከምንም ነገር በላይ ስለድነትህ አስብ፤ በሐጢአተህ ምክንያት ወደ ክርስቶስ መጣህ ይቅርታንም

አገኘህ፤ ሐጢአትህን ተናዘህ ክርስቶስን የግል አዳኝህ አድርገህ በተቀበልህ ጊዜ ከጌታ ጋር በመታረቅ የሀጢአትን ይቅርታ አገኘህ፤ በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን አገኘህ፤ በእምነት ከጸደቅህ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ሠላምን አግኝተሃል::

ይህ ታላቅ ክብርና ደስታ ነዉ፤ አሁን በክርስቶስ ጸድቀናል ከዚያም እግዚአበሔር በእኛ ሕይወት ዉስጥ የቅድስና ስራ እየሰራ ነዉ::

ጽድቅና ቅድስና የሚባሉት ሁለት ታላላቅ የስነመለኮት ቃላቶች ሲሆኑ እኛ ግን ክርስትናን ስንጀምር ጥቂቱን ነዉ የምናደርገዉ ብለህ ታስብ ይሆናል። ይህ ግን ትክክል አይደለም ማለት አይደለም፤ ካልጸደቅህ ክርስቲያን ነኝ ማለት አትችልም፤ ስትጸድቅ ግን የቅድስና ሂደት ትጀምራለህ::

ጽድቅ

ጽድቅ የእግዚአብሔር ልዑላዊ ስራ ነዉ። ሀጢአተኛዉን ሰዉ ነጻ ነህ ብሎ እግዚአብሔር የሚያዉጀዉ አዋጅ ነዉ፤ ሕጉ የሚፈልገዉን ነገር መመላት/ማርካት/ ማለት ነዉ::

እንደሚገባ መመላለስ

እነዚህን ትርጉሞች እንመልከት

- የእግዚአብሔር ልዑላዊ ስራ----ሁሉንም የሚያደርገዉ እግዚአብሔር ብቻ ሲሆን የሐጢአተኛዉ ሚና የለም (ሮሜ 3፡24፣ 4፡4-5)።
- አዉጇል-----ዳኛዉ ሕጋዊ የሆነ ፍርድ አስተላለፈ።
- ሐጢአተኛዉ----በተፈጥሮዉ በደለኛ (ኤፌ 2፡1-3) በስራዉም በደለኛ (ሮሜ 3፡10-23)።
- ጻዲቅ----ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል መንገዘ ነዉ (ሮሜ5፡1)።
- የሕጉ ፍላጎት-------የእግዚአብሔር ሕግ የሚፈልገዉ ሀጢአተኛዉ ዘላለማዊ ሞት እንዲሞት ነዉ (ሮሜ6፡23)።
- ረክቷል------በሕጋዊና በፍትሀዊ መሰረት የክርስቶስ የስርየት ሞት እግዚአብሔርን አስደስቶታል /አርክቶታል/ (ሮሜ 5፡18-21፣3፡26)።

በእምነት መጽደቅ ማለት ምን ማለት ነዉ? የዚህ አስተምህሮ እግዚአብሔር ወንድና ሴቶችን ከራሱ ጋር ያስታረቀበት እና የዳኑበት መንገድ ነዉ:: የእርሱ ስራ ነዉ፤ ይህ የሚያሳየን

እግዚአብሔር በልጁ በኩል ለእኛ የሰራውን ስራ የሚያሳይ ነዉ። የተባረከዉ ጌታችንና አዳኛችን በወንጌል ላመኑ ሁሉ በነጻ ይቅር አለን፣የሀጢአታችንን ይቅርታ አገኘን። በዚህ ብቻ አላቆመም ‹‹የክርስቶስ ኢየሱስን ጽድቅ ለበስን በእግዚአብሔር ፊት ነጻ እና ጻዲቅ መሆናችን ታወጀ፤ አሉታዊ ሳይሆን አዎንታዊ እይታ አለዉ፤ የክርስቶስን ጽድቅ ለብሰናል የራሳችን አዉልቀን ጥለን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን አገኘን፤ በሮሜ 5፡19 በዚህ ጻዲቅና ቅዱስ አምላክ ፊት ጻዲቅ ሕዝብ ተደርገን ተቆጠርን፤

ዲ.ኤም ሊዮድ ጆንስ

ጽድቅ ማለት በቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት ቅዱስ ሆኖ መቆም ማለት ነዉ፤ሀጢአተኛዉን ልዩ አያደርገዉም፤ ይህንን መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነዉ፤ እንደገና ዶ/ር ሊዮድ -ጆንስ የሚለንን እንስማ፡-

ጻድቃን ሆነን ተሰራን ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር እንደ ጻድቃን አደርጎ ቆጠረን ማለት ነዉ። ይህ ለብዙ ሰዎች መረዳቱ ከባድ ነዉ፤እነርሱ እንደሚሉት ሁልጊዜም ሀጢአታቸዉን ስለሚያስቡ ጻድቃን ነን ብለዉ ለመቀበል ይቸገራሉ፤እንዲህ ብሎ የሚያስቡ ሰዎች ስለ ጽድቅ ያላቸዉ አስተምህሮ አልገባቸዉም ማለት ነዉ። ጽድቅ በእኛ ዉስጥ የሚለወጥ አይደለም በእግዚአብሔር ብቻ በእኛ ላይ የሚታወጅ አዋጅ ነዉ:: እኛ ከምንሰራዉ ስራ የሚገኝ ዉጤት አይደለም ነገር ግን ለእኛ የተሰራ ስራ ነዉ። እኛ በእግዚአብሔር ፊት ስንታይ ጻድቃን ሆነን ተገኘን ይህም የእርሱ አዋጅ ነዉ።

አንድ ሰዉ እንደዚህ ብሎ ሊጠይቅ ይችላል፤ጽድቅ እኔን ጥሩ ሰዉ ካላደረገኝ ጥቅሙ ምንድን ነዉ? ጥቅሙ ይህ ነዉ ጸድቀሀል ማለት በእግዚአብሔር ፊት ልክ ነህ ማለት ነዉ፤ ወደ ሰማይ እንዲሁ ትገባለህ፤ በክርስቶስ ተቀባይነትን አግኝተሃል ማለት ነዉ (ኤፌ 1፡6)።

እግዚአብሔር በዚያ አላበቃም ለዉጥ የሚባለዉን ሂደት በአንተ ዉስጥ ጀመረ፣ለቅድስና ተጠርተሃል፣ ይህ ነዉ ልዩ ሰዉ ያደረገህ፤ ጽድቅ ከማንኛዉም በደልና ሀጢአት እንዲሁም ኩነኔ ነጻ መሆን ማለት ነዉ። ለአንዴና ለመጨረሻ በእግዚአብሔር የተነገረ ነዉ፤ በቅጽበት በጸደቅህ ጊዜ የቅድስና ሂደት በአንተ ዉስጥ ይጀምራል ከሀጢአት ሐይል ነጻ ያወጣል።

ቅድስና

ቅድስና የሚለዉ ቃል በብዙ የተለያዩ ምክንያቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ነገር ግን በአዲስ ኪዳን አማኞች በቅድሚያ ልባቸዉንና አእምሮአቸዉን የሚያነጹበት መንገድ ነዉ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ መቀደሳችሁ ነዉ (1ተሰሎንቄ 4፡3)

ይህ ማለት ቅድስና ነዉ (1ተሰሎንቄ 4፡7)

ይህ እግዚአብሔር በአንተ ዉስጥ ይሰራል (1ተሰሎንቄ 5፡23)

ቅድስና የመንፈስ ቅዱስ ቀጣይነት ያለዉ ስራ ሲሆን የጸደቀዉን አማኝ ከሀጢአት ነጻ የሚያወጣበትና በእግዚአብሔር አምሳል ያለዉን ሰዉን ማደስ ነዉ። መልካምን ስራ እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ፤(ኤል በርኮፍ) ፈጣን የሆነ ቅድስና የለም ቅድስናን ለማግኘት አቋራጭ መንገድ የለም። ‹‹ እንዲድ አምላክን እንፍቀድለት›› የሚሉት ቃላት ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረዉ አስተምህሮ ጋር ግን አብረዉ አይሄዱም።

ሰዉ ሳይሆን እግዚአብሔር የቅድስና ባለቤት ነዉ። ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንድናደርግና ከእለት ወደ ዕለት ቅድስናችንን እየጨመርን እንድንሄድ ተጠርተናል። ይህንን የምናደርገዉ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀዉን ነገር በመጠቀም ነዉ፤(2ቆሮንቶስ 7፡1፣ ቆላ 3፡5-14፣ 1ጴጥ 1፡22 አንብቡ)።

በምድራዊ ሕይወት ማንም ሰዉ ፍጹም ሊቀደስ አይችልም (1ነገ 8፡46፣1ዮሐ 1፡8) መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን በሰማይ አማኞች ከሐጢአት ሙሉ በሙሉ ነጻ እንደሚሆኑ ይነግረናል (ዕብ 12፡23፣ራዕ 14፡5) ቅድስናችን ፍጹም የሚሆነዉ ስንሞት ወይም ከሞት በኋላ ነዉ።

ስለዚህ ቅድስና ማለት በእኛ ዉስጥ ባለዉ ሐጢአት ላይ ድልን ማግኘት ማለት ነዉ። የሐጢአት ሐይል ተሰብሮአል ሮሜ 6፤ይህ ታላቅ ምዕራፍ ሲነገረን የሐጢአት ባሪያ እንደነበርን(ሲገዛን፣ሲቆጣጠረን የነበረ) እና አሁን ግን በክርስቶስ ስንሆን ተቀየረ፤ አሁን ለሐጢአት ሞተናል(ቁ.11)፤ በፊት እነደዛ አይነት ሰዉ ነበርኩ አሁን ግን አይደለሁም፤ በፊት ከሀጢአት በታች ነበርሁ አሁን ግን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነኝ፤ሀጢአት በእኔ ላይ ስልጣን የለዉም፤ በእኔ ላይ ሐይል የለዉም።

ይህ ማለት ግን ሀጢአት ክርስቲያንን አይነካውም ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ክርስቲያንን እንደ በፊቱ ስልጣን ኖሮት ሊገዛው አይችልም። አሁን ክርስቲያን በእርሱ ላይ ድልን ተቀዳጅቷል ፍጹም የሆነው ስልጣኑ አብቅቷል። የሐጢአት ባሪያ አይደለንም እርሱ ሊገዛን አይችልም ስለዚህም የሐጢአት ጠላቶች ነን፤ የክፉን ተጽእኖ እንዋጋለን እንቋቋመዋለን፣ አንታዘዘውም(ቁ.12)፤ የሐጢአትን ፍሬ አናፈራም(ቁ.13)።‹‹ እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና›› ሀጢአት ከእኛ በላይ ከነገሰ እንሞታለን ማለት ነው (ሮሜ 8፡13፣ቆላ 3፡5)።

ይህ ሁሉ ቀላል አይደለም ትጋትና ዉሳኔን ይጠይቃል። የሚቻለዉም ‹‹ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና›› (ሮሜ 6፡6)።

ክርስቲያን ብንሆንም እንኳ አሮጌዉ ተፈጥሮ በዉስጣችን ይኖራል።ይህ ደግሞ ሊያበሳጨን አይገባም፤ አሮጌዉን ሰዉ ልንዋጋዉና ልናስወግደዉ አዲሱን ሰዉ ደግሞ እንዲገዛን መፍቀድ ይኖርብናል፤(ኤፌ 4፡20-32)። ይህን ስናደርግ ሕይወታችን ያድጋል፣ይቀደሳል፣ ክርስቶስን ወደ መምሰል ያድጋል ምክንያቱም ቅድስና በሁለንተና ሕይወታችን ላይ ተጽዕኖን ይፈጥራል።

ማስተዋል	ኤርሚያስ 31፡33-34
ፈቃድ	ሕዝቅኤል 36፡25-27
ጥልቅ ፍቅር	ገላትያ 5፡24
ሕሊና	ዕብራዉያን 9፡14

እግዚአብሔር ሕዝቡ መልካምን ስራ ሲሰራ ይደሰታል። ይህ መልካም ሥራ ድነትን ለማስገኘት አይደለም (ኤፌ2፡8-9) ነገር ግን የድነት ዉጤት ለእግዚአብሔርን ክብርን ያመጣል (ማቴ5፡16)።

መልካም ስራ የእምነታችን ማረጋገጫ ነዉ። ያዕቆብ በመልዕክቱ አስረግጦ የተናገረዉ ነገር ነዉ፤ ያዕ 2፤ ለምሳሌ ቁ.17 ላይ እምነት እንዲህ ይላል ‹‹ ሥራ ከሌለህ ብቻህን ሙት ነህ›› በሚቀጥለዉ ጥቅስ ላይ ‹‹ እምነቴን በስራ አሳይሃለሁ›› እንደገና በቁ.20 ላይ ‹‹ እምነት ያለስራ ሙት ነዉ›› አንድ አማኝ እምነቱ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫዉ በስራ መገለጡ

ነው›› በማቴዎስ ሄነሪ የቆየዉ ማብራሪያ መጸሐፍ ላይ ‹‹ሐይማኖት በሕመም ሰዓት ካልደረሰልህ ለነፍስህም ሊደርስልህ አይችልም›› ይላል፤ በኤፌ 2፡10 ላይ ጳዉሎስ ሲናገር ‹‹እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።›› ኢ ኤፍ ሄቨን

ልዩነቶች

ጽድቅና ቅድስና የሚሉ ቃላትን ጠቅለል ስናደርጋቸዉ እንደሚከተለዉ ይቀርባሉ፤

- ጽድቅ የእግዚአብሔር ስራ ነዉ፤ የሰዉ ድርሻ የለበትም፤ ነገር ግን ቅድስና ማለት ግን የእግዚአብሔር ስራ ሆኖ የሰዉም ትብብር የሚፈልግ ነዉ።
- ጽድቅ ቅጽበታዊ ነዉ፤ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሆነ ክንዉን ነዉ፤ እንደማንኛዉም ክርስቲያን ጸድቀሃል፣ ቅድስና ግን ሂደት ነዉ በድነት ጊዜ ይጀምርና በቀረዉ ሕይወት ዘመን ሁሉ የሚከናወን ነዉ፤ ክርስቲያን በቅድስና ያድጋል እንደገና ሊደክምና ወደኋላ ሊል ይችላል፤ሁሉም ክርስቲያኖች በተለያየ የቅድስና ደረጃ ላይ ይገኛሉ።
- ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንድናገኝ የሚያደርግ ነዉ፣ ቅድስና ግን ክርስቶስን እየመሰልን እንድንሄድ የሚረዳን ነዉ። ከክርስቶስ ጋር ህብረት ማድረግ የቅድስና መሰረት ነዉ፤ምክንያቱም በክርስቶስ ስንሆን ክርስቶስን እንድንመስል የተጠራን ነን።

ድነት ማለት ልክ ባህርን ወጀብ ሲናዉጠዉ እንደሚናወጠዉ አይደለም፤ በድነት ስፍራ ላይ ነዉ ያለኸዉ ማለት መሰረትህ አለት ነዉ ማለት ነዉ። ወጀቡ አይጎዳህም አለቱ ክርስቶስ ስለሆነ በጥሩ ስፍራ አለህ።

ድነት ማለት መዳን ከሚባለዉ ቃላት በላይ ነዉ። አሁን በዳንከዉ ሕይወት መደሰት አለብህ። አንተ አለቱ ላይ ነህ ከፊትህ ልትወጣዉ የማትችለዉ ኮረብታ ሊኖር ይችላል። ከባህር በራስህ መዉጣት እንደማትችል ሁሉ በራስህ ኮረብታዉን ልትወጣዉ አትችልም። እንደገና አጽንኦት ሰጥቼ የምነግርህ ነገር ቢኖር በአለቱ ላይ በሰላም አለህ በሙሉ ኃይልህና ሕይወት ወደ ላይ መሄድ ትችላለህ፤ ጥያቄዉ ግን እንዴት ሊሆን ይችላል? ከዚህ በኋላ ከተራራ ጫፍ ላይ ገመድ ይወረወርልህ እና እንዲህ የሚል ትዕዛዛዊ ድምጽ ትሰማለህ‹‹ አንተ ዉጣ እኔ እጎትትሃለሁ›› የሚል ነዉ።

ይህ ቅድስና ነዉ፤ አንተ ወደ ላይ መዉጣት እየፈለግህ ብዙ መዉጣት የማትችላቸዉ እንቅፋቶች በመንገድህ ላይ ሲደቀን እግዚአብሔር ግን ያግዝሃል ወደ ከፍታ ያወጣሃል።

መታዘዝ

አንዳንድ ክርስቲያኖች የተሳሳተ ሐሳብ ያላቸዉ ሲሆን ይኸዉም ጌታን ስንቀበለዉ ጌታ አዳኛችን ሲሆን ከቆይታ በኋላ ጌታችን ይሆናል ብለዉ ያስተምራሉ። የዚህ አስተምህሮ ግን የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት የሌለዉ ነዉ።

ማንም ሰዉ ያለ ጌታ ርዳታ ወደ ክርስቶስ ሊመጣና ሊድን አይችልም። ከዚያ በኋላ ይታዘዘዋል፤የክርስቶስ አዳኝነት ዘላለማዊ ሲሆን ከጌትነቱ አይለይም፤መጽሐፍ ቅዱስን እንመልከት ‹‹*ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።መጽሐፉ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፤››(ሮሜ 10:9-13)* ጌታ የእምነታችንና የድነታችን ባለቤት ነዉ። (ኤ ደብሊዉ ቶዘር)

ኢየሱስ አዳኝህ ነዉ ማለት የሕይወትህ ጌታ ማለት ነዉ፤ የድነት ማረጋገጫዉ ወደ መድረክ መዉጣት፣እጅን ማንሳት፣ወይም ለማመን የወሰንክበትን የአድራሻ ካርድ ቃለመጠይቅ መሙላት አይደለም፤ማረጋገጫዉ አዲስ ፍጥረት መሆን ነዉ። ‹‹*ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል››* *(2ቆሮ5:17)*፤

ኢየሱስ ሲያድነን ራሳችንን ለርሱ እንድንሰጥና የሕይወታችን ንጉስ አድርገን እንድንኖር ይፈልጋል ለዚህም ጠርቶናል። ኢየሱስ ጌታና አዳኝ ነዉ፤አንዱ ያለ ሌለኛዉ ሙሉ አይሆንም፤ይህ እዉነት ነዉ ምክንያቱም ድነት ሀጢአትን ይቅር ከማለት ይበልጣል። ከሀጢአታችን ድነናል፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነናል፤ ከሰይጣን ሐይል ድነናል፤(ኤፌ2:2፣ ዮሐ 8:33-34፣44) ለክርስቶስ ጌትነት (ዮሐ 20:28፣1ቆሮ 1:9)።

ጌታ ከእኛ የሚጠብቀዉ ነገር ክርስቶስን የሕይወታችን ጌታ እንድናደርግና እንድንታዘዘዉ ነዉ። መታዘዝን ሊተካዉ የሚችል ነገር የለም (1ሳሙ 15:22)፤ አዳምና ሔዋን ካለመታዘዛቸዉ

የተነሳ የሐጢአት ተፈጥሮ በእኛ ውስጥ ችግር ሆነ (ዘፍ 2፡16-17) እና 3፡11። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር እናነባለን፤ በእነርሱ አለመታዘዝ ከፍተኛ የሆነ ችግር መጣ ‹‹በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ›› (ሮሜ5፡19)፤እግዚአብሔር ይመስገን፤ በዚህ ክፍል ደግሞ በአንዱ(ክርስቶስ) መታዘዝ ምክንያት በዙዎች ጻድቃን ሆኑ፤ በእግዚአብሔር ጸጋ ድናችኋል፤ አሁን እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገዉ እርሱን በመታዘዝ ጌትነቱንና ስልጣኑን እንድታዉቅ ነዉ።

በክርስቲያን ሕይወት መታዘዝ ቁልፍ ሀሳብ ነዉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ይህንን እናገኛለን። (ዘጸ19፡5) መታዘዝ ለበረከት አስፈላጊ ጉዳይ ነዉ፤ ጴጥሮስ በመጀመሪያዉ ምዕራፍ ላይ የሚያስታዉሰን የዳንነዉ ለመታዘዝ እነደሆነ ነዉ (1ጴጥ1፡2)፤ በቁ.14 እንደገና መልሶ ያነሳል በቁ 22፤ በመጀመሪያዉ የዮሐንስ መልዕክት ዉስጥ መታዘዝ የመዳናችን ፈተና እንደሆነ ይጠቅሳል፤(1ዮሐ 2፡3-4)።

የእዉነተኛ መታዘዝ ሚስጢሩ በግል ከጌታ ጋር ያለን ግንኙነት ነዉ፤ ከክርስቶስ ጋር ያለን ቅርበትና ሕልዉናዉ ከአመጽና ከሐጢአት ይጠብቀናል፤(ዮሐ15፡1-10) መታዘዝ ቀዝቃዛ መሆን አይደለም፣ በፍርሃት የሚደረግና ቴክኒካዊም አይደለም፤ ነገር ግን በልባችን ለጌታ መሰጠትና እርሱን መዉደዳችንን የምናሳይበት ምላሽ ነዉ፤(መዝ 40፡8፣ዮሐ4፡34)፤ከጌታ ጋር ህብረት ማድረግና ለጌታ መታዘዝ የማይለያዩ ጉዳዮች ናቸዉ። የተጠራነዉ በጣም ከባድና ጨካኝ ለሆነዉ ሕግ ለመታዘዝ አይደለም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ነዉ፤ ‹‹ነገር ግን፦ ቃሌን ስሙ...›› (ኤር 7፡23) ይላል።

በጣም የሚያስደስተዉ ነገር ትዕዘዜን ጠብቁ የሚለዉ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አልፎ አልፎ የተጻፈ ነዉ፤ ነገር ግን በብዛት የተጻፈዉ ‹‹ቃሌን ስሙ›› የሚል ወይም ‹‹ታዘዙኝ›› የሚል ነዉ። ይህ ክፍል የሚያስተምረን በክርስትና ዉስጥ መታዘዝ ማለት ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት ማለት ነዉ። ጌታን የምትወደዉ ከሆነ ትታዘዘዋለህ (1ዮሐ5፡3)፤ በክርስቶስ አዳኝነት ደስተኛ ከሆንክ ለጌትነቱ በፊቱ ተንበርክከህ እዉቅና በመስጠትህ ደስተኛ ነህ።

ፈተና

ጌታን ትታዘዘዋለህ?

ሌሎች ክርስቲያኖች?	ገላትያ 6፡10
መደበኛ አምልኮና ህብረት?	ዕብራዉያን 10፡25
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ?	2ጢሞ 2፡15
ጥምቀት ?	ሐዋ 2፡38
መጋቢዎችህንስ?	ዕብራዉያን 13፡17

ክርስቲያኖች እንዴት ነዉ መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባ መጽሐፍ ነዉ ብለዉ የሚቀበሉትና ነገር ግን ትዕዛዛቱን የማይታዘዙት? ይህ ማለት የቃሉን ሀልዎት ማጣት ማለት ነዉ። ትክለኛ እምነት መታዘዝ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ግንኙነትን ከእግዚአብሔር ጋር ያደርጋል። የጌታ ትዕዛዛቶች ከባድና የሚያሳዝኑም አይደሉም።

ክርስቶስ

ክርስቲያንና አጥቢያ ቤተክርስቲያን

ከጌታ ጋር መመላለስ ማለት ከክርስቶስ ሕዝቦች ጋር አብሮ ማምለክ ማለት ነዉ። ስለዚህም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ሕብረት በማድረግ መኖር ያስፈልጋል።

የቤተክርስቲያን አባልነት

አንዳንድ ቤተክርስቲያን ለቤተክርስቲያን አባልነት ብዙም አይጨነቁም።የሚከራከሩትም አንድ ጊዜ ጌታን አምኜ ዳግም ተወልጃለሁ የአለም አቀፍ ቤተክርስቲያን አባል ሆኜአለሁ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሌላ ቤተክርስቲያን አባልነት የሚናገረዉ ነገር የለም። ይላሉ ለዚህ መልሱ ምንድን ነዉ?

‹‹ቤተክርስቲያን›› የሚለዉ ቃል

አዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን የሚለዉን ቃል በሁለት መንገድ የሚመለከት ሲሆን የመጀመሪያ የተጠቀመዉ በኤፌሶን 5፡25 ‹‹ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደወደዳትና ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ›› ይህ ስለ አለም አቀፍዋ ቤተክርስቲያን የሚናገር ሲሆን ሁሉም የዳኑ ሰዎች በሁሉ

ስፍራ በአንድ ጊዜ ያሉትን ነዉ፤ ይህች ቤተክርስቲያን የዳኑትን ሁሉ የያዘች ናት፤ ሁለተኛዉ በ1ቆሮ 1፡2 ላይ የተጠቀሰዉ ሲሆን ስለ አጥቢያ ቤተክርስቲያንን የሚናገር ነዉ፡፡ በቆሮንቶስ ያለች ቤተክርስቲያን ለአምልኮና ህብረት የሚሰባሰቡ ሰዎችን የያዘች ናት፡፡ የቆሮንቶስ አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንጂ አለም አቀፋዊ አይደለችም፡፡

የአዲስ ኪዳን ልምምድ

በአዲስ ኪዳን ሁሉም አማኞች የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላት ናቸዉ፡፡ በርግጥ እያንዳንዱ ሰዉ ጌታን ሲያምን የአለም አቀፍ ቤተክርስቲያን አባል ይሆናል፡፡ የዳኑት አማኞች ደግሞ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላት መሆን አለባቸዉ፤ በሐዋ 2፡47 አንድ ሰዉ ሲያምን የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ሆኖ ይጨመራል፡፡ በዚህ ስፍራ ቤተክርስቲያን የሚለዉ የኢየሩሳሌምን ቤተክርስቲያን ነዉ የሚያሳየዉ፤‹‹ ጌታም የሚድኑትን ሰዎች ዕለት ተዕለት ይጨምር ነበር›› የሚድኑትም ሰዎች ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን ራሳቸዉን የማይሰጡ ከሆነ የሚከተሉት ነገሮች ትርጉም አልባ ይሆናል (ሐዋ 6፡3፣ ሐዋ 14፡23፣ ዕብ 10፡24-25፣13፡17)፡፡

ጥቂት ክርስቲያኖች እንዲህ ብለዉ ይመልሳሉ ‹‹ ይህን ሁሉ አምናለሁ ነገር ግን እንደ ቢራቢሮ ከአጥቢያ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በመዞር አላምንም፤ትክክለኛ አባል መሆን አልፈልግም በአባልነት መዝገብ ላይ ስሜ መመዝገቡና የአባልነት ትርጉሙም አይገባኝም፤በተጨማሪም እንዲህ ብለዉ ይጠይቃሉ‹‹ የአንድ አጥቢያ አባል መሆን ትርጉሙ ምንድን ነዉ? ይላሉ፤ ጥቂት የወንጌላዉያን ቤተክርስቲያን አባላት የአጥቢያ አባልነትን አይቀበሉም፤ አብዛኛዉ አማኝ ይህን ያደርጋሉ የቤተክርስቲያንን ሹመትና ተግሳጽ ለመቀበል እና ንጽሕናን ለመጠበቅ ጥሩ መንገድ ነዉ፡፡

ንጽሕና

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል መሆን የሚችሉት ዳግም የተወለዱ አማኞች ብቻ ናቸዉ፤ ለዚህም እዉቅና ሰጥተዉ ይኖራሉ፡፡ አባል ሆነዉ ሲቆዩ አባል መሆናቸዉን አያስቡም ምክንያቱም በአገልግሎቶቹ ሁሉ ዉስጥ ስለሚሳተፉ ነዉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስርአቱ ላይሳካ ይችላል ዳግም ያልተወለዱ አማኞች የቤተክርስቲያን አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በእዉነተኛ ወንጌል የተወለደች ቤተክርስቲያን ጥቂት ክፉ ነገሮችን ልታደርግ ትችላለች፡፡ ይህ ቤተክርስቲያንን

ንጽሕና ለመጠበቅ ብቸኛዉ መንገድ አይደለም። ብዙ ወንጌላዉያን ቤተክርስቲያን ግን ስራቸዉን በተሳካና በሚያረካ መንገድ ያከናዉናሉ።

ሹመት

መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ይላል ‹‹ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።›› 1ቆሮ 14፡40) እንዲህ አይነት ልምምድ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ያለ ሲሆን አባላት የሚፈጽሙት ነገር ነዉ። ጴጥሮስ ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ሲናገር ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን›› ሐዋ 6፡3። ዲያቆናት ሊሆኑ የሚችሉ ከእናንተ መካከል የሚለዉ ጥያቄ ሊካፈሉና ለማምለክ ከተሰበሰቡት መካከል ማለት ነዉ። በመደበኛነት የሚያመልኩ ናቸዉ ወይስ ሌሎችንም የሚጨምር ነዉ? በመደበኛነት የሚያመልኩ ዳግም የተወለዱ አማኞች ናቸዉ ብሎ መመለስ ቀላል ነዉ። ታዲያ ማን ነዉ ይህ ዳግም የተወለደ አማኝ ያኖዉ ደግሞ ዳግም ያልተወለደ ተፈጥሮአዊ ሰዉ ነዉ ብሎ የሚለይ ማነዉ?

የቤተክርስቲያን አባል መሆን ማለት በርግጥ የአንድን ሰዉ ድነት የሚያረጋግጥ አይደለም፤ አንድን ሰዉ በአባልነት ከመቀበላችን በፊት ስለድነታቸዉ በትክክል ማወቅና መመስከር ይኖርባቸዋል። የቤተክርስቲያን መሪዎችም ተገቢዉን ቃለ መጠይቅ ሊያደርጉና ይገባል፤ በዚያን ጊዜ ትክክለኛዉን መረጃና ዳግም መወለዳቸዉንና አለመወለዳቸዉን ማወቅ ይቻላል። በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ዉስጥ የመሪዎችና የዲያቆናት መኖር ለአባላቶቻቸዉ የሚያስፈልገዉን ነገር ማዘጋጀት ነዉ። አባላትን በትክክል ማወቅ ጥርጣሬንና ግራ መጋባትን ለማስወገድ ይረዳል። ይህም ለቤተክርስቲያን አመራር ጥሩ ሲሆን ማን አባል ለመሆንና አባል ላለመሆን እምቢ የሚሉትን ለመለየት ጠቃሚ ይሆናል። እምቢ የሚሉ ሰዎች የሚያሳዝኑ ሲሆኑ ለዚህም የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን ነዉ።

ተግሳጽ

አንድ ሰዉ የቤተክርስቲያን አባል ሲሆን ራሱን ከመጋቢዉ ስር በማድረግ ለእንክብካቤዉና ለተግሳጹ ራሱን አሳልፎ መስጠት ይገባል (ዕብ 13፡17)። በሌላ ቋንቋ መጋቢዎችና መሪዎች በቤተክርስቲያንም ሆነ በግል ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ራሳቸዉን አሳልፈዉ መስጠት

ይገባል፤ ሕብረትና እርስ በርስ ፍቅርን ማሳየትና መከባበር ብቻ ሳይሆን እንደ ቤተክርስቲያን አባላት አንዳቸዉ ለአንዳቸዉ ራሳቸዉን አሳልፎ መስጠት ይገባል።

አባልነት ሕይወትን ለአጥቢያ ቤተክርስቲን አሳልፎ መስጠት ማለት ነዉ። ጥቅሙና ሐላፊነት መዉሰድ ጠቃሚ ጉዳይ ነዉ፤

ጥቅም

በቤተክርስቲያን መጋቢ እንክብካቤ ስር ናችሁ፤ የሚቀጥለዉን ክፍል እንመልከት

አንድ ሰዉ በአባልነት ስንቀበለዉ እርሱ ብቻ ሳይሆን የአባልነት ፎርም ተዘጋጅቶ ቅጹን መመላት አለበት፤ ቤተክርስቲያንም ቃል ማስገባት አለባት። አንድን ሰዉ በአባልነት ስንቀበለዉ ለዚያ ሰዉ ፍቅርን መስጠት እና ማገልገል ያስፈልጋል። ‹‹*ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ (ሐዋ 2:44)* ይህ የአዲሱ አማኝ ሰዉ ሐላፊነት ብቻ ሳይሆን የቤተክርስቲያንም ሐላፊነት ነዉ። (ጂ ኤሪክ ላኔ)

በተለይም ለአዳዲስ አማኞች እነዚህ ሁለት ነገሮች ጠቃሚ ናቸዉ።

ሐላፊነቶች

መደበኛ የስም ቁጥጥር፣ ስጦታዎችህን፣ መንፈሳዊና ሞራላዊ አገልግሎትን እንዲሁ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የቤተክርስቲያን አባላት ሐላፊነታችንን መወጣት አለብን። በቤተክርስቲያን አገልግሎት የምትረካ ከሆነ ቤተክርስቲያኒቱን በጸሎትና በገንዘብ በቋሚነት የማገልገል ሐላፊነት አለብህ።አባላቱ የመጋቢዉን ኑሮና ቤተሰብ የመንከባከብ ሐላፊነት አለባቸዉ፤ ምዕመኑ ከሚያገኘዉ ደመወዝ ለመጋቢዉ ማሳነስ የለባቸዉም።

መጋቢያዊ እንክብካቤ

ቤተክርስቲያን በሰዎች የተመሰረተች ድርጅት ሳትሆን በእግዚአብሔር በራሱ የተፈጠረች ናት። በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድናድግ የእግዚአብሔር ሐሳብ ሲሆን ዋናዉ የቤተክርስቲያን ሥራ ሰዎች በሕይወታቸዉ እንዲያድጉ ማድረግ ነዉ። በኤፌ4:11 ላይ እንደሚነግረን እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ዉስጥ ሊያስተምሩ የሚችሉ ሰዎችን ሰጥቷል፤ በቁ 13-15 ላይ ያሉትን ስናነብ ከመንፈሳዊ ሕጻንነት ወደ ብስለት እንድናድግ የሚያደርግ መንፈሳዊ ስጦታዎች ናቸዉ።

የክርስቲያኖች ባህርይ በአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ዉስጥ የመሪነትን ስፍራ ይሰጣል፤ (1ተሰ5፡12-13፣1ጢሞ5፡17፣ዕብ 13፡7፣17) በዚህ ክፍል ስናነብ የመሪዎቹ ትክሻ ሰፊና ሐላፊነት የተሞላበት ነዉ ለሕዝቦቻቸዉ ብዙ መጸለይ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ተግሳጽ

በአንድ መጋቢ ስር ሆኖ ተግሳጹን መቀበል፣እግዚአብሔር የሰጠህን ሐላፊነትም መወጣት በጣም ትልቅ የሆነ እድል ነዉ፡፡ ትኩረት አድርጌ መናገር የምፈልገዉ ይህ እድለኝነት መሆኑን ነዉ፤ ለማድግና ለመብሰል ስትፈልግ በመጋቢ ስር ሆነህ ስትሳሳት ለመገሰጽም ለመመከርም ዝግጁ መሆንህ ትልቅ የሆነ ዕድል ነዉ፤

ዛሬ ብዙ ሰዎችና ማህበረሰብ ተግሳጽ የሚለዉ ቃል ቆሻሻ የሆነ ቃል ነዉ፡፡ እያንዳንዱ ሰዉ የሚያስደስተዉን ነገር መከተል ይፈልጋል፤ ይህ ደግሞ የአለማዉያን ባህርይ ነዉ፤ እናንተ ደግሞ ከአለም አይደላችሁም (ዮሐ 17፡14)፤ እናንተ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የሚያስከብር ወይም የሚያሳፍር ነገር ልታደርጉ ትችላላችሁ፤ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ስታደርግ ለቤተክርስቲያን ሰላም ሲባል ማቅናት ይገባል (ገላ6፡1) ይህም ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል (ሮሜ16፡17)፡፡

ተግሳጽን ለመቀበል ፈቃደኛ ነህ? መቼ ነዉ አስፈላጊ የሚሆነዉ?

‹‹ልባችሁን ለጌታ ተግሳጽ ክፈቱ የእርሱን ተግሳጽ ለመቀበል ዝግጁ መሆንና ሊቀድሰን ለሚችለዉ ራስን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ታላላቅ የተባሉ ሰዎች ጸጋዉን የቀመሱ ሲሆን ምናልባትም ታላቅ የሚለዉን ስም ያገኙት በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል›› (ኤ ደብሊዉ ቶዘር)

እረኛዉ ከባድ ነገር የሚገጥመዉ ወይም ተኩላ በበጎች ዙሪያ ሲያደባ ልምድ ያላቸዉ አገልጋዮች ቀድመዉ ችግር እንዳለ ያስገነዝባሉ፡፡ ስለዚህም ልምድ ያለዉ መጋቢ በሕዝቡ ፊት እየሄደ ለአባላቱ አደገኛ ነገር እንደመጣ የሚያስጠነቅቅ ነዉ ይህን በማድረጉ ይመሰገናል፡፡ በርግጥ ተራራ ጫፍ ላይ አረንጓዴና ልምላሜ ያለዉ ሣር ይበቅላል በዚህ ጊዜ በመታለል መዉደቅ ይኖራል፡፡ ነገር ግን እረኛዉ በጥበቡ ስራን መስራት አለበት፤ ለአንድ አባል ይህ ትልቅ ድነትና ሰላም ነዉ፤ እርሱም አለምን እንደተገዳደረ ሳይሆን ዳቢሎስን እንደተገዳደረ እንደሆነ ይገባዋል፡፡ ራሱን ማመን እንደሌለበት ይረዳል፣በእዉቀት እየተሞላ ሲሄድ እየጠነከረና

ወደ ብስለት እያደገ ይሄዳል። ስጦታውም ሊመራውና ሊጠብቀው ይችላል ፍላጎት ሲኖር ልምዱ ስላለው ይነሳል። (ጂ ኤሪክ ላኔ)፤

በመዝ 23 ዳዊት ሲናገር እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ከምቅበዘበዝበት ስፍራ ነፍሴን መለሳት አለ። ጌታ ይህን መመለስ በተለያየ መንገድ ይፈጽመዋል። አንደኛው መንገድ በመሪዎች፣ዲያቆናት እና መጋቢዎች ወይም በበጎቹ እረኞች ነው፤ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች ያለው ‹‹ስለ ነፍሳችሁ ይተጋ›› ዕብ 13፡17።

መንፈሳዊ እድገት፣ የዘላለም ሕይወት ባለቤትነቱ የእርሱ ነው፤ ስለዚህ የአንተን ስሜቶችና ነፍስህ በአደጋ ላይ ስትሆን አያድንህም፣ ጭካኔና ደግነት በሐኪሞች ጋ አለ ትንሽዋን ሕመም ለማዳን በሕጋቸው ላይ ታላላቅ በሽታ ይፈቅዳሉ። ብዙ መከራዎችንና ሥቃዮችን በማብዛት የአሁኑን ሕመም ያስወግዱታል ሕመምን ብቻ ሳይሆን ሞትንም ጭምር ማለት ነው። (ዮሐንስ ብራወን)

የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት ትልቅ ሐላፊነት ነው። ሙሴ የገጠመውን ችግር ተመልከት (ዘኁ 21፡5) ጳውሎስም እንዲሁ (2ቆሮ 13፡1-3)፤ የመጋቢ ሐላፊነቶቹ ብዙ ነው ፍላጎቶችም ብዙ ናቸው። ነገር ግን እውነተኛ የእግዚአበሔር ሰው ከሆነ እግዚአብሔርን ታመሰግናለህ፤ መጋቢው ፍጹም አይደለም ስህተት ሊሰራ ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ባሪያ ነው፤ እንደገና 1ተሰ 5፡12-13፣ 1ጢሞ 5፡17፣ዕብ 13፡7፣17 አንብብ እነዚህ ጥቅሶች ባህሪህን ይገልጻሉን?

ሕብረት

ክርስቲያን ስትሆን ወዲያው የታላቁ እግዚአብሔር ቤተሰብ ሆነሀል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ ዜጋ ሆነሀል (ኤፌ2፡19) በዳንህ ጊዜ አንተ በተለየ ስፍራ የምትኖር አይደለህም። የቤተክርስቲያን አካል ሆነሀል፣ ከሌሎች አማኞች ጋር በሕብረት መደሰት ይኖርብሃል፤በጣም የሚያስደስተው ነገር በዳንህ ጊዜ ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ተሳስረሃል ማለት ነው።

ሕብረት ማለት ‹‹በጋራ መሆንና ያለንን ነገር ማካፈል ማለት ነው›› የምናካፍለው ነገር ይኖራል። ይህም የተባረከው ወንጌል ነው፤ አንድ ሰው ለሌላው የሚያካፍለው ነገር አለው። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ራሱን ነው። ይህ የምንከፋፈለው ነገር ልምምድን ነው? ስለዚህ

ክርስቲያኖች ጌታን ማየት ብቻ ሳይሆን ወደ ግራና ቀኝም መመልከት ያስፈልጋቸዋል። ከአማኞች ጋር መተያየት ያስፈልጋል፤ አማኙ ብቸኛ ሰዉ ሳይሆን የሌሎች ወዳጅ ሆኖአል ማለት ነዉ(ኢ ኤፍ ኬቨን)

የእግዚአብሔር ሰዎች ከተለያየ ስፍራ የመጡ ሲሆን ሀብታምና ድሀ፣ነጭና ጥቁር፣ሰነፍና ጎበዝ የያዘ ሲሆን ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸዉ። በክርስቶስ ፍቅር ፊት ሁሉም ግድግዳዎች የወደቁ ናቸዉ፤(ኤፌ 2፡14-16፣ገላ3፡26-28) አዲስ ኪዳን በዚህ ምሳሌ የታሰረ ነዉ።

ከአስራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት መካከል ቀናተኛዉ ስምኦን ቀንደኛ የአይሁድ አክራሪ ብሔርተኛ ነበር፤ማቴዎስ ቀራጩ የሚጠሉት የሮማዉያን ባሪያ ነበር። እነዚህ ሁለቱ ሰዎች እርስ በርሳቸዉ ይጠላሉ ነበር ነገር ግን በክርስቶስ አንድ ናቸዉ።

በጋራ መከፋፈል

ሕብረት ማለት ጥቂት ክርስቲያኖች ተሰባስበዉ ስለ ወቅታዊ ጉዳይ፣ ስለ በዓላት፣ ወይም ስለማህበራዊ ነገር ማዉራት ማለት አይደለም። ክርስቲያኖች ተሰባስበዉ ቢጫወቱ በራሱ ችግር የለዉም። ዋናዉ የክርስቲያን የመሰባሰብ አላማ ያለንን ማካፈል ሲሆን የምናካፍለዉም ገንዘባችን፣እምነታችንን እና ችግሮቻችን ነዉ።

በአዲስ ኪዳን ህብረት የሚገለጠዉ እርስ በርስ ለመበረታታት ሲሆን ይህም በተለያየ መንገድ የሚታይ ነዉ።

- በአማኞች መካከል አንዳቸዉ ለአንዳቸዉ ወዳጅ በመሆን ነዉ። (ሐዋ 2፡44፣46፣4፡23፣20፡7)
- በፍላጎቶቻቸዉ ክርስቶስን ለመማር እና እዉነቱን ስለ እርሱ ያላቸዉን ልምምድ ለማካፈል ነዉ። (ሐዋ 2፡42፣20፡7፣11)
- በጋራ ይጸልዩ ነበር (ሐዋ 2፡42፣4፡24፣31፣12፡5)
- በአንድነት ይመሰክሩ ነበር (ሐዋ 4፡31፣33)
- አንዳቸዉ ለሌሎቹ ያስቡ ነበር (ሐዋ 2፡44-45፣4፡34-35፣11፡27-30፣ ሮሜ 12፡13፣1ቆሮ16፡1-3፣2ቆሮ8፡1-4፣ ገላ 2፡10)
- አንዳቸዉ ለሌላቸዉ ሸክማቸዉን ያካፍሉ ነበር (1ቆሮ12፡26፣ገላ6፡2)
- በክርስትናቸዉ እርስ በርሳቸዉ ይበረታቱ ነበር (ሮሜ 15፡1-3፣ገላ6፡1፣ዕብ10፡24)

- ሚሲዮናዉያንን በመርዳት (ፊሊ. 4፡14-16)
- ለጌታ ራት ጉዳይ በጋራ ይሰበሰቡ ነበር (ሐዋ 2፡42፣1ቆሮ10፡16-17)

እርስ በርስ መዋደድ

በሚያሳዝን መልኩ አንዳንዴ ክርስቲያኖች ሲሰባሰቡ በጣም በመከራከርና በጭቅጭቅ የተሞሉ ናቸዉ (ሐዋ 6፡1፣15፡36-41)። ሕብረታችንን መጠበቅ አለብን በምንም ምክንያት ሕብረት መፍረስ የለበትም።

ሁልጊዜ በፍቅር ጎዳና መጓዝ ያስፈልጋል፤ስለ ፍቅር በ1ቆሮ13 ላይ የተብራራ ነዉ፤ ‹‹ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤››

አስታዉስ ባለማወቅ ሰዎችን ልታሰቆጣ ትችላለህ ነገር ግን ባለማወቅም ቢሆን ሰዎችን ማስቆጣት የለብህም። እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ።

የቤተክርስቲያን ሕብረት በዚህ ላይ መደገፍ ያስፈልጋል። ከግለሰብ በላይ ቤተክርስቲያናችን መንፈሳዊ መሆን አትችልም። ቤተክርስቲያን የሐጢአተኞች ስብስብ መሆንዋን አንዳንዴ እንዘነጋለን፤ ሐጢአተኞች ናቸዉ በጸጋዉ የሚድኑት ማንም ሰዉ ፍጹም የለም። ትልቁ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ያለዉ ችግር ይህንን ነገር በደንብ አለመረዳታችን ነዉ፤ ራሳችንን አናዉቅም ስለሰዎች ያለን አመለካከት ደግሞ ትልቅ ነዉ እና የሌለንን ጥሩ ባህርይ ሌሎች እንዲኖራቸዉ እንፈልጋለን። ለምሳሌ እኛ በምንታመምበት ጊዜ ሰዎች ወደ እኛ መጥተዉ እንዲጎበኙን እንፈልጋለን ነገር ግን እኛስ ሰዎችን ለመጎብኘት ፈቃደኛ ነን? ማናችንም ፍጹም አይደለንም ስለዚህ ሁላችንም ትዕግስትን መለማመድ ያስፈልጋል። ይህ ለሀጢአት ቦታ መስጠት ማለት አይደለም። ትልቅ ትዕግስት ሲኖረን ፍቅርን እናዳብራለን።

ጥቂት ክርስቲያኖችን ማግኘት ቀላል ነዉ። ሌሎች ከባድ ነዉ ነገር ግን ሁሉም የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናቸዉ። ስለዚህ መስራት ይገባል ታገሱ፤ አስታዉስ ጥቂት ክርስቲያኖችን ማግኘት ይከብዳል ነገር ግን ታገስ።

ሕብረት ማለት እንደሚናገር ተሸከርካሪ ማለት ነዉ። የቅርብ ተናጋሪዉ የሞተሩ ዋና ክፍል ነዉ፤ እርስ በርሳችን መቀራረብ አለብን፤ከክርስቶስ ጋር ህብረት ማድረግ እንደሚያስደስት ሁሉ እንዲሁ ከእርሱ ሕዝብ ጋር እርስ በርስ ህብረት በማድረግ እንደሰታለን።

5

አምልኮ

በድነት ያገኘነዉ አንዱ ትልቁ እድል ከሰማይ እግዚአብሔርን እንድናመልከዉ መፍቀዱ ነዉ። መንግስተ ሰማይ ስንደርስ ደግሞ ቅዱሳን ለዘላለም እርሱን እያመለክን እንኖራለን፤ ራዕይ 5 እና 7 አንብቡ። ሰዉ የተፈጠረዉ ሐይለኛዉን እግዚአብሔርን እንዲያመልከዉ ነዉ፤ ነገር ግን ሐጢአት አበላሽዉ፤ በዘፍ 3 ላይ እንደምናነበዉ ሀጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሰላም አበላሽቷል። ሰዉ ከእግዚአብሔር መሰወርን ፈለገ (ቁ.8) ይህንን ማድረግ ቀጠለ፤ ሐጢአት ሰዉ እግዚአብሔርን እንዳያገኝ አደረገ (ቁ.22) ነገር ግን ያጣነዉን ነገር በድነት ጊዜ ተሀድሶ ተደረገ (ሮሜ 5፡1-2)። ሰዉ በሐጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ሲለይ አሁን ሊያድናቸዉ የማይችሉትን የራሳቸዉ አምላክ አዘጋጁ (መዝ 115፡4-8)፤ በዘመንኛዉ ቋንቋ ሰዎች ዛሬ ስፖርትን፣ መኪናን፣የአትክልት ስፍራን ወዘተ እያመለኩ ይገኛሉ፤

አሁን ግን አዳኙ ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አምጥቶናል፤(ዮሐ 14፡6)። መካከለኛዉ ሰዉ አለ (1ጢሞ 2፡5)፤ ለሀጢአትህ ስርየት አግኝተናል (ዕብ 9፡11-14) ስለዚህ አሁን ሐይለኛዉን እግዚአብሔር ማምለክ ቻልን፤

‹‹አምልኮ የልብ ትህትናን የሚጠይቅ ሲሆን በአክብሮት ማድነቅ፣መደነቅ፣ በጥሩ ልማድ መግለጽ ማለት ነዉ። አምልኮ ማለት በፍቅርና በመደነቅ በእግዚአብሔር በሀልዎቱ ፊት መፍሰስ ማለት ነዉ፤›› (ኤ ደብሊዉ ቶዘር)

አምልኮን መማር

አምልኮ ትልቅ ዕድል ስለሆነ አንድ ሰዉ ካመነ በኋላ በሕይወቱ ቅድሚያ ሊሰጠዉና ሊተገብረዉ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ። እግዚአብሔርን እንዴት ማምለክ እንዳለብህ በመማር ነዉ።

‹‹በመጀመሪያ ማምለክ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ተግባር ነዉ። አምነዉ ከተለወጡት ሰዎች ዉስጥ የሚሰሩ ሰዎች ይወጣሉ፤ እግዚአብሔር እንዲህ እንድንሆን አይፈልግም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚፈልገዉ የተለወጡ አማኞች እርሱን እንዲያመልኩት ነዉ። ከዚያ በኋላ ሰራተኛ መሆንን ይማራሉ፤›› ኤ ደብሊዉ ቶዘር

የአምልኮ ደረጃ ይመጣል እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገር ታመሰግናለህ፤ነገር ግን አምልኮ ከዚያ ያልፋል፤ እንደገና የቶዘር ትርጉም ‹‹ማድነቅና መደነቅ ነዉ›› በሌላ ቋንቋ እግዚአብሔር ምን ያህል ታላቅና ቅዱስ መሆኑን እንረዳለን ብዙ ማድነቅና አክብሮት ይኖራል፡፡ አምልኮ እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገር የምንገልጸዉ ሳይሆን ስለማንነቱ እና ማን እንደሆነ የሚገልጽ ነዉ፡፡ እርሱን ባወቅኸዉ መጠን ታመልከዋለህ፤ እርሱን ባወቅኸዉ መጠን ትወደዋለህ፤ ፍቅር ደግሞ የአምልኮ መሰረት ነዉ፡፡ *‹‹አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ።››* *ዘዳ 6፡5*

እግዚአብሔርን ሳንወደዉ ልናመልከዉ አንችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስና አመክንዮ በዚህ ላይ ይስማማል፤ ከዚህ ዉጭ እግዚአብሔርን አያረካም፤‹‹በፍጹም ልብህ፣...በፍጹም ነፍስ፣...በፍጹም ሐይልህ›› ፤ በመጀመሪያ ይህ ሊሆን አይችልም ነገር ግን በጥልቀት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ልምምድ ለዚህ ነገር ያዘጋጀናል፡፡ በዉስጣችን ያለዉ መንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር የፍቅር ሙላት ያደርሰናል፡፡ (ኤ ደበሊዉ ቶዘር)

በአምልኮ ዉስጥ የምንማረዉ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ማድነቅ ነዉ፡፡ አምልኮ ተቀባይነት እንዲያገኝ ግልጽ የሆኑ ነገሮች አሉ ይህም እግዚአብሔርን ማወቅ እና ቅዱስ የሆኑ አስፈላጊ መመሪያዎችን ማወቅ ነዉ፡፡ የመጀመሪያ አስፈላጊዉ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ የሆነ ሐሳብ ሊኖረን ይገባል፡፡ እዉነተኛ አምልኮ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ በሚገልጥልን መጠን ይወሰናል፡፡ በአደባባይ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና ስብከት ለጉባኤ አምልኮ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

ስለ እግዚአብሔር በጣም ትልቅ የሆነ ሐሳብ ሊኖረን አይችልም፡፡ በሐሳብ ደረጃ እዉቀቱ ሊኖረን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚችለዉ ራሱን ለእኛ በገለጠልን መጠን ነዉ፤ ባህርዩን፣ሐይሉን፣ ጥበቡን በገለጠልን መጠን እርሱ ሊታወቅ ይችላል፤መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔር ገልጦልናል እግዚአብሔር ታላቅና ፈጣሪ ነዉ፡፡ (ኢ. ኤፍኬቨን)፤

በግልህ ወይም በጋራ በቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ስታመልክ ማወቅ የሚገባህ ጉዳይ በእግዚአብሔር ሕልዉና ፊት በፍቅሩ መደነቅ ይገባል፤ አምልኮ በተለያየ መንገድ ይገለጻል፤ ይህም ሁለተኛ ጉዳይ ነዉ፤ ለምሳሌ በመቆም፣ በመንበርከክ፣ የጸሎት መጽሐፍን መጠቀም፣ ሶስት ወይም አራት መዝሙሮችን መዘመር እግዚአብሔርን ከማድነቅ አይበልጥም፡፡

እግዚአብሔርን ለማምለክ ሁለት ነገሮችን ማስተዋል አለብን፡፡ እርሱም እግዚአብሔር ሰሪያችንና ጌታችን መሆኑን በማወቅ ነዉ፡፡ ማንኛዉም አምልኮ በእነዚህ ዉስጥ ካላለፈ የሐሰት አምልኮ ይሆናል፡፡ በተለይ እግዚአብሔርን ስለማምለክ የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (መዝሙር 100 እና ዮሐ 4፡22-24) (ኢ ኤፍ ኬቨን)፡፡

ኢየሱስም አለ እግዚአብሔርን ለማምለክ ‹‹ በእዉነትና በመንፈስ ነዉ›› (ዮሐ4፡24)

‹‹ በመንፈስ ማምለክ›› ማለት በመንፈስ ማምለክ ሲሆን በእዉነት ማምለክ ማለት በእዉነት ማምለክ ነዉ፡፡ ሁለት የተለያየ የአምልኮ አይነት ሳይሆን አንድ አምልኮ ሆኖ የተለያየ መልክ ያለዉ ማለት ነዉ፡፡ በመንፈስ ማምለክ ማለት ዉጫዊ የሆነ ሐይማኖታዊ ስርዓትን የሚቃወም ነዉ፡፡ ለእግዚአብሔር የበራ ልብ እርሱን የሚያዉቅ ልብ፣ ማድነቅ፣ ፍቅር፣ መታመን፣ ለእርሱ መገዛት፣ እርሱን በእዉነት ማምለክ ባህርይዉን ለመግለጽ እና ለመቅረብ ሲሆን ይህም በርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ አምልኮ ነዉ፡፡ (ዮሐንስ ብራወን)

አምልኮ ስሜትን ከማርካት ያለፈ ትርጉም ያለዉ ሲሆን፣ አእምሮም ይሳተፍበታል፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ለእዉነተኛ አምልኮ ወሳኝ ነዉ፤ ነገር ግን አእምሮ በጥሩ አስተምህሮ ተሞልቶ ልባችን ግን ከእግዚአብሔር መገኘት ቢርቅ እዉነተኛ አምልኮ አልተከናወነም፡፡ በእዉነት እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማመስገን ልብ እና አእምሮ መገናኘትና አንድ መሆን አለበት፡፡

የጉባኤ አምልኮ

ወደ ክርስቲያኖች አምልኮ ስፍራ ስትሄድ ቀለል ባለ አስተሳሰብና ልብ መሆን የለበትም፤ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ መሆን አለበት፤ሐይለኛዉን እግዚአብሔርን መገናኘት ይኖርብሃል፡፡ ተስፋ በማድረግና ወደፊቱ ቅረብ እግዚአብሔርን ተገናኘዉ፣ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ አምልከዉ፤ መዝሙሮቹ ስሜትህን የሚገልጹ ይሁኑ፤ ለመደሰት ብቻ አትዘምር ነገር ግን እግዚአብሔርን በማምለክ ዘምር፡፡

ከሁሉም በላይ በመንፈስ ዘምር ስትዘምር እግዚአብሔርን የምታይበት እይታ ይኑርህ፡፡ ዓላማህ ራስህንና ፍጥረትን ከማስደሰት በላይ እርሱን ማስደሰት ይሁን፤ ይህን ለማድረግ የምትዘምረዉን መዝሙር አስተዉል ልብህ በድምጽ የተሞላ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡ (ጆን ዊስሊ)

በጸሎት ጊዜ ሀሳቦችህንና ገለጻዎችንና ስሜቶችህን ሁሉ በመቆጣጠር አንድ በማድረግ ተከተል፤መጽሐፍ ቅዱስህን መያዝ አትዘንጋ ለማንበብና ለመስበክ ዝግጁ ሁን፤ ስብከቶችን በጥሞና ተከታተል፤ ካልገባህ አምልኮው ሲያበቃ ሰዎችን ጠይቅ።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ወደ አምልኮ አዳራሽ አይገቡም፤ሁሉም አማኞች በሚሳተፉበት ጊዜ እኛም አብረን መሳተፍ ይገባናል። በዚህ ጊዜ አብረን ላንዘምር፣ ላንጸልይ፣ ስብከት ላንሰማ ሁሉ እንችላለን፤እያንዳንዱ ሰዉ በትኩረት መከታተል ያስፈልገዋል። ጆን ዌስሊ ስለመዝሙር የተናገረዉን አይተናል በጸሎትና ስብከት ላይም እንዲሁ ነዉ። አንድ ሰዉ በጸሎት ሲመራ ሌላዉ ተከትሎ መጸለይ ያስፈልጋል፤መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ ስብከትና ከመንፈስ ቅዱስ አሰራር ዉጭ ምንም ሊያነቃቃን የሚችል ነገር አይኖርም። ሰባኪዉ እየሰበከ ልብህን የሚያነሳሳና አዳኙን እንድታደንቅ ሲያደርግ አንተም አብረህ እያመለክህ ነዉ ማለት ነዉ። እርሱ ይሰብካል አንተ ትሰማለህ ነገር ግን ሁለታችሁም በጋራ እያመለካችሁ ነዉ። አምልኮ በእሁድ ቀን በአዳራሽ ዉስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ለእግዚአብሔር ሕዝቦች የተሰጠ እድል ነዉ ይህ የአንተ እድል ነዉ።

ሐያሉ እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት ታላቅነቱን ማሰብና ሐጢአተኝነታችንን ማየት ማለት ነዉ፤ ልብህ በፊቱ ትሁት ይሁን በምስጋና መፍሰስ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔርን መምሰል ታላቅ ሚስጢር ነዉ

እግዚአብሔር የራሱ ቅድስና

ነፍሴን ያነቃቃታል ትናፍቅሃለች

ትልቅ ደስታን ያመጣል

ከልቤ አመሰግናለሁ፤

ክርስቶስ ስለሞተልኝ የእኔ ነዉ ብየ እጠራዋለሁ

እንዲህ አልኩ እዘምርለታለሁ

ኢየሱስ ተመስገን የፍቅር ንጉስ አደንቅሃለሁ፤

(ደብሊዉ ቨርነን ሀያም)

6

መመስከር

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ለሐዋርያቱ የሰጠዉ የመጨረሻ ቃል እንዲህ የሚል ነዉ ‹‹ምስክሮቼ ትሆናላችሁ›› እያንዳንዱ ክርስቲያን ምስክር ነዉ፡፡

ምስክር መሆን ትኩረት በማድረግ ይጀምራል፤

ምስክርነት በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ክብር ላይ ትኩረት ከማድረግ ይጀምራል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ አለም ሰዎች አይከበርም ምክንያቱም አብዛኛዉ ሕዝብ እርሱን አያዉቀዉም አይወደዉምም፡፡ እዉነቱን በጭቃ ላይ የሚጥሉና ስሙንም እንደ ከንቱ የሚቆጥሩ ናቸዉ፤ይህን ነገር ሊቀይሩ የሚችሉ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸዉ፡፡ እስኪ ራስህን ተመልከት ከማመንህ በፊት ስለ እግዚአብሔር ያለህ አመለካከትና አሁን ያለህን አመለካከት አነጻጽር፤ ለእግዚአብሔር ክብር ትኩረት ስትሰጥ ለሰዎች መልካሙን ዜና ወንጌልን ትናገራለህ፡፡

ሁለተኛዉ ምስክርነት የሚጀምረዉ ለሰዎች ትኩረት ስንሰጥ ነዉ፤ ትኩረት ላላመኑ ሰዎች በእስራትና በእዉርነት ዉስጥ ላሉ ማለት ነዉ፡፡ ያለክርስቶስ ወንድ ሆነ ሴት ወደ ሲኦል የሚገባ ነዉ፤ ሽክም ይሰማሀል? ምስክርነት ብቸኛዉ ወደ ድነት የሚያመጣ ነዉ፡፡

ብዙ ክርስቲያኖች ለመመስከር ያፍራሉ ተቃዉሞ መነሳት የወንጌሉ ባህርይ ሲሆን ይህም በመልካም ሀሳብ የሚከናወን ነዉ፤ ነገር ግን ለችግሮች ሁሉ መልስ የለም፤ ምስክርነት ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ሰዉ ሰራሽና ስልታዊ ነዉ፡፡

ምስክርነት የሚወጣዉ ከአምልኮ ነዉ

ምስክርነት ከትኩረት የሚጀምር ከሆነ ምስክርነትም የሚወጣዉ ከአምልኮ ነዉ፡፡ ብዙ የቆዩ ክርስቲያኖች ለአዳዲስ ክርስቲያኖች እንዴት መመስከር እንዳለባቸዉ ማስተማር ያስፈልጋቸዋል፤ ይህ ስህተት ነዉ፤የአዳዲስ ክርስቲያኖች መጀመሪያ የሚያስፈልጋቸዉ ነገር አምልኮ ነዉ፤ የሰዎች ህይወት በእግዚአብሔር ካልተማረከ ምስክርነት ከበድ የሚል ነገር ነዉ፡፡

ልቤ በክርስቶስ ተሞልቷል

ክብሩን እናፍቃለሁ እናገራለሁም

ለእርሱ እዘምራለሁ

ምላሴ ለዝማሬ ተዘጋጅቷል

ሰማያዊውን ንጉስ ክብር እናገራለሁ።

ቻርልስ ዌስሊ ትክክለኛ ሲሆን ልብህ ክርስቶስን በማምለክ መሞላት አለበት።ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነትና አምልኮ ለምስክርነት ዋና መሰረት ናቸዉ። (ሐዋ 2፡41-47)

እግዚአብሔር ሰባኪ ወይም ሚሲዮናዊ ብሎ አይጠራህም። ነገር ግን ክርስቶስን ባመንህ ጊዜ በዚህ ዓለም ምስክሬ ነህ ብሎ ጠርቶሃል። በሐዋ 11 ላይ ወንጌልን ወደ ዓለም ሲያሰራጩ እንመለከታለን።እግዚአብሔር ታላላቅ ሰባኪዎችን ብቻ ሲጠቀም አናይም።ተራና ፈሪ የሆኑ ሰዎችን ሲጠቀም እናያለን። ‹‹*ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ። የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።(ሐዋ 11፡20-21)* ከእነዚህ ስም ከሌላቸዉ ቅዱሳን መማር ያስፈልጋል።

በቃልና በሥራ

ክርስቲያን ተብለህ ከተጠራህ ጀምሮ የምታደርገዉ ነገር ሁሉ ምስክርነት ነዉ። ጥሩ ወይም መጥፎ ምስክርነት ሊሆን ይችላል። ባህርይህ ከቃላት በላይ በጣም አስፈላጊ ነዉ። ሰዎች የምትናገረዉን ነገር በተግባር ካላሳየህ ንግሮችህን ሊያምኑ አይችሉም።ምስክርነት በሕይወታችን አልፎ አልፎ የሚታይ ሳይሆን ሃያ አራት ሰዓት የሚታይ ነዉ።

ያላመኑ ሰዎች ሕይወትህ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመሆኑና ስለ አለመሆኑ ያዉቃሉ። ወንጌሉ መነገር አለበት።(ሮሜ10፡14)። ሰዎች በቤት፣በትምህርት ቤት፣ በቢሮ ወይም በፋብሪካ እግዚአብሔር ያዘጋጀዉን ድነትና ፍቅር ማየት አለባቸዉ። የማትነግራቸዉ ከሆነ ሌላ የሚነግራቸዉ ሰዎች ሊኖሩ አይችሉም።

ምስክርነትህን ያለገደብ ልትሰጥና ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን የግል ልምምድ መናገር ያስፈልጋል። ዓላማህ ወንጌልን ለሰዎች ሁሉ ማድረስ ሊሆን ይገባል። ሰዎች ሐጢአተኛ

መሆናቸዉ ሊነገራቸዉ ይገባል (ሮሜ3፡23)፡፡ ከእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ በታች መሆናቸዉ ሊያዉቁና ሊነገራቸዉ ይገባል (ሮሜ1፡18)፡፡ ሰዎች በእግዚአብሔር ተፈርዶባቸዋል (ዮሐ 3፡18) ስለዚህም እግዚአብሔር ንስሀ እንዲገቡ እንደሚፈልግ ንገራቸዉ (ሐዋ 3፡19፣17፡30) ስለዚህ ለድነት ወደ ክርስቶስ መመለስ ይገባል (ኤፌ 2፡4-9፣ዮሐ1፡12)፡፡

በምስክርነትህ ትዕቢተኛ ወይም ሐይለኛ መሆን የለብህም፡፡ በሌላ መልኩ ማፈርና ይቅርታ መጠየቅ የለብህም፤ የእግዚአብሔርን ነገር በሞቀና በተነቃቃ ሕይወት መስክር፤ ለማሸነፍ የመከራከሪያ ነጥብ አዘጋጅተህ ከልክ በላይ አትሂድ፤ ታገስ ወደዳቸዉም፤ እንግዳ ስለሆነዉ እምነት አትደነቅ (ሐዋ 26፡24፣1ቆሮ4፡10)፤ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ጠቁም፣ ስሙ በከንፈርህ ላይ በተደጋጋሚ ሊነገር ይገባል ሰዎች የአንተን ሕይወት አይተዉ የክርስቶስ አገልጋይ መሆንህን ያዉቃሉ፤ ለእያንዳንዱ ሰዉ ሸክም ይኑርህ፡፡

‹‹አንድ መቶ ባዶ ጠርሙሶች በፊትህ ቢኖር የተጠራቀመ ዉሃ ብታፈስባቸዉ አንዳንዶች ጥቂት ዉሃ ይይዛሉ፣ብዙዎቹ ግን ይወድቃሉ ነገር ግን በደንብ ዉሃ ለመሙላት ከተፈለገ እያንዳንዱን ጠርሙስ ወስዶ መሙላት ነዉ፤ይህም በግል ዉጤታማ ስራ ይሰራል፡፡››

ሲ ኤች ስፐርጅን

7

ጸሎት

ጸሎት ፍላጎቶቻችንን ለእግዚአብሔር የምናቀርብበት፣ ከፈቃዱ ጋር የምናስማማበት በኢየሱስ ስም ሀጢአታችንን የምንናዘዝበት፣ ስለምህረቱ ምስጋና የምናቀርብበት መንገድ ነዉ፡፡

አጭር ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሌለዉ ሕዝብ የሚለየዉ ዋናዉ ነገር ጸሎት ነዉ፤ የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከቱ

ሙሴ ዘጸአት 33፡12-22

ዳዊት	2ሳሙኤል 7፡18-29
ዳንኤል	ዳንኤል 9፡3-19
ጳውሎስ	ኤፌሶን 1፡15-23

እነዚህ ሰዎች ከተለያ ስፍራ ቢመጡም ሁሉም የጸሎትን ዋጋ የሚያውቁ ናቸዉ። እነዚህ ሰዎች ታላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች የተባሉት አስቀድመዉ ተራ የሆኑ ሰዎች ነበሩ፤ በያእቆብ መልዕክት ዉስጥ ኤሊያስ እንደ እኛ ያለ ሰዉ ነበር ይለናል (5፡17)። ‹‹ኤሊያስ እንደ እኛ ያለ ሰዉ ነዉ››ተመሳሳይ ስሜቶች፣ተመሳሳይ እንባ፣ተመሳሳይ ጥርጣሬ፣ልክ እንደ እኛ ያለ ሰዉ ነዉ፤ ይህን ለማመን ይከብዳልን? 1ነገስት 17፣18፣እና 19።

አንዳንድ ጊዜ በጋራ አስበን ወዲያዉ ሮጠን እንሄዳለን? ኤሊያስ ያደረገዉ ነገር (1ነገስት 19፡14) አንዳንዴ ብቸኝነት እና ሌሎች እንዲያስቡልን እንፈልጋለን? ኤሊያስ ይህን አድርጓል (1ነገ 19፡14)፤ ይህ ሰዉ ታላቅ የጸሎት ሰዉ ነበር። ‹‹ የጻዲቅ ሰዉ ጸሎት በሥራዋ ታላቅ ነገርን ታደርጋለች›› (ያዕ 5፡16)

ጸሎት በሕይወትህ ምን ነገሮችን አደረገ? አልፎ አልፎ በሕይወትህ የሚኖር ነዉ ወይስ አልፎ አልፎ ነዉ? ወይስ ችግር ሲኖር ነዉ የምትጸልየዉ? በየቀኑ ደስ ብሎህ የምታደርገዉ ነዉ? ወይስ እንደ ከባድ ስራ የምትቆጥረዉ ነዉ? በክርስቲያን ሕይወት ዉስጥ ጸሎት የሚጫወተዉ ሚና ምንድን ነዉ?

የትላልቅ ሰዎችን ምስክርነት አይተናል አሁን ደግሞ የኢየሱስን ምሳሌ እንመልከት። ኢየሱስ ቀኑን በጸሎት ጀመረ፤(ማር 1፡35)፤ በሁሉ ነገር ይጸልይ ነበር ይህም፤

የጥምቀት በረከት	ሉቃ 3፡21
የመለወጡ ደስታ	ሉቃ 9፡29
በጌቴሴማኒ መከራ	ማቴ 26፡36-44
በተፈተነ ጊዜ	ዮሐ6፡15፣ ማቴ 14፡23
ሐላፊነትና ትልቅ ዉሳኔ በወሰነ ጊዜ	ሉቃ 6፡12-13

ጸሎት ንጹሁ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ካስፈለገዉ እኛማ እንዴት ብዙ አንጸልይም? ጳዉሎስ ብዙ መጸለይ እንዳለብን እና ‹‹በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤(ኤፌ 6፡18)፡፡ በጸሎት ሁሉ የሚለዉ ንግግር ማንኛዉም አይነት ጸሎት ማለት ነዉ፤ ሦስት አይነት ጸሎቶች አሉ እነዚህም፤

የግል ጸሎት

ኢየሱስ ይህን የተናገረዉ በማቴ 6፡6 ላይ ሲሆን ‹‹ዝጋ›› የሚለዉ ቃል የራስህን ክፍል ቤት በር ማለት ነዉ፤ በሌላ ቋንቋ ከሰዎች በመለየት በተለይ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ መሆን ማለት ነዉ፡፡ ይህ ጸሎት አስፈላጊ እንጂ የምርጫ ጉዳይ አይደለም፤ በሕይወታችን የምንፈጽመዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ በጣም አስፈላጊ ነዉ እንግዳ ነገር አይደለም ሰይጣን ልዩ የሆነ ነገር አድርጎ ሊያሳየን ይፈልጋል፤ ለብዙ ክርስቲያኖች ጸሎትን መለማመድ ከባድ ጉዳይ ነዉ፤ ትኩረት ማድረግ ከባድ ሊሆን ይችላል፤ አእምሮህ ብዙ ጊዜ ይባዝናል ክፉ ሀሳብን ሊያስተናግድ ይችላል፤ ክርስቲያኖች ከአምስት እስከ ስድስት ሰዓት ይጸልያሉ የሚል መጽሐፍ አንብበህ ይሆናል ሰይጣን ደግሞ የአንተን የ5 እና 10 ደቂቃ ጸሎት በማነጻጸር ያሳይሃል ከዚያም ተስፋ እንድትቆርጥ ያደርግሃል፤ ነገር ግን እንደዛ ማድረግ የለብህም፤ ሰይጣን እንዲያታለልህ እድል አትስጠዉ፤ አሁን አዲስ ክርስቲያን ነህ ከሃያ አመት በኋላም ተመሳሳይ ችግር ይኖርሃል፤ ዋናዉ የዕድሜ ወይም የመቆየት ሳይሆን የጥቂት ልምምድ ጉዳይ ነዉ፤ ከሰይጣንና ከስጋ ጋር በቋሚነት በጦርነት ላይ ነን፡፡

ስለ ጸሎት ያለን አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ጸሎት ከባድ ከሆነ አይጠቅምም ወይም ትክክል አይደለም እያልን ነዉ፤ ጳዉሎስ ስለ ጸሎት ሲነግረን ‹‹መጋደል›› ነዉ ይለናል (ቆላ 4፡12) እና ‹‹ ተጋድሎ›› ነዉ (ሮሜ15፡30)፤ ትልቅ ጦርነት ዉስጥ እንዳለ ተረድቶአል፤ ክርስቲያን ሲጸልይ በጦርነቱ ግንባር ላይ አለ ማለት አይደለም፡፡

ቃላቶቻችን ትክክለኛ አይደሉም ብዙ ሰዎች ዛሬ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸዉን ጊዜ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቃላት ‹‹የጥሞና ጊዜ›› የሚል ነዉ፤ ርዕሱ ስህተት ተጽዕኖን ፈጠረ፤ ስለ ጥሞና ጊዜ ሳስብ ምንም ችግር እንደሌለና ሰላም እንደሆነ ነዉ፤ እግዚአብሔር ይመስገን ጸሎት ቀለል ሲልብን መንፈሳችን ከፍ ይልና በእግዚአብሔር ይደሰታል፤ ነገር ግን

ሁል ጊዜ እንደዛ አይደለም፤ ጸሎት ማለት መድከም፣ መጋደል እና መዋጋት መሆኑ ብዙ ክርስቲያኖች ሲዘነጉ ዳቢሎስ ይደሰታል።

እነዚህ ችግሮች ከመነሳታቸዉ በፊት መንበርከክ ያስፈልገናል፤ ለመጸለይ አመቺ ጊዜ መፈለግ ከባድ በሚሆነን ጊዜ በተጠመደልን ወጥመድ ዉስጥ ገብተን በቀላሉ እንወድቃለን፤ በዚህ ጊዜ ዲብሎስ ያየናል።

እነዚህ ችግሮች ሁሉ እያነሳሁ ተስፋ ማስቆረጥ አልፈልግም፤ እዉነተኛ ክርስቲያን ከሆንክ እነዚህን ሁሉ ታያለህ ታልፋቸዋለህም፤ ጥያቄዉ ግን እንዴት አስተናገድካቸዉ የሚል ነዉ። መልሱን እኔ ልመልስልህ እችላለሁ፤ መደበኛ የሆነ ጊዜ ወስን ከዚያም ጋር ተጣበቅ አእምሮህ ሲባዝን ድምጽህን ከፍ አድርገህ ጸልይ፣ አታቋርጥ ይልቁን ተጋደል እንጂ፤ እነዚህ መልሶች ጠቃሚና አስፈላጊ ናቸዉ። ትክክለኛዉ መልስ ግን ያለዉ ‹‹ በመንፈስ ጸልዩ›› የሚለዉ ነዉ፤ (ኤፌ 6፡18)።

በመንፈስ ጸልዩ ማለት ጸሎት ማለት በምላሳችን የምንናገረዉ ደረቅ ቃል፣ ባዶና ስርአት ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ተቃራኒዉ ነዉ፤ በሐይል በእዉነትና በጥልቅ ፍቅር መሆን አለበት። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ነዉ በልባችን እና በአእምሮአችን ጸሎትን የሚፈጥረዉ፤ የምትጸልየዉ ስለፈለግህ ወይም ስራ ስለሆነ አይደለም ነገር ግን ጥያቄዉ የሚመጣዉ ከመንፈስ ቅዱስ ነዉ፤ መንፈስ ቅዱስ የምትጸልይበትን ርዕስ መስጠት ብቻ ሳይሆን የሚያደርገዉ እንድትጸልይ ሐይልና ብርታትን ይሰጣል።

እንዴት ነዉ በመንፈስ የሚጸለየዉ? ስለ ጸሎት ያለህን ነገር ተመልከት ልክ በየቀኑ እንደምታደርገዉ ሳይሆን እንደ ግል አምልኮ ጊዜ አድርገህ ዉሰድ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ትገናኛለህ እና ራስህን አዘጋጅ፤ ይህ ራስን ማስገዛትን ይጠይቃል፤ ለጸሎት ጊዜ ስጥ፣ በጸሎት መቸኮል የለብም፣ ጥቂት ጥያቄዎችን አቅርብ፣ ከዚያ ማቆም፤ ‹‹እኔ እግዚአብሔር መሆኔን ታዉቃላችሁ›› ወደ ጸሎት ስትቀርብ ሐጢአተኛና ለዚህ የማትበቃ መሆንህን እወቅ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ምህረት አሰላስል፤ የአለምን በር ዝጋና ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ተገናኝ። ይህ ቀላል አይደለም በጸሎት እንቅስቃሴ ዉስጥ ስንገባ የሚያረካ ነዉ። መንፈሳዊ ሐሳብ ይኑርህ ከማንም በላይ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ፈልግ መንፈስ ቅዱስ ሐሳብህን እንዲመራዉ ፍቀድለት፤ የሚከተሉትን ሐሳቦች የተወሰደዉ ከዶ/ር ዲ.ኤም ሊዮድ ጆንስ ሲሆን በጥንቃቄ አንብበዉ።

‹‹በምትጸልይበት ጊዜ ልብህ በጌታ ኢየሱስ ፍቅር ካልተሞላና ካልተቀጣጠለ ጸልየሃል ማለት አይቻልም። መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ፍቅርና መረዳት ያመጣል፤ ወደ ቅድስናዉ መግባት የሚቻለዉ በክርስቶስ ኢየሱስ ደም በኩል ነዉ፤ ይህን ስታስብ ልብህ ይሞቃል ይቀልጣልም የሆነ ነገር በሕይወትህ ሆኖአል ማለት ነዉ። ‹‹ በመንፈስ መጸለይ›› የሚለዉን ሐሳብ ስታደርግ አሁን በጥሩ መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ አለህ ማለት ነዉ። በዚህ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት አድርገሃል ማለት ነዉ። በዚህን ‹‹ቅዱስ የሆነ ድፍረት›› ይኖርሃል፤ በጸሎት ነጻነትን እንደ ማግኘት በምድር ላይ የሚያስደስት ነገር ይኖራልን? በዚህ ትደሰታለህን? በድንገት ነጻነትን ስታገኝ በጸሎት ደግሞ መታገል ይኖርብሃል፤ ትኩረት ስታደርግ ሀሳብን ሰብስብ በማድረግ ግንኙነት መፍጠር በድንገት ነጻነትን ይሰጣል፤ በጉባኤ ጸሎት ትጸልያለህ? የማሰናከያ እንቅፋት ሆነሀል? መሄድ አልቻልምን? የምትጸልየዉ በአእምሮህ ነዉን? ሀሳቦችን በስርዓት ታደርጋቸዋለህን? ጥያቄዎችህን ሰብስባቸዉ፤ ያንን ማድረግ ይገባል፤ የምትከሰስበት ሁኔታ እንኳ ቢኖር ማቆም የለብህም፤ ወዲያዉኑ መንፈስ ቅዱስ ይመጣና ከራስህ ዉስጥ ያወጣሃል፤ ቃሉ በአንተ ላይ ሲፈሰስ በዚህ ጊዜ ለጌታ መናገርህ ይገባሃል፤ ስለዚህ መለዋወጥ ማለት ነዉ። በመንፈስ ዓለም ዉስጥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ስለዚህም በክብሩና በነጻነቱ መደሰት አለብህ››።

የመጨረሻዉን ጽሑፍ አንብብ፤ ስለዚህ ሁላችንም ጸሎትን መለማመድ ያስፈልገናል ይህ ማለት ግን እዉነተኛ ጸሎት የለም ማለት አይደለም። ይህ ማለት በመንፈስ አትጸልይም ማለት አይደለም፤እዉነተኛ ጸሎት አልጸለይክም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ሐሳባችን ያከብራል፤ እግዚአብሔር ያዉቃል ይወደናልም፤ የእኛን ትንሽ ጸሎት ጊዜ፣ድህነታችን፣ያልተገባን መሆናችንን ያከብረዋል፤ ድካማችንን፣ ፍርሃታችንን፣ ጥርጣሬንና ኢፍትሐዊነታችንን ሁሉ ያያል፤ የምሕረት አምላክ ሁልጊዜ የሕዝቡን ጩኸት ይመለከታል፤ በዳቢሎስ የሚነሳዉን እንቅፋት ሁልጊዜ በጸሎት ማፍረስ አለብን፤ መድከምና መልፋት አለብን ከዚያም በላይ በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ወደ እግዚአብሔር መጮህና በመንፈስ መጸለይ አለብን።

የጸሎት ስብሰባ

የግል ጸሎት አስፈላጊ ነዉ፤ ነገር ግን የማህበር /የጉባኤ/ ጸሎት እጅግ አስፈላጊ ነዉ። የቤተክርስቲያን አባላት በሙሉ በጋራ ሲጸልዩ እንዴት ዉብ ነዉ! ይህንን (በሐዋ 4፡23-31) ምሳሌ ማየት ይቻላል፤ ክርስቲያን ከሆንክ በመጀመሪያ የማህበር ጸሎትን ማስቀደም አለብህ፤

ይህም ከሴቶች ህብረት፣ ከወጣት ቡድን፣ ወይም ከሰንበት ትምህርት ቡድን የሚበልጥ ጉዳይ ነዉ።ከስራ ብዛት የተነሳ ጸሎትን መካፈል የማትችል ከሆነ፤

‹‹አንድ ሰዉ በግሉ የማይጸልይ ከሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ መናገር አይችልም፤ በማህበርም የማትጸልይ ከሆነ በሕይወት አለሁ አትበል››

ሮበርት ሙራይ ኤም ቸይኔ

ዳቢሎስ የጸሎት ስብሰባን ይጠላል። የጸሎትን ስብሰባ ለማጥፋት ይጥራል። ስለዚህ ክፉ የሆነዉ ክንዱ እንዲሰበረ መጸለይ ያስፈልጋል።ብዙ ክርስቲያኖች አይጸልዩም ጥቂት ክርስቲያኖች ግን ለረዥም ጊዜ ይጸልያሉ።ይህም ለማጉረምረምና ለክስ በሮችን የሚከፍት ነዉ።የጸሎትን ህብረት መክሰስ ይቻላል ነገር ግን ከመክሰስህ በፊት ምን ያህል እኔ ለዚህ የጸሎት ህብረት ያደረኩት አስተዋጽኦ ምንድን ነዉ? ብለህ አስብ የጸሎት ህብረት ማለት ዋና የቤቱ ሐይል ማለት ነዉ። ይህ ፍጹም እዉነት ነዉ። በድስት ዉስጥ እሳት ሲቀጣጠል ብታይ ተስፋ አትቁጠር ጽና፤ በመክሰስ ሳይሆን በጽናት በጸሎት ወደፊት ቀጥል፣ጸልይ፣አዲስ ክርስቲያን ልትሆን ትችላለህ እንደቆዩት መጸለይ ትችላለህ ጸሎቱ ለሁሉም ቤተክርስቲያን የበረከት ምንጭ መሆን አለበት።

ሁልጊዜ መጸለይ

ጸሎት አሁን ልንገልጸዉ ከምንችልዉ በላይ ትርጉም ያለዉ ነዉ። አንድ ሰዉ ቀጣይነት ያለዉ የመንፈስ ጸሎት ሊጸልይ ይችላል። ሳትንበረከክና ዓይንህን ሳትጨፍን መጸለይ ትችላለህ፤ መኪና እየነዳህ፣ ጓሮ እየቆፈርህና ዕቃዎችን እያጠብክ መጸለይ ትችላለህ። በዚህ ሁሉ ልብህን ወደ እግዚአብሔር ማንሳት ትችላለህ።ቀኑን በሙሉ እንዲህ የምታደርግ ከሆነ በስራ ቦታ ሁሉ ለሚገጥምህ ማንኛዉም ተግዳሮቶች ራስህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ትሰጣለህ። እንደ ፈሪሳዉያን አይነት ሳይሆን በልብህ ጌታ ሆይ ርዳኝ ማለት ትችላለህ። ነህምያ ይህን አድርጓል (ነህ2፡1-5) *‹‹ንጉሡም፦ ምን ትለምነኛለህ? አለኝ። እኔም ወደ ሰማይ አምላክ ጸለይሁ...››* ቁ.4 ይህ የሆነዉ በማይክሮ ሴኮንድ ዉስጥ ነዉ። አንዳንድ ሰዎች ይህንን አይነት ጸሎት ለእግዚአበሔር ቴሌግራም መጻፍ ነዉ ይላሉ። አገላለጹ ቀረቤታን የሚመለከት ሲሆን ቀለል ያለ ጸሎት ‹‹ጌታ ሆይ ተመስገን›› ወይም ‹‹እግዚአብሔር ሆይ ርዳኝ›› ሊሆን ይችላል። እነዚህን ሶስት ዓይነት ጸሎቶች አስፈላጊ ናቸዉ። ሁልጊዜ በቀጣይነት ልንተገብራቸዉ የሚገባ ነዉ። በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ ስለጸሎት በሰፊዉ ተጽፏል ምክያቱም በጣም አስፈላጊ በመሆኑ

ነው። የክርስቲያን የጸሎት ሕይወት ደካማ ከሆነ አጠቃላይ ሕይወቱ ደካማ ነው። የጸሎት ሰው ስትሆን ሁሉም ነገር ይከተልሃል።

የመጨረሻው ሐሳብ ማንኛውንም በጸሎት ጉዳይ የተጻፉትን መጻሕፍት አንብብ። በጸሎት ለመበርታት የሚያስፈልገው ነገር መጸለይ ብቻ ነው።

8

መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ፡ የትኛው ትርጉም?

በክርስትና ከሃምሳ አመት በላይ ከሆነህ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም አለብህ። (በርግጥ ይህ የዘመኑ ጉዳይ ነው) ሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች አሉ። የአሜሪካኑ እትም በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ተወዳጅ ነው። ዛሬ በዘመናችን በተለይ አዳዲስ ክርስቲያኖች የትኛውን እትም ማንበብ እንደሚገባቸው ግራ በመጋባት ላይ ናቸው። ከ1961 ዓ/ም ጀምሮ ብዙ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ተጽፈዋል። በዚህ ላይ ተጨምሮ (የአሜሪካን እትም እና ሪቫይዝድ ስታንዳርድ እትም ተጨመረ 1952) በመቀጠልም አዲስ ኪዳን አዲሱ መደበኛ ትርጉም ታተመ። ዛሬ ብዙ እትሞች አሁን ጥቅም ላይ ዉሏል። በአንድ ጉባኤ ከ 4 አሰከ 5 የሚደርሱ እትሞችን ይጠቀማሉ። እነዚህን እትሞች መጠቀም በተለይ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ግራ መጋባትን ይፈጥራል። ከብዙ አመታት በፊት ከማቴ 17፡21 ላይ እሰብክ ነበር ‹‹*ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው››(አሜሪካ እትም)* አንድ አዲስ ክርስቲያን ግራ በመጋባት ዉስጥ ሆኖ ክፍሉን ይመለከተዉ ነበር። ምክንያቱም እርሱ ሌለኛዉን እትም ይዞ ስለነበር ነዉ። እርሱ በያዘዉ እትም ላይ ቁ.21 የለዉም። **እኔ ያነበብኩት** ክፍል እርሱ **በያዘዉ** እትም ዉስጥ የለም።

የቃል በቃል ትርጉም ወይስ ሀሳብ ትርጉም

የሐሳብ ትርጉም ብዙ ጊዜ ግራ መጋባትን በማህበረሰቡ ዉስጥ ይፈጥራል። ሐሳቡን መተርጎም ማለት **በመጀመሪያዉ ክፍለ ዘመን** የነበረዉን መጽሐፍ ቅዱስ ሐሳቡን ወደ አሁኑ ዘመን ቋንቋ መተርጎም ማለት ነው። (ኬ ኤም ታይለር) የኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ስለ ቃላቱ ሲያብራራ

ክፍሉን ማብራራት ወይም ማጉላት ብሎታል፤ ይህ ቃላት በጣም ጠቃሚ ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ ለአንዳንድ ችግሮች ዳርጎአል።

ለምሳሌ የሐሳብ ትርጉምን የተቀበሉ እንደ አሜሪካ ትርጉም፣ የሪቫይዝድ ስታንዳርድ እትም እና አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከ1971ዓ/ም ጀምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እትሞች ታትመው ገበያ ላይ ዉለዋል። የቃል በቃል ትርጉምና የሐሳብ ለሐሳብ ትርጉም መካከል ያለዉ ልዩነት ምንድን ነዉ? ቃል በቃል የሚተረጉመዉ ሰዉ የመጀመሪያዉ (ኦሪጂናል) መጽሐፍ ቅዱስን የግሪኩና የዕብራይስጡ ምን ይላል ብለዉ ይጠይቃሉ? ነገር ግን ሐሳብ ለሀሳብ የሚተረጉሙ ሰዎች የሚጠይቁት ጥያቄ ምን ማለት ነዉ? የሚል ነዉ። በእነዚህ ሁለቱ ጥያቄዎች መካከል ብዙ የጎላ ልዩነት የለም ብለህ ታስብ ይሆናል። ነገር ግን የተለያየ መልስ ይመልሳሉ። የሐሳብ ትርጉም ብዙ ጊዜ ችግሩ የኦሪጂናሉ መጽሐፍ የሚለዉን ቃል ሊስቱት ይችላሉ። ምንድን ነዉ የሚለዉ? እኔ የማስበዉ ስለዚህ ክፍል ምንድን ነዉ? ስለዚህ በኦሪጅናል መጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ የሌለዉን ወይም የማይለዉን ሐሳብ እና ቃላትን ይሰጣል። ‹‹ የሕያዉ መጽሐፍ ቅዱስ/ ሊቪንግ ባይብል ብዙ ስህተትና የማይለዉን የሚሉ ቃላቶች አሉበት።

ለምሳሌ በዮሐ1፡17 ላይ የአሜሪካዉ እትም ‹‹ሕግ ለሙሴ ተሰጥቶ ነበር ጸጋና እዉነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ተሰጠን›› የሕያዉ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ይላል ‹‹ሙሴ ሊለወጥ የማይችለዉን፣ ምህረት የሌለዉ፣ፍትህን የያዘ ሕግ ብቻ ሰጠን። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ፍቅርንና ሕይወትን ሰጠን›› በዚህ እትም ዉስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የማይለዉን ነገር ነዉ የሚለዉ›› ሙሴ ሕግ ብቻ አይደለም የሰጠን ኢየሱስ ሲናገር ‹‹ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአል›› የብሉይ ኪዳኑ ሕግ ምሕረት አልባ አይደለም፤ በብዙ ቦታ ስለ እግዚአብሔር ምህረት ይናገራል። ስለዚህ ሕያዉ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ የተናገረዉን ነገር አልጠቀሰም።

ሐሳብን መተርጎም ምናልባት ለማንበብና ለመረዳት ቀላል ነዉ። ነገር ግን ስለ ትክክለኛነቱ ብዙ ማረጋጫ አይሰጥም። እንዲህ አይነት ትርጉም ጠቃሚ ነዉ። ጥሩ ትርጉም መባል ይችላል።

ጥሩ ትርጉም ማለት ምን ማለት ነዉ?

ክርስቲያኖች ማድረግ ያለባቸዉ ነገር በትክክል መተርጎም አለመተረጎሙን በትክክል ማየትና ማረጋገጥ ነዉ። ብዙ አዳዲስ አማኞች የአሜሪካኑን እትም አንብበዉ መረዳት ይከብዳቸዋል። ከ17ኛዉ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አንዳንድ ቃላት ትርጉማቸዉን አጥተዋል። አንተ የምትጠቀመዉ

የትኛዉን እትም ነዉ? የትኛዉን ክፍል እንደተረዳህና የትኛዉን ክፍል እንዳልተረዳህ ማወቅ ትችላለህ ነገር ግን አዳዲስ ክርስቲያኖች የትኛዉ እትም ትክክለኛና የትኛዉ ዕትም እክል እንዳለበት አያዉቁም፤ ስለዚህም የሚመክሩና የሚመሩ ሰዎች ያስፈልጋቸዋል፤ በዚህ ጉዳይ መጋቢህን ማነጋገር ይገባሃል።

የትክክለኛነቱ ጉዳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎችን ባሕርይ የሚመለከት ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ መለኮት መሆኑን ያምናሉ ወይ? በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ እና ስልጣን ያምናሉን?

ይህ ቀላል ነጥብ አይደለም። ለምሳሌ የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉሙ ሰዎች በእግዚአብሔር ቁጣ አያምኑም፤ በዚህ አስተምህሮ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ የሆነ ነገር አለዉ፤ ነገር ግን እነዚህ ትርጓሜዎች አይቀበሉትም፤ በሮሜ 3:25 ላይ ማስተሰረያ የሚለዉን ቃል እየተነጋገሩበት ሲሆን የክፍሉ ሐሳብ እግዚአብሔር ልጁ በመስቀል ላይ የእኛ ምትክ ሆኖ ቁጣዉ እንደበረደ የሚናገር ነዉ። ክርስቶስ ምትካዊ ሞት በመሞት ሐጢአታችንን በመደምሰስ የእግዚአብሔርን ቁጣ መለሰ፤ የአር ኤስ ቪ እና የኤን ኢ ቢ እትም ክርስቶስ ሐጢአታችንን አስወገደ ብቻ ነዉ የሚለዉ፤ ኢየሱስ ሐጢአታችንን ቢያስወግድ ጳዉሎስ ያለዉ አስወገደ ብቻ አይደለም (ሮሜ3:25)፤ የቃላቱ ትርጉም የሚወሰነዉ በተርጓሚዎቹ የአስተምህሮ እምነት ላይ ተመርኩዞ ነዉ፤ ዶ/ር ሊዮድ ጆንስ እንዳሉት ‹‹ በሐዋርያቱ የተጠቀሱ ቃላት እንኳ አንድ ቃል በተለያየ ቦታ ሲጠቀስ የተለያየ ትርጉም ይሰጣል››።

የተለያዩ ዘመናዊ እትሞች ጥቂቶቹ ታማኝ በሆኑ ተርጓሚዎች እና በመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን የሚያምኑ ናቸዉ። ከእነዚህ ዉስጥ አዲሱ የአሜሪካ ስታንዳርድ እትም፣ የተሻሻለዉ እትም፣ አዲሱ የንጉስ ያዕቆብ እትም፣ አዲሱ አለም አቀፍ መደበኛ ትርጉም፤ አዲሱ መደበኛዉ ትርጉም በወንጌላዉያን አብያተክርስቲያናት በእንግሊዝኛዉ ትርጉም እጅግ በጣም ጥሩ የሚባሉት ነዉ። ለግል የጥሞና ጊዜ ሆነ ለማህበረ ምዕመናን ስብከት የሚሆን የሚወደድ ለማስታወስም የሚመች ነዉ።

አዳዲስ ክርስቲያኖች የአሜሪካኑን እትም ይወዱታል፤ ችግርም የለበትም ነገር ግን አዲሱ መደበኛ ትርጉም(ኤን አይ ቪ) እና የንጉስ ያእቆብን ትርጉም እንድትጠቀሙ አበረታታችኋለሁ፤

9

ለመጽሐፍ ቅዱስ ዋጋን መስጠት

በወንጌላዉን አብያተክርስቲያናት ዘንድ በተለምዶ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነዉ ስንል ምንም ስህተት የሌለበትና እስትንፋስ መለኮት ማለታችን ነዉ። ይህ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ይዟል ከማለት ያለፈ ትርጉም ያለዉ ነዉ። ለወንጌላዉያን መጽሐፍ ቅዱስ ልዩና የበላይ ባለስልጣን መሆኑን እናምናለን በእርሱ እንኖራለን፤ በዚህ ምዕራፍ ዉስጥ እስትንፋስ መለኮት እና ስህተት አልባ የሚለዉ ቃላት ትርጉማቸዉን ከማብራራት ሌላ የምጨምረዉ ነገር አይኖረኝም፤ እስትንፋስ መለኮት ማለት ስልሳ ስድስቱን መጽሐፍት የጻፉት ሰዎች የራሳቸዉን ሐሳብና አስተያየት አይደለም የጻፉት ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተዉ የጻፉት ነዉ። ‹‹ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።(2ጴጥ1፡21)፤ በኢ.ጄ አይ አገላለጽ ‹‹ሕፀፅ አልባ›› ማለት መጽሐፍ ቅዱስ ከስህተት ነጻ ማለት ነዉ፤ ከስህተት ነጻ ማለት ነዉ፤ አስተምህሮዉም ፍጹምና ከእዉነት ጋር የቆመ ነዉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ መለኮትና ከስህተት ነጻ ነዉ ሲባል ክርስቲያኖች የሚያምኑትና የሚኖሩት የበላይ ባለስልጣናቸዉ ነዉ ማለታችን ነዉ። የአማኞች ሐሳብ እግዚአብሔርን ማስደሰትና ለክብሩ መኖር ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል፤ ምክንያቱም በመጽሐፉ ዉስጥ ፈቃዱን ገልጾአል፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን የምንቀበል ከሆነ መጽሐፉ የሚለዉን ነገር ሁሉ መፈተን አለብን፤ ይህ ለክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ለማመንም ሆነ ለማወቅ አስፈላጊ ነዉ።

መጽሐፍ ቅዱስ የእኛ ባለስልጣን ካልሆነ ሌላ ነገር ባለስልጣናችን ነዉ ማለት ነዉ። የእኛ ሰዎች አመለካከት ነዉ፤ ምርጫዉ የእኛን የሰዎችን አመለካከት ወይም እግዚአብሔር ያለዉን መቀበል የእኛ ምርጫ ነዉ። የራሳችን ሐሳብ ለመምራት የእኛ የስልጣናችን መሰረት በምን መሰረት ላይ እንደተገነባ ማወቅ የግድ ነዉ።

በቅርብ አመታት ዉስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዙሪያ በወንጌላዉያን አማኞች መካከል ሁለት ሐሳቦች ብቅ ያሉ ሲሆን፤ አንደኛዉ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ልባችን እስትንፋስ መለኮት ነዉ

ብለን መቀበል የለብንም የሚል ሲሆን የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ዝቅ የሚያደርግ ነዉ። ሁለተኛዉ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ አስተምሮ መቀበል አለብን የሚሉ ሲሆን በአኗኗራቸዉ ግን የሚክዱ ናቸዉ። እነዚህ ሁለት ሀሳቦች ለብዙ ጊዜያት ሲሸከረከሩ የቆዩ ናቸዉ፤ (2ጢሞ 4፡3-4፣ቲቶ 1፡15-16) አሁን ላይ ደግሞ በስፋት እየተነገሩ የመጡ ናቸዉ።

ሥልጣን የለዉም

የመጨረሻ ስልጣን ከሌለዉ ፍጹም የሆነ መመዘኛ የለዉም እና ሁሉም ነገር አንጻራዊ ነዉ ወደ ሚል ሐሳብ ያመጣናል። ትክክልና ስህተት የሚባልም ነገር የለም፤ እንዴት ነዉ እያንዳንዱ ሰዉ ይህንን ነገር የሚመለከተዉ? ዓላማዉን ሰዎች የሞራል መመዘኛ የሆነ ነገር የለም ይላሉ እና በቤተክርስቲያን ደግሞ ፍጹም እዉነት የለም ይላሉ፤ ለምሳሌ በአንደኛዉ ክፍለ ዘመን የነበረች ቤተክርስቲያን በሲኦል መኖር ታምን ነበር፤ አሁን ይህንን የምታምን ከሆነ በአንዳንዶች ዘመን እንደ እንግዳ ፣ኋላቀር እና ፍቅር የጎደለዉ ሰዉ ተደርገህ ትታያለህ።

አለም ስለሞራል የምታስበዉና ቤተክርስቲያንም ስለ እዉነተኛ አስተምህሮ የምታስበዉ ተመሳሳይ ነዉ። ቤተክርስቲያን ለግብረ ሰዶማዉያን በቤተክርስቲያን ዉስጥ የጋብቻ ቃል ኪዳን ስርዓት መስጠት አለባት ወይስ የለባትም የሚል ክርክር ዉስጥ የገባችበት ነዉ። ይህ ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ መተዉ ብቻ ሳይሆን ሐጢአትን ማበረታታት ነዉ። እንዲህ አይነት ሐሳብ ሲነሳ ብዙ ጊዜ መዉደድ እንጂ መፍረድ የለብንም የሚል ነዉ። እንደዚህ ያለ ድምጾች ከፍ ብለዉ እየተወሩ ሲሆን ነገር ግን የመከራከሪያ ነጥባቸዉ ደካማ ነዉ፤ ለምሳሌ እንደ ኢየሱስ ያለ ፍቅርን የሚወድ የለም ነገር ግን እርሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ሲኮንን እናያለን፤ በእርሱ ዘመን የነበሩትን የሐይማኖት መሪዎች የእፉኝት ልጆች ሲላቸዉ እንመለከታለን፤(ማቴ 23፡33) እንዲህም ብሎአቸዉ ነበር እናንተ የዳቢሎስ ልጆች ናችሁ (ዮሐ 8፡44)።

ሰዎች ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚገባ ካለመረዳታቸዉ የተነሳ ስለ ፍቅር ያላቸዉ መረዳት የተዛባ ነዉ። እግዚአብሔር በቃሉ ዉስጥ በግልጽ እየተናገረ ፍቅር ማለት ሁሉም ሰዉ መንግስተ ሰማይ ይገባል ብሎ ሰዎችን ማሳሳት ማለት አይደለም፤ ይህ ደግሞ በሞራሉ አለምም ተመሳሳይ ነዉ፤ አንድ ሴት ልጅ ከአንድ ወጣት ጋር በፍቅር ከወደቁ በኋላ አብረዉ ተኙ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተጋብተዉ ሶስት ለጆችን ወለዱ፤ ሴቲቱ ክስተቱን ስትናገር ‹‹ ስህተት መሆኑን አዉቃለሁ ነገር ግን ምንም ማድረግ አልቻልኩም እወደዋለሁ›› ትላለች ይህ

እንግዲህ ስለ ፍቅር መናገሯ ነዉ። ስለ ፍቅር (1ቆሮ13) ምን ይላል? ፍቅር ራስ ወዳድ አይደለም በክፉ ስራ አይደሰትም፣ በግልጽ እንደሚናገረዉ በሁለቱ መካከል ዉስጥ ምንም ግንኙነት የለም። ከአንድ በኩል የሆነ ፍቅር ብቻዉን ጋብቻን ያፈርሳል፤ ደስተኛ ያልሆኑ ባለትዳሮች ሶስት ልጆችን ቢያፈሩም ፍቅር ይጠብቃል፣ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፤ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣን እያጣጣሉ የእግዚአብሔርን የሞራል ሕግን መጠበቅ አይቻልም። ዓለም ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንደ ኋላቀር ፋሽን እና እንደ መሐይም አድርጋ ልትቆጥር ችላለች፤ ምልክቱም የቤተሰብ መፍረስ(የፍቺ መበራከት) ኢሞራላዊ ሕይወትና ብልሹ ባሕርይ የሃያኛዉ ክፍለ ዘመን መገለጫዎች ናቸዉ።

ሐጢአትን መታገስ

የወንጌላዉያን ክርስቲያኖችም የዛሬ ሃያ አምስት አመት በፊት የምንቃወመዉ ነገር አሁን ግን በመላላት ላይ ይገኛሉ። ይህ ትዕግስት በቸርነት መንፈስ የሆነ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል የተጣበቀ ግንኙነት ካለመኖሩ የተነሳ የመጣ ዉጤት ነዉ። እግዚአብሔር ያወገዘዉን ነገር መታገስ ለአደጋ ይዳርጋል፤ ይህ መታገስ ጌታ ዳግም እስኪመለስ ደረስ በዚህ ባህርይ የሚቀጥል ነዉ። የቤተሰብ መፍረስ፣ ብዙ ወንጌላዉያን ቤተክርስቲያን በአመንዝራ ሕይወት ዉስጥ መሆናቸዉ ሲሆን ይህን ርኩሰትና ሐጢአት ልጆቻቸዉ በቴሌቪዥን እንዲያዩ መፍቀዳቸዉ ነዉ። ዝርዝር ሐሳቦቹ ሰፊና የሚያስፈራ ነዉ፤ ከዘመናት በፊት የወንጌላዉያን ቤተክርስቲያናት ባህርያቸዉ ባህላዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነበር፤ በአንዳንድ ጉዳዮችም ደግሞ ጠበብ ያለ ሐሳብ ነበራቸዉ። ዛሬ ግን ልጆቻቸዉን ወደ ባህር መወርወር ጀምረዋል፤ የፈሪሣዉያን ትምክህት እንደሌሎቹ አይነት ሰዎች አይደለም፤ ይህ የፈሪሣዉያን አይነት ባህርይ ዛሬ በብዙ ወንጌላዉያን ቤተክርስቲያን ዉስጥ ይታያል። ይህ አይነት ባህርይ ጌታ ኢየሱስን እወዳለሁ ለሚል ክርስቲያን ተገቢ አይደለም።

እዉነቱን ግን ስንመለከት መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ክርስቲያኖች ከሌሎቹ ሰዎች ልዩ እንደሆኑ ይናገራል። በእግዚአብሔር ፊት የጸደቁ እንጂ የሚፈረድባቸዉ አይደለም ዘላለማዊ ፍጻሜያቸዉ እንዲሁ ይለያል፤መንግስተ ሰማይ የሚገቡ እንጂ ወደ ሲኦል አይወርዱም፤ የሕይወት ዘይቤያቸዉ እንዲሁ ይለያል፤ ጳዉሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍላቸዉ ‹‹ *እንግዲህ አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ።››* ኤፌ *4:17* በዚህ ክፍል ጌታ ሕዝቡ ከሌሎቹ ሕዝቦች በተለየ

ሁኔታ እንዲኖሩ ይፈልጋል። ስለዚህ በዚህ ክፍል ዉስጥ በግልጽ ክርስቲያኖች እንዴት መኖር እንዳለባቸዉ ያብራራል። ‹‹ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ።›› 5፡8 በመቀጠልም በቁ 10 ላይ ሐዋርያዉ ለአማኞች ‹‹*ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ*›› ይላቸዋል። ለጌታ ደስ የሚያሰኘዉን የሚለዉ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ አንድ ጊዜ የተጻፈ ሲሆን እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስን የማናምን ከሆነ ለዉስጣችን ፍላጎት ተሰጥተናል ማለት ነዉ። ሀሳባችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቃኘ ሳይሆን በተለያየ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሚያጠነጥን ዜና መጽሔትና የመዝናኛ ቴሌቪዥን ላይ ነዉ። በክርስትና ሕይወት ለመኖር እንደ ክርስቲያን ማሰብ ያስፈልጋል። እንደ ክርስቲያን ለማሰብ ደግሞ ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በማንበብ ጊዜ መዉሰድ ያስፈልጋል። እኛ የምናምነዉን የምንኖረዉ ነዉ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉጭ ለዓለም የምንለዉ ምንም የሞራል ሕግና መልዕክት የለም። ኢሞራላዊ ተግባርና ንግግር እግዚአብሔርን ከማያዉቁ ሰዎች የሚመጣ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስን በምንም የሚተካ ነዉ። የወንጌል ስርጭት ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እየተናገረ ነገር ግን መሰረታዊ የሆኑ የአዲስ ኪዳን ትምህርቶችን የሚያስወግድ በተለይም ሐጢአትን በተመለከተ፣ በደልና ፍርድ፣የንስሀ አስፈላጊነት፣ሀጢአትን ሳያምኑ ንስሀ ትክክል መሆን አይችልም። ሀጢአትን እሰካልተጋፈጡ ድረስ ሀጢአትን ማመን አይቻልም።

ኤ ደብሊዉ ቶዘር ለምንድን ነዉ መጽሐፍ ቅዱስን የምናምነዉ? በሚል ርዕስ የተናገረዉን የመጨረሻ ሐሳብ እንመልት።

ባለፉት ጥቂት አመታት በወንጌላዉያን ቤተክርስቲያናት ዙሪያ የሚነሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ሐሳቦች እና ልምምዶች ብቅ እያሉ ነዉ። **ልዩ መንፈስን** እያስተዋወቁ ይገኛሉ። ይህ መንፈስ ግን ትክክለኛ የክርስቶስ መንፈስ አይደለም። ብዙ ዘዴ የሚሉት ነገር አለ ነገር ግን ስጋዊ ነዉ፣ ዓላማ ብለዉ የሚያቀርቡት መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፋቸዉ አይደለም።ባህርያቸዉ ከአለማዉያን ጋር ተመሳሳይ ነዉ። በዚህ ሁሉ ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያከብሩና የሚከተሉ ሰዎች በእነርሱ መካከል ሆነዉ ሲያለቅሱ እነርሱ ግን ይቃወሙአቸዋል። የእዉነተኛ አስተምህሮን የሚቀበሉ ሰዎች አሁን አሁን አቋማቸዉን በመቀየር ላይ ናቸዉ። እነዚህ ክፉ የሆኑ ልማዶች በፍጥነት ካልተቀየሩ የአባቶቻችን እምነት መሆኑ ይቀርና የጋራ ሐይማኖት

ወደ መሆን ይሄዳል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለዉ ቃል ብቻ ይቀራል እዉነተኛ የሆነዉ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና እዉነተኛ አስተምህሮ ከየቤቱ ሊጠፋ ይችላል።

10

መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም

በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ረዥሙ ምዕራፍ መዝ 119 ሲሆን አወቃቀሩም በጣም ማራኪ ነዉ። 22 ክፍሎች ዉስጥ ሰምንት ቁጥሮችን የያዘ ሲሆን በእያንዳንዱ ክፍል ርዕስ ላይ የዕብራይስጥን ፊደል የያዘ ነዉ። የመዝሙሩ ሐሳብም ለእግዚአብሔር ቃል ያለዉን ፍቅር የሚገልጽ ነዉ። 176 ቁጥሮች የሚናገሩት የእግዚአብሔርን ቃል በተለያየ ቃላት፣መንገድ፣አዋጅ፣ትዕዛዝና ተምሳሌት ነዉ።

105 ቁጥሮች ሲጨመቅ በክርስቲያን ሕይወት ዉስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ስፍራ እንዳለዉ የሚያመለክት ነዉ። ‹‹ሕግህ ለእገሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነዉ›› የምንኖርበት ዓለም በመንፈሳዊም በሞራልም የወደቀና ጨለማ የሆነ ነዉ።ፍጹም የሆነ መመዘኛም የለም ምክንያቱም የሞራል ባሕርይ ከአንዱ ትዉልድ ወደ ሌለኛዉ ትዉልድ ሲተላለፍ ይቀያየራል። እንዴት ነዉ ክርስቲያን የሚኖረዉ? በምትቀያየረዉና በምትበሰብሰዉ አለም መመዘኛ የተያዘ ነዉ ወይስ ፍጹም የማይቀያየርና ስልጣናዊ የሆነ መመዘኛ አለን? መዝ 119 እንደሚናገረዉ የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ሆኖ የሚያበራ ለሚያዩ ሰዎች ግልጽ ሆኖ የሚያሳይ ነዉ።

የእግዚአብሔር ቃል ምንድን ነዉ?

መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ መጽሐፍ ነዉ። 40 የሚሆኑ ጸሐፊዎች ከ1500 አመታት በላይ ወስዶባቸዉ 66ቱን መጽሐፍ መጻፋቸዉ ድንቅ መጽሐፍ ነዉ። መጸሐፍ ቅዱስ ልዩ መጽሐፍ መሆኑን ልናደንቅ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ የቆየ የተረት መጽሐፍ ቢሆን ኖሮ ስለስልጣኑ ብዙ እዉቀት ባልኖረን ነበር።መጽሐፍ ቅዱስ ግን ብዙ የሚናገረዉ ነገር አለ። መልእክቱም ለድነት አስፈላጊ ነዉ። ‹‹እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው›› *ሮሜ10፡17*። ለመንፈሳዊ እድገት አስፈላጊ ነዉ። ‹‹አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ›› 1ጴጥ 2፡2። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነዉ ስንል እግዚአብሔር ራሱ የጻፈዉ ነዉ ማለት አይደለም። እርሱ የመጀመሪያዉ ባለስልጣን

ቢሆንም ጸሐፊዎቹ ግን ሰዎች ናቸዉ። ይህ ማለት ግን የራሳቸዉን ሀሳብ ጻፉ ማለት አይደለም። ‹‹ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ጻሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ›› (2ጴጥ 1፡20-21)□□

ጸሐፊዎቹ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተዉ ጻፉት ይህ ማለት እግዚአብሔር ቃል በቃል አጽፎአቸዋል ማለት አይደለም። ሙሴ እና ጳዉሎስ እንደ ጸሐፊ ሁሉንም ነገር ጌታ ቃል በቃል አጽፎአቸዋል ማለት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ተነድተዉ ጻፉ፤ በታማኝነት ሐሳቡን ገለጹ ማለት ነዉ (1ቆሮ2፡13)። ስለዚህ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ያምኑታል ይደገፉታል፤(1ቆሮ2፡13)፤ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሻር እንደማይችል ተናገረ (ዮሐ10፡35)፤ ይህንንም እርሱ ራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጠቀመ አረጋገጠ፤ ሰይጣንን ለመቃወም ቃሉን ተጠቀመ፤(ማቴ4፡11) ነፍስ እንደምትፈልግ (ማቴ 19፡16-22) ለጠላቶቹ መልስ ለመስጠት (ማቴ 15፡1-9) የመስቀሉን ትርጉም ለማብራራት (ዮሐ3፡14)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ እግዚአብሔርን ለእኛ ለመግለጽ ነዉ፤ ሁለት አይነት መገለጦች አሉ፤ የመጀመሪያዉ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ራሱን መግለጡ ነዉ በመዝ 19፡1 ላይ ‹‹ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።›› ይህ መገለጥ አጠቃላይ መገለጥ ይባላል። ምክንያቱም ሁሉም ሰዉ ሊያየዉ የሚችል ስለሆነ ነዉ፤(ሮሜ1፡18-20)፤ ሀጢአት የሰዉን አእምሮ ስላሳወረ ይህ መገለጥ ወደ ድነት አያመጣም፤ ስለዚህ ልዩ መገለጥ ያስፈልጋል የፍጥረትን ዉበት ለማሳየት ብቻ ሳይሆን በሀጢአት የተበላሸዉን የሰዉን ተፈጥሮ ማሳየት ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ በኩል ስለተገለጠ ይህ ልዩ መገለጥ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ።

እንዴት ነዉ መጽሐፍ ቅዱስን የምንጠቀመዉ?

መጽሐፍ ቅዱስን እስካልወደድነዉ ድረስ በትክክል ላንጠቀመዉ እንችላለን፤ መዝሙረኛዉ ለእኛ ጥሩ ምሳሌን አስቀምጦአል ይህም ‹‹አቤቱ፥ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።›› (መዝ 119፡97)፤ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነዉ ብለን የምናምን ከሆነ ልንወደዉና ገንዘባችን ልናደርገዉ ይገባል፤ ፍቅር ከማድነቅና ከማክበር የሚበልጥ ነዉ፤ ዊሊሃም ቲንዳሌ ለምን ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ? የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስላለን ነዉ? መጽሐፉን ስላደነቀ ሳይሆን ስለወደደዉ ነዉ።

ፍቅር መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደምንጠቀምበት ይወስናል። መዝሙረኛው እንዳለው ‹‹አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ›› ይላል የሚቀጥለው አረፍተ ነገር ‹‹ቀኑን ሁሉ እርሱ ተዝታዬ ነው›› ከብዙ አመታት በፊት ስፔን በምትገኘው ቤተክርስቲያን ስሰብክ ሳለሁ ሁለት ወንዶች ወጣቶች ወደ እኔ መጡ አንደኛው በስፔን ባለችው ቤተክርሰቲያን ውስጥ ካለች አንዲት ሴት ፍቅር ይዞት ነበር ፍቅራቸው የታወቀ ነበር። ነገር ግን የመግባቢያ ቋንቋ ችግር ሆኖባቸው ነበር ምክንያቱም እርሱ የስፓኒሽ ቋንቋ አይችልም ነበር። እርስዋ ደግሞ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር አትችልም። ከዚያ ወዲያው ወደ እንግሊዝ ተመለስን። ይህ ወጣት ግን በማታው ክፍለ ጊዜ የስፓኒሽ ቋንቋ ለመማር ወሰኖ መማር ጀመረ። በፊት ስፓኒሽ ለመማር ፈቃደኛ አልነበረም ነገር ግን አሁን እርስዋን ስለወደደ ነው ይህን የሚያደርገው። ፍቅሩን በስፓኒሽ ቋንቋ ለመግለጽ ስለፈለገ እና እርስዋ እንድትረዳው በማሰብ ነው ይህን ያደረገው። ፍቅር ሁልጊዜ የመነሳሳት ሐይል ነው። ተግባሩም ሸክም ሳይሆን ደስታ ነው።የእግዚአብሔርን ቃል የምንወድ ከሆነ ቃሉን ማንበብና ማሰላሰል ይኖርብናል። ይህ መሆን ያለበት አልፎ አልፎ ሳይሆን ቀንና ማታ ነው (መዝ 1፡1-2)።

በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም አስፈላጊ ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ምግብ ነው መንፈሳዊ ዕድገትን ያመጣል ስለዚህም በየቀኑ መመገብ ያስፈልጋል። ለመንፈሳዊ እድገት እንቅፋት የሚባለው በሀጢአት ውስጥ መኖር ሲሆን ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ›› (መዝ119፡11)። የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰላሰል እና በልብ ውስጥ ለመሰወር ጊዜና ስራ ይፈልጋል።ቃሉን ለማንበብና ለማሰላሰል በችኮላ ሳይሆን በርጋታ መሆን አለበት። በችኮላና በፍጥነት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጥቅም የለውም።

እውነተኛ ክርስቲያን ሁልጊዜ በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ይገባል። በርግጥ ሁልጊዜ መንፈስ ዝግጁ ሲሆን ሥጋ ግን ደካማ ነው። ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳችንን ማንበብ እንዳለብንና ወደ ድሮው ዘመን ዓይነት መትጋት እንዳለብን አይተናል ይህን ስናደርግ በአጭር ሳምንታት ውስጥ ማሳካት ይቻላል። ይህን እንዴት ማድረግ ይቻላል? የእግዚአብሔርን ቃል በመውደድ፣ ይህን ስታደርግ ግማሽ መንገድ ተጉዘሃል ማለት ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠና ሁለት ነገሮችን መፈጸም ይኖርብሃል ይኸውም ማንበብና ማጥናት ነው።

ማንበብ

ይህ በየቀኑ የሚሆን ስልታዊ መሆን አለበት። በምታነብበት ጊዜ በቸልታ ድንገት አንድ ስፍራ ላይ ከፍተህ ወይም የምትወደዉን ስፍራ መርጠህ መሆን የለበትም። የምትወደዉን ብቻ መርጠህ የምታነብ ከሆነ አብዛኛዉ መጽሐፍ ቅዱስ ስለማታነበዉ እንግዳ ይሆንብሃል። ይህን አይነት ዘዴ ለማስወገድ ብዙዎቻችን ስልታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መከተል ያስፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ አመት ዉስጥ አንብቦ ለመጨረስ ብዙ አይነት ስልት መጠቀም አለብን። ብዙ የሆነ ፍላጎት አይኑርህ፣ የምታጠናበትን ስልት ምረጥ፣ ለአንተ አመቺ የሆነዉን ስልት ምረጥ ይህን የማታደርግ ከሆነ እያጠናህ ሳይሆን እያነበብህ እና ተሰላችተህ ሁሉ ልታቆመዉ ትችላለህ። ከመረጥከዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጋር ተጣበቅ በየቀኑ አንድ ምዕራፍ መርጠህ ማንበብ ጀምር በጣም ከሰፋብህ ቀነስ ቀነስ አድርገህ አእምሮህ እንደቻለ መጠን አጥና ከዚያ ጥቅምን ታገኛለህ።

መጋቢዎቻችሁንና ከእናንተ ቀደም ያሉትን ሰዎች ስለ አጠናን ዘዴ ጠይቁአቸዉ። ስልት በጣም አስፈላጊ ነዉ። የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናት ስትጀምርና ለጊዜዉ ባይሳካልህ ብዙ አትጨነቅ ምክንያቱም ዳቢሎስ ስለሚመለከተዉና ስለሚዋጋ ነዉ።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት የሚመችህ ጊዜ መቼ ነዉ? ለዚህ ጥያቄ ተመሳሳይ መልስ ላይኖር ይቻላል። ምክንያቱም የተለያየ ጊዜ ሊኖረን ስለሚችል ነዉ። ለአንዳንዶቹ ቀን ሲመቻቸዉ ለሌሎቹ ደግሞ ሌሊት ይመቻቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ ለማንበብ አመቺ የሆነ ጊዜ ፈልገህ መምረጥ አለብህ። ቆንጆ የሆነ ጊዜ ስትመርጥ ከሃላፊነትህ ጋር ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ጡረታ የወጣ ሰዉ ከልጆቹ ጋር ብዙ ጊዜ ይኖረዋል። ምን ሰዓት ይመችሃል ከዚያ ሰዓት ጋር ተጣበቅ ራስህንም ስጥ። በክርስትና ሕይወት ራስህን የማታስገዛ ከሆነ ፍሬያማ ልትሆን አትችለም።

ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠና ከጸሎት ጋር የሚገናኝ ነዉ። ይህ ሲሆን ሕይወታችን ይመገባል ከዚያም ወደሌላዉ ይተርፋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ይህ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ የሚለይ ሲሆን ብዙ ጊዜን የሚጠይቅ ነዉ። ይህ በሳምንት አንዴ ወይም ሁለቱ ሊሆን ይችላል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከማንበብ ይልቅ ብዙ ነጥቦችን እንድንይዝ የሚያደርግ ነዉ፤ ስለዚህ ጥሩ የማብራሪያ መጽሐፍ፣ የጥቅስ ማዉጫና አትላስ (ስእላዊ መግለጫ የሚሰጥ መጽሐፍ) ያስፈልግሃል፤ እነዚህን እንዴት መጠቀም እንዳለብን መደበኛ የሆነ መሣሪያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። ገቢያ ላይ ያሉትን መጽሐፍቶች ከመግዛትህ በፊት መጋቢህን አማክር ይህን በማድረግ ገንዘብህን ከማባከን ታድናለህ።

ጥቂት ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ጊዜ የላቸዉም፤ ይህ የሚሆነዉ አሁንም እንደምለዉ ለመጽሐፍ ቅዱስ ፍቅር ስለሌላቸዉ ነዉ፤ ቴሌቪዥን ለማየት ጊዜ እንደሚኖርህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስንም ለማጥናት ጊዜ ሊኖርህ ይገባል፤ በእሁድ ቀን የጥሞና ጊዜ ለማድረግ እንዲሁ ጊዜ ሊኖረን ይገባል።

መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ከባድ የሆነ ሥራ ነዉ፤ ነገር ግን በየቀኑ መደሰት ይገባል፤ እንደምናዉቀዉ ቃሉ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሃን ነዉ፤ ስናጠናዉ መንፈሳዊ ሕይወታችን ይበለጽጋል ቤተክርስቲያን ትጠነክራለች።

11

ትክክለኛ እና ስህተት

ሁሉም ሰዎች ሊያዉቁት የሚገባዉ ነገር ስህተትና ትክክለኛ ነገር ስለመኖሩ ነዉ፤ ማህበረሰብም በደንብ የተጣበቁበት ነገር ባይኖርም የራሱ የሆነ የሚረዳዉ መስፈርት ይኖረዋል፤ ዛሬ ያ ሁሉ ነገር ተቀይሯል፤ የሰዎች ሞራል ሞቷል፣ አሁን አለም የምትኖረዉ በፈላስፎች መርህ ነዉ፤ ይህ የፈላስፎች ፍልስፍና የሚሞት ነዉ፤ ስለዚህም ትክክልና ትክክል ያልሆነ ነገር የለም ምክንያቱም ፍጹም የሆነ ነገር የለም ይላሉ፤ ከሰላሳ አመታት በፊት የተወገዙ ሀጢአቶች እንደ ግብረሰዶም፣ዝሙት፣በአደባባይ በራቁት መሄድ፣ የሚያስጠላ ንግግር፣ አሁን ግን ተቀባይነትን አግኝቷል፤ አሁን ወደ ቀደመዉ ነገር ለመመለስ በሞራላችን ላይ ማሻሻልና ያለማመቻመች መስራት ይጠበቅብናል።

ለዉጡ ለምን መጣ? በምድር ላይ የፍቅርንና የጨዋነትን መንፈስ ለማሳደግ ነዉን? አይደለም፤ ለዉጥ የሚያስልገዉ እግዚአብሔርንና የክርስቲያን እምነትን ስለተዉ ነዉ፤ ይህ የፍቅር

መግለጫ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ የሚለዉን ነገር ካለማድረግ የመጣ ነዉ። ለብዙ አመታት አዲስ ኪዳን ከሚያስተምረዉ የሞራል ሕግ በላይ ያለ ክርስቶስ የሞራልን ሕግ እንጠብቃለን የሚሉ ሰዎች ነበሩ። ሰዎች እንዲህ ይሉ ነበር እና የሚያስፈልገን የተራራዉ ስብከት ብቻ ነዉ በማለት የክርስትናን አስተምህሮ ሲከፋፍሉ ነበር። አሁን ግን ስናየዉ የተራራዉ ስብከት ብቻዉን ትንሽና ዉስንነት ያለዉ ነዉ።

ይህ ሁሉ አስተሳሰብ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነዉ። እንዲህ ባለ ሁኔታ ዉስጥ እንዴት ነዉ ክርስቲያን መኖር ያለበት? የእግዚአብሔርን ፍጹም የሆነዉን ሕግ በመቀበል ነዉ። ለምሳሌ ጌታ በአስርቱ ሕግጋት ዉስጥ የተናገረዉ ነገር ምንድን ነዉ? ከብዙ ሺህ አመታት በፊት የተነገረዉ ቃል ዛሬም እዉነተኛ ነዉ።ዛሬም ዝሙት ትክክል አይደለም። የሞራል ሕጎች መታየት ያለባቸዉ በማህበረሰቡ ሐሳብ ሳይሆን ፍጹም ሕግ በሆነዉ በመጽሐፍ ቅዱስ ነዉ። አለም ይህንን ላትቀበል ትችላለች ክርስቲያን ግን የግድ መቀበል አለበት። ሕጋችን የእግዚአብሔር ሕግ ነዉ አለበለዚያ ግን የክርስቲያን እምነት ምንም ሐይል የሌለዉ ይሆናል። የክርስቲያን እምነት ክርስትናን የማይተገብረዉ ከሆነ ግብዝ ይባላል።

ሕሊና

ሕሊና መልካሙንና ክፉን ለመለየት የሚያስችለን ከጌታ የተሰጠን ነገር ነዉ። ይህንን ጳዉሎስ ሲከራከር ባመኑና ባላመኑ መካከል በእኩል የሚሰራ ነዉ (ሮሜ 2፡15)። ሰዎችን ከእንስሳ የሚለያቸዉ ነገር ነዉ።አእምሮ፣ፈቃድና ሕሊና አላቸዉ። ሕሊና ከአእምሮ ጋር የተያያዘ ሲሆን ሕመም ግን ከሰዉነት ጋር ይያያዛል። ስህተት ስንሰራ የሚወቅሰንና የሚያስጠነቅቀን ነዉ። ሕሊና ሊሳሳት ይችላል እንከን አልባ አይደለም ለዚህም ሕግ ሊኖረዉ ይገባል ዮሐንስ ማክ አርተር እንደሚሉት ‹‹ሥራዉ እኛን ሞራል ወይም ሥነ ምግባር ማስተማር ሳይሆን ታላቅ መስፈርት ላለዉ ሕግ መልካምም ይሁን ስህተት ተጠያቂ ማድረግ ነዉ›› የአለማችን ትልቁ ችግር በዚህ 21ኛዉ ክፍለ ዘመን እግዚአብሔርንና የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን አለማመንዋ ነዉ። ስህተትና ትክክል ብላ የምትበይነዉንም ከላይ ባለዉ ሕግ አንጻር አይደለም። ይህ ደግሞ በማህበረሰባችን ዉስጥ ከሰላሳ አመታት በፊት የሞራል ዉድቀትን (ርኩሰትን) በቴሌቪዥን መመልከት ተቀባይነት አልነበረዉም ሕሊናን ያደማሉ።

ሕሊና በግል ላደረግነዉ በደል የሚያነቃን ነዉ። ነገር ግን ዛሬ በደል የሚባለዉን ነገር አስወግደናል። ይህ ዛሬ ማህበረሰቡን ወደ ወንጀል መበራከት መርቶታል። በኒዉዮርክ ከተማ

አዛዉንቶች ይደበደባሉ፤በርናንድ ዊከሚንግ የተባለ ሰዉ ወንጀል ፈጽሞ ሲሮጥ በጥይት ተመታ በኋላም ሽባ ሆኖ ሳለ የኒዎርክ የሽግግር ባለስልጣን 4.8 ዶላር ቢሰጠዉም ግለሰቡ ግን የካንሰር ሕመምተኛ ስለነበር ገንዘቡን መድሀኒት በመግዛት ጨረሰዉ፤ ዘራፊዉና ወንበዴዉ ማክሚንግ ፍርድ ቤቱ የተጎዳ ሰዉ ነዉ ብሎ ፈረደለት አሁን ይህ ሰዉ ሚሊየነር ነዉ፤

ዛሬ ማህበረሰቡ በሚሰራዉ ስራ ሰህተት ነዉ ብሎ ሕሊናዉ ቢነግረዉም የሕሊናን ድምጽ አይሰሙም፡፡ አዲስ ክርስቲያን ብትሆንም ከዚያ አይነት አሰራርና አካሄድ ነጻ ወጥተሃል፤ አዲሱ ሕይወት መቃወምና እንዲህ አይነት ሐጢአቶችን ማስወገድ ብሎም ተጽዕኖ መፍጠር አለበት፡፡

አዲሱ ሕግ

የክርስቲያን ድንጋጌ በማይለወጠዉ በእግዚአብሔር ላይ የቆመ ሊሆን ይገባል፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ስንገዛ እንቀደሳለን በቅድስናም እናድጋለን፤ የቅድስና አላማ ክርስቶስን እንድንመስለዉ የሚያደርግ ነዉ፤ይህ የእግዚአብሔር ሐሳብ ስለሆነ አማኞችም የየእለት እለት ፍላጎቶች መሆን አለበት፡፡ ይህ ቀላል አይደለም የእኛ ሕግ ከክርስቶስ ጋር ተመሳሳይ አይደለም ይህ ሊሆንም አይችልም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ አስተሳሰብ እንዲኖረን መማር አለብን፤ ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ክፍት ስንሆን ቃሉ በዉስጣችን ገብቶ ይቆጣጠረናል፤ ፍላጎታችንን ሁሉ ይገዛናልም፤ በዚህ ጊዜ ሕሊናችን ከላይኛዉ ሐይል ጋር መተባበር እንዳለበት ያዉቃል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ መስፈርታችን ሲሆን ለእግዚአብሔር ቦታ ይኖረናል፤ ሀጢአትንም እንጸየፋለን፤ በዚህ ጊዜ ድካማችንን እንረዳለን፤እግዚአብሔር የሚጸየፈዉን ነገር አንታገስም፤ በክርስቲያን ሕይወት አደገኛዉ ነገር ሀጢአትን እንደ ጤነኛ ነገር አድርጎ መቀበል ነዉ፤ሐጢአትን የምንተወዉ ከሆነ የቅድስና አስተምህሮ ተስፋ ያስቆርጣል፤ በሮሜ 6 ላይ ለሀጢአት እንደሞትን ይናገራል በስጋችን ላይ እንዲነግስ መፍቀድ የለብንም፤ ሀጢአት የእኛ ንጉስ አይደለም፤ሀጢአት በክርስቲያን ላይ የሚሰራዉ አማኞች ከሀጢአት ጋር የተባበሩ ጊዜ ነዉ፡፡

ከሀጢአት ጋር መተባበርን ስናቆም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚል ሀጢአትን እንገድለዋለን፤ ይህ ለሁሉም ክርስቲያን ግዴታ ነዉ፤(ሮሜ8፡12-13)፡፡

ሐጢአት የሚሞተዉ ራሳችንን ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ስናስገዛ ነዉ። ይህ የሚሆነዉ በእኛ ሐይል ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ነዉ። መንፈስ ቅዱስ ሐጢአትን እንድንገድለዉ ሐይል ይሰጠናል። ዮሐንስ ማካርተር እንደሚለዉ ‹‹ ሀጢአትን የመግደል ስራ የምንሰራበት ሐይል በዉስጣችን ያለዉ መንፈስ ቅዱስ ስራ ነዉ። የምንገድልበትን መንገድ ያሳየን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ታዘዙ ብሎ ስለነገረን ነዉ›› ማካርተር በመቀጠልም ዝርዝር ትዕዛዛትን አስቀምጦልናል።

ከስጋዊ ፍላጎት መታቀብ(የሐጢአት ፈላጎት)	1ጴጥ 2፡11
ለሀጢአተኛዉ ተፈጥሮ ምንም አቅርቦት ያለማድረግ	ሮሜ 13፡14
ልባችንን በክርስቶስ ላይ ማድረግ	1ዮሐ 3፡2-3
የእግዚአብሔርን ቃል ማሰላሰል	መዝ 119፡11 ኢያ 1፡8
ሳያቋርጡ መጸለይ	ሉቃ 22፡40 ማቴ 26፡41
መጠበቅና መጸለይ	መዝ 19፡12-14
ራስን መግዛትን መለማመድ	1ቆሮ 9፡25-27
በመንፈስ ቅዱስ መሞላት	ኤፌ 5፡18

12

ጥርጣሬዎች

ጥርጣሬ ማለት በልብ፣በአእምሮና በሕሊና ዉስጥ የሚዘራዉ የዳቢሎስ ዘር ነዉ። ክርስቲያንን ከድነት ወደ ኋላ የሚጎትት ነዉ። ክርስቲያን ይህን ሊቋቋም አይችልም። ለድነትህ ፍጹም ርግጠኛ ከሆንክ እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ አለብህ።

ምሁር ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ችግር የለባቸዉም፣ እንዲህም ይላሉ ‹‹አምነን ከወሰን ጀምሮ ምንም ችግር የለብንም›› እንዲህ ዓይነት ንግግር ብዙ ጊዜ ችግር ያለበት ሲሆን እዉነትና ጥሩ ስለሚመስል ጥርጣሬን ይጭራል ›› (ዲ ኤም ሊዮድ ጆንስ)

የታላላቅ የእግዚአብሔርን ሰዎችን የሕይወት ታሪክ ስናነብ በሕይወታቸዉ ትንሽ ጥርጣሬዎች አለ፤ ወጣቱ ቻርልስ ስፐርጆን ይህን የሕይወቱን ተሞክሮ ያካፍለናል እርሱን የ19ኛ ክፍለ ዘመን ታላቅ የሆነ ሰባኪ ነበር፤ እንዲህ ይላል፡-

‹‹አስታዉሳለሁ ጌታን በተቀበልኩ ቀናት ወደ አእምሮዬ የመጡ ብዙ ክፉ ሐሳቦች ነበሩ፤ እጅን በአፌ ላይ በመጫን ብዙ ፈርቼ ነበር፤ ይህ ደግሞ አንዱ የሰይጣን ስራ ነዉ፤ እግዚአብሔር ነጻ ያወጣዉን ሕዝብ እንደገና በፍርሃት ገመድ ማሰር ይፈልጋል፤ብዙ የተመረጡ ቅዱሳን በዚህ ተፈትነዋል፤በአንደ ወቅት በጣም ተፈትኛለሁ ከዚያም የተወደደዉን አያቴን ለመጠየቅ ሄድሁ፣ስለገጠመኝ ችግር አጫወትኩት እንዲህ አልኩት‹‹ አያቴ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለሁም ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት ክፉ ሐሳቦኝ ገጥሞኝ አያዉቅም፤ አያቱም ለቻርልስ እንዲህ ሲሉ መለሱለት ‹‹ አትጨነቅ አንተ ክርስቲያን ስለሆንክ ነዉ፤ ይህ ፈተና የገጠመህ እነዚህ ችግሮች ሁሉ የደረሰብህ ከአንተ ልጆች ሳይሆን ከዳቢሎስ የመጣ ነዉ እርሱ ልብህን በየቀኑ ያንኳኳል፤ ነገር ግን አንተ ለእርሱ ድምጽ በርህን ዝጋ ልብህንም አትክፈት›› (ሲ ኤች ስፐርጆን)

ጥርጣሬና ሐጢአት

በሐሳብህ ሐጢአት ስትሰራ ጥርጣሬ በቃልና በተግባር ወደ ልብህ ይገባል፤ ዳቢሎስ እንዲህ እያለ ይከሳል ‹‹ እንዲህ ያለ ክፉ ሐሳብና ባህርይ እያለህ ክርስቲያን መሆን አትችልም›› በደለኝነትና ሐጢአተኝነት ሲሰማህ እርሱን ለማመን በር ይከፍታል፤ ለሰይጣን ማታለል አትፍቀዱለት፤ በደለኝነትና ሐዘን ከተሰማህ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆንህ ማረጋገጫ ነዉ፤ ከማመንህ በፊት እንዲህ ያለ ስሜት አልነበረህም፤ አሁን ክርስቲያን ስለሆንክ ነዉ እነዚህ ነገሮች የገጠመህ፤

ሐጢአት በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት የለዉም ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን ይቅርታ አለ፤ 1ዮሐ1፡7-10 አንብብ፡፡ ይህ ቃል የተጻፈዉ ለክርስቲያን ነዉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከሐጢአት ፍጹም ናችሁ አይልም ነገር ግን ሐጢአት ስትሰሩ ድነታችሁን አትጠራጠሩ ሐጢአታችሁን

ተናዘዙ ይላል (1ዮሐ2፡1) አስታውሱ፡፡ ሐጢአት ስንሰራ ስለ እኛ የሚናገር ጠበቃ አለ ይህ ማለት እኛን ወክሎ ለእግዚአብሔር የሚናገር ማለት ነዉ፡፡

ጥርጣሬና መከራ

ጥርጣሬ የሚመጣዉ መከራና ሐዘን ሲመጣ ነዉ፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለመሆኑ የምትጠራጠር ከሆነ ለራስህ ጌታን ይቅርታ ጠይቅ በዚህ ጊዜ የኤሊያስን ሕይወት ማስታወሱ ጥሩ ነዉ፤ *ልባቸው ለቀና ለእስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነዉ! እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ፥ አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና ለሞታቸው መጣጣር የለውምና፤ ኃይላቸውም ጠንካራ ነውና (መዝ 73ን ያንብቡ፤)፡፡*

ጥርጣሬና እምነት

ጥርጣሬን ማንም አይፈልገዉም ጥሩም አይደለም፤እንደዚህ ማሰብ የለባችሁም ምክንያቱም ጥርጣሬ ካለብህ እዉነተኛ እምነት የለህም ማለት ነዉ፡፡

ብዙ ጥርጣሬዎች ሲኖሩ እዉነተኛ እምነት ይኖራል፡፡ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ በተደጋጋሚ የተናገረዉ ነዉ‹‹ ለምን ትፈራላችሁ እምነት የላችሁምን?›› (ማቴ 6፡30፣ 14፡31፣16፡8፣ ሉቃ 12፡28) ጥርጣሬ በልባቸዉ ቢገባም እዉነተኛ አማኞች ነበሩ፤ በእነዚሁ ሰዎች ዉስጥ ሁለት ነገሮች በቀጣይነት አብረዉ ይኖራሉ እነዚህም እምነትና ጥርጣሬ ናቸዉ፡፡

ጥርጣሬ ሲመጣ ወዲያዉ ምንጩን መመርመር ይገባል፡፡ እነዚህ የሚመጡት ከዳቢሎስ ስለሆነ የስፕርጀን አያት ያሉትን ማስታወስ ጥሩ ነዉ ‹‹ የራስህ አታድርጋቸዉ ምንም አይነት በር አትክፈትላቸዉ››

ሰይጣን ተስፋ በማስቆረጥ ሲከሰኝ

በደሌን ሲያሳየኝ

ወደ ላይ ጌታን አየዋለሁ

ሐጢአቴን ያስወግድልኛል

(ቻሪቲ ሌስ ዴ ቸንዝ)

13

ዋስትና

ለጥርጣሬ ጥሩ የሆነዉ መልስ ጠንካራ የድነት ዋስትና አለ።

‹‹ሰይጣን የክርስቲያን ጠላት ስለሆነ የክርስቲያኖችን ደስታና ምቾትን መንጠቅ ይፈልጋል። ሕይወትንም በጨለማና በጥርጣሬ መመላት ይፈልጋል። ዋስትና ክርስቲያንን ጠንካራ እንደሚያደርግ ዳቢሎስ ያዉቃል። ይህ የጨለማዉ መሪ ዳቢሎስ አዳምን ከገነት እንዳስወጣዉ ሁሉ ዛሬም ዋስትናን ለማሳጣት ይታገላል።›› (ቶማስ ብሩክስ)

እግዚአብሔር ሕዝቡ ዋስትና እንዲሰማዉ ይፈልጋል (ዕብ 10፡22)። ዋስትና ማለት ለጥቂት ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ወይም ግምት አይደለም። ሮሜ 8ን በደንብ አንብቡ። ሲጀምርም በቁ.1 ላይ ‹‹ኩነኔ የለባቸዉም›› ብሎ ነዉ ሲጨርስም ‹‹ማን ይለየናል››(ቁ.39) በሚል ነዉ። ማን ናቸዉ ኩነኔ የሌለባቸዉ? እነዚህ በክርስቶስ ያሉ ናቸዉ። ይህ ማለት ሁሉም ክርስቲያኖች ናቸዉ ሁሉም ክርስቲያኖች እንደ ሐዋርያዉ ጳዉሎስ እና እንዳንተና እንደኔ ያለ ሰዉ የለም። ከማን ነዉ የማንለየዉ? የጻፈዉ ጳዉሎስ ነዉ የጻፈዉ ‹‹ እኔ አምኛለሁ››(ቁ.38) ወይም ‹‹ አምኛለሁ›› ከእግዚአብሔር ፍቅር ማን ይለየናል? ይህ ቃል ሁሉንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለሚያጠቃልል እግዚአብሔርን እናመሰግናለን።

ስለዚህ ዋስትና ለሁላችንም ነዉ።አለዚያ ግን ጥርጣሬ በሚባል ቸነፈር እንመታለን በዚህም ምክንያት አይናፋርና ደካማ ክርስቲያን ሆነህ ለዘላለም ትኖራለህ። ክርስቲያን ከሆንክ እንዲህ አይነት ዋስትና አልተሰጠህም። ልብን በወንጌል ሙላ በዋስትና ዉስጥ ትልቅ ደስታ አለ። በሮሜ 8፡35-36 ዉስጥ ያሉ ችግሮች ዓላማ እንዲኖረን የሚያደርግና በክርስትና እንድንጸና የሚያደርግ ነዉ።

ዋስትና ከእምነት ዉስጥ የሚወጣ የሚያድግና የሚያፈራ ፍሬ ነዉ (እስጢፋኖስ ቻርኖክ)

ዋስትና በከፊል የተገለጠ ክብር ሲሆን ገነት ዉስጥ መኖር ማለት ነዉ (ቶማስ ብሩክስ)

እምነት ማህተም ሲሆን የእምነት ዋስትና የእግዚአብሔር ማህተም ነዉ (ክሪስቶፈር ነሴ)

አንድ ሰዉ ይህን ዋስትና እንዴት ያገኛል?

በመጽሐፍ ቅዱስ እዉነት የራስህን ሕይወት ማየት አለብህ ድነት ስለ ማግኘትህን በዉስጥህ ልዩነትን ተመልከት፤ አሁን ጽድቅን በመዉደድ ሐጢአትን ትጠላለህን? ቤተክርስቲያን መሄድ ትወድዳለህ? ወይስ ያስጠላሃል?፤ አሁን ጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ትርጉም አላቸዉ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለክርስትና መሰረት የሚሰጡህ ነገሮች ናቸዉ፡፡ ነገር ግን ከዚህ የሚበልጥ ነገር ያስፈልግሃል፤ ወደ መስቀሉ በመመልከት ጌታ ለአንተ ያደረገዉን ነገር ተመልከት፤ ጳዉሎስ በዚህ ይደሰታል (ሮሜ 8፡31-34) የእግዚአበሔርን ፍቅር ስትመለከት ትዕቢትህ ወደ ትህትና ይቀየራል፡፡ ወደ መስቀሉ ስትመለከት የአንተን ሁልጊዜ ሐጢአተኝነትህን እና የእግዚአብሔርን ፍቅር ታደንቃለህ፡፡ መስቀሉን በእንደዚህ ሁኔታ ስትረዳ ለዋስትና መሰረት ይሰጥሃል፤ እሰካሁንም ደረስ ይህ አይበቃም፡፡

ክርስቲያን ሐጢአተኝነቱን በደንብ ሲረዳ የእግዚአብሔርን ጸጋ ያደንቃል፤ መንፈስ ቅዱስም ዋስትናን በልቡ ዉስጥ ያረጋግጥለታል ሐዋርዉ ጳዉሎስ በዚህ ይደሰታል (ሮሜ 8፡16)፡፡

በሮሜ 5፡5 ላይም ‹‹*በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም*››

ዶ/ር ሊዮይድ ጆንስ ሲናገር፡-

ይህ ለክርስቲያን የተቻለ ትልቅ ዋስትና ነዉ፤ ይህን ዋስትና ማሳነስ የለብህም መጽሐፍ ቅዱስ ሲያረጋግጥ ‹‹አሁን በክርስቶስ ላሉ ኩነኔ የለባቸዉም›› ኩነኔ አነደሌለብኝ አምናለሁ ሰለዚህ ርግጠኛ ነኝ፤ይህ ልክ ነዉ፤ አሁን ደግሞ ጠለቅ ብለህ በመሄድ እንዲህ ማለት ትችላለህ ‹‹ ወደ አንደኛ ዮሐንስ መልዕክት በማንበብ ሕይወትን ስለ ልጅነትህ መፈተን ራሴን በዚህ ቃል ስፈትሽ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለዉን ማረጋገጫ አያለሁ ይህ ጥሩ ነዉ ሌላ አይነት የተሻለ ትልቅ ዋስትና አለ የተሻለዉም ዋሰትና ይህ ነዉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልብህ የፈሰሰዉን የእግዚአብሔርን ፍቅር ማሳነስ የለብም፤ በዚሁ መጽሐፍ 8፡16ላይ ተጽፏል፤ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክራል፤

የድነት ዋስትና ሲጀመር መሰረቱ ስሜት ላይ አይደለም፤ መሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል እግዚአብሔር ለአንተ አድርጓል ደግሞም በአንተ ዉስጥ እየሰራ ነዉ፤ የእግዚአብሔርን

ፍቅር ላልተረዳ ዋስትናን ቀለል አድርጎ ሊመለከት ይችላል፤ ዋስትና የሚገኘዉ ስለመዳን ራስህን ስላሳመንህ አይደለም፤ በመጀመሪያ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ ጸልይ እና በፈቃዱ ለአንተ የገባዉን ኪዳን አስብ (1ዮሐ5፡13)፡፡

ብዙ አዳዲስ አማኞች በዉድቀታቸዉ ላይ ትኩረት በማድረግ ዋስትናቸዉን የሚያጡ ይመስላቸዋል (1ዮሐ5፡13)፡፡ ድካማችንን መመልከት ጥሩ ነዉ ለመናዘዝም ይጠቅማል ነገር ግን በዉድቀት ላይ ብቻ ማተኮር ስለ ዋስትና ወደ አደጋ ሊያመራ ይችላል፤የድነት ዋስትና መሰረት ያደረገዉ በጽድቅ ላይ እንጂ በቅድስና ላይ አይደለም፤ወይም በሌላ ቋንቋ ዋስትና መሰረት የሚያደርገዉ ክርስቶስ ለአንተ ባደረገዉ ነገር ላይ ነዉ፡፡ በስራ ሳይሆን እንዲሁ በጸጋዉ ነዉ፤ክርስቲያን ያደረገን ጸጋዉ ነዉ፤የድነት ዋስትናችን መሰረት ያደረገዉ በጸሎታችን ወይም በመታዘዛችን ቢሆን ኖሮ ከፍና ዝቅ ባልን ቁጥር ዋስትናዉ ችግር ዉስጥ ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ በጸጋዉ ላይ መሰረት ካደረገ ከሆነ ግን ሁል ጊዜ በቋሚነት ይቆማል፡፡

14

ዉድቀት

አዳዲስ ክርስቲያኖች ጌታን በተቀበሉበት ዕለት በጣም ደስ ይላቸዉና በሚያልፉበት የተለያዩ ችግሮች ዉስጥ ሲያልፉ ግን ወደ ጥርጣሬ እና ፍርሃት ዉስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በፊት የሰራኸዉን ሀጢአት ታስታዉሳለህ በህይወትህ ላይ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ወደ ግራ መጋባት ዉስጥ ትገባለህ በአዲሱ ሕይወት ላይ ዉድቀት ይሰማሀል፤ በዚህ ያበቃልን? በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ይወድሃልን? ይተማመንብሀልን?

መልሱ አያበቃም ደግሞም እግዚአብሔር ፍቅሩ አያበቃም እዉነቱን ስትጋፈጥ ልትወድቅ ትችላለህ፤ ለክርስቲያን ሐጢአት ማለት ዉድቀት ሲሆን ከመዉደድ መዉደቅ፣አለማክበር፣እና እግዚአብሔር አለመታዘዝ ማለት ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ዉድቀትን አያስወግድም፤ ዉድቀት ለጊዜዉ ለቅድስና እንቅፋት ይሆናል፤ ነገር ግን በአንተን ጽደቅ ላይ ተጽዕኖ አያመጣም፤ ድነሀል፤ አሁንም የእግዚአብሔር ልጅ ነህ (ምዕ.2ን ያንብቡ)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚናገረዉ ብዙ ዉድቀት ዉስጥ ያሉ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በሐይል ሲጠቀምባቸዉ እናያለን፡፡

ለምሳሌ ዮሐንስ ማርቆስ ይህ አዲስ ክርስቲያን ሆኖ ከአገልግሎት የወደቀ ሰዉ ነበር (ሐዋ 12፡25-13፡13። ጳዉሎስንና በርናባስን በጴርያ ተለይቷቸዉ ነበር፤ በሐዋ 15፡36-41 ትቶአቸዉ ሄደ፤ ወንጌሉ እየተሰበከና እየሰፋ ሲሄድ መከራዉም የዚያህኑ ያህል እየጨመረ ሄደ፤ በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ማርቆስ መከራዉ ከአቅሙ በላይ ስለነበረ ተለያቸዉ፤ ስለዚህ ጳዉሎስ በጣም ስለተበሳጨበት በሚቀጥለዉ የወንጌል ጉዞ ላይ ሊያካትተዉ አልፈለገም።

ማርቆስ ስህተት ሰርቶ ነበር፤ ከአመታት በኋላ ጳዉሎስ ማርቆስን ለአገልግሎቱ ይጠቅመኛል ሲለዉ እናያለን በዚህም ወንጌልን ሊጽፍ ችሎአል፤(ቆላ 4፡10-11) ዛሬ በአዲስ ኪዳን ዉስጥ ሁለተኛዉን ወንጌልን ጽፎልናል ውድቀቱ ለመልካም ሆነለት። በዚህ ተጽናኑ፤ የሚወደን እና ይቅርታን የሰጠን አምላክ በወደቅን ጊዜ እንደማይጠቅም ዕቃ አድርጎ ይጥለናል የሚል ሐሳብ የለኝም፤ ጴጥሮስ አልወደቀምን?(ማር 14፡68) በሐዋርያት ስራ ዉስጥ ምን ያህል ታላላቅ ስራዎችን እንደሰራ ጌታም እንደተጠቀመበት እንመለከታለን።

ዉድቀት ማለት እንደማይጠቅም ዕቃ ተደርጎ መጥፋት ማለት አይደለም፤ ወደቀት ክፉ ነዉ እግዚአብሔርን ሊያሳዝንና በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ ችግር ሊያመጣ ይችላል፤(ሐዋ 15፡39)። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግስት ዉስጥ ጠቃሚነታችን ያበቃል ማለት አይደለም፤ በተለይም ስላለፈዉ ዉድቀታችን እያሰብን ወደፊት ያለዉን ነገር እንዳናስብ ስለሚደርገን ወደፊት ሊሆን ያለዉን ብቻ ነዉ ማየት ያለብን (ፊሊ.3፡13-14)።

ከዉድቀት መማር

በክርስትና ሕይወትህ ወድቀህ ታዉቃለህ? ከሆነ ከዚያ ዉድቀትህ መማር ይኖርብሃል፤ ወደ ስህተት ጎዳና ሄደህ ከሆነ አሁን ግን ወደዚያ ስህተት መንገድ መሄድ የለብህም፤ ዳቢሎስ ዉድቀትህን አይቶ ሊጎዳህ ይፈልጋል በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ድል ተሸጋገር፤ ዉድቀትህ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እንድትደገፍ ሊያስተምርህ ይገባል (ዮሐ 15፡1-5)።

አቤንኤዘር ማለት በብሉይ ኪዳን እስራኤል የዉድቀትና የድል ጊዜ ነዉ። በዚህ ጊዜ አስራኤል የቃልኪዳኑን ታቦት ያጡበትና በፍልስጥኤም የተማረኩበት ነዉ(1ሳሙ.4፡1-22)፤ ይህ የዉድቀት ጊዜ ሲሆን የእግዚአብሔርን ሕግ ችል ባሉ ጊዜ የሆነ ነገር ነዉ፤ምዕራፍ 1ሳሙ. 7ን አንብቡ እና አቤንኤዘርን ቁ.11 ላይ ያለዉን የአቤንኤዘርን ድል አንብቡ፤ አንዱ አምላክ በአንዱ ቦታ በተመሳሳይ ሕዝብ ተመሳሳይ ጠላት በሽንፈትና ዉድቀት ስፍራ ድል አለ፤ ለምን?

ቁ.2 ላይ በጌታ ፊት አለቀሱ ጌታን ተከተሉት ወደ እግዚአብሔርም ጮሁ

ቁ. 3-6 ወደ ዉደቀትና ሽንፈት የመራቸዉን ሐጢአታቸዉን ተናዘዙ

ቁ.8 በጌታ ላይ ብቻ እምነታቸዉን አኖሩ

በቁ.13-14 ላይ ዉጤቱ ተሃድሶ ሆነ። በሚቀጥለዉ ጊዜ ሲወድቁ አቤንኤዘርን ያስታዉሳሉ።

አቤንኤዘርን አነሳለሁ

በእርሱ ርዳታ መጥቻለሁ

ደስታን ተሰፋ አደርጋለሁ

ወደ ቤቴ በሰላም እደርሳለሁ

ብዙ ተቀበዘበዝኩኝ

ለምወደዉ ጌታ ሊነጥለኝ

ልቤን ዉሰደዉ

በላይኛዉ ቤትህ

አትመዉ

15

ወደ ኋላ መመለስ

ወደ ኋላ መመለስ ለክርስቲያን ከባዱና አስቸጋሪ ነዉ። ብዙዎቻችን በትንሹም ይሁን በብዙ በዚህ ዉስጥ አልፈናል። ወደ ኋላ የመመለስ ደረጃ አለዉ። የሚታወቅ ወደ ኋላ መመለስ አለ። ይህም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድን ማቆምና ከክርስቲያኖች ጋር ያለዉን ሕብረት ማቆም ነዉ። ብዙዎቻችን ይህን ስላላደረግን እግዚአብሔር ይመስገን። አንዳንድ ጊዜ ልባችንና አስተሳሰባችን አለማዊ የሚሆንበት ጊዜ ይኖራል።ቤተክርስቲያን መሄድን ልታቆም ትችላለህ። ዉጫዊ ማንነታችን ክርስቲያን ሊመስል ይችላል ዉስጣችን ግን ወደ ኋላ ሊያፈገፍ ይችላል።

ወደኋላ መመለስ ማለት ቅዳሜ ምሽት አልኮል መጠጣት ማለት አይደለም። ልብህ ከእግዚአብሔር ጋር አለመሆን ማለት ነዉ። እንደ ዴማስ ይህን አለም ወድዶ መኮብለል ማለት ነዉ(2ጢሞ 4፡10) ወደ ኋላ የሚሉ ክርስቲያኖች ማለት በልባቸዉ ይህን ዓለም የሚወድዱ ማለት ነዉ። የእግዚአብሔርን ነገር ጸሎትን፣ቤተክርስቲያን መሄድን፣መጽሐፍ ቅዱስ አለማንበብን፣ ሕብረት ያለማድረግና ይህን ዓለም መዉደድ ነዉ። እግዚአብሔር የከለከለዉን ነገር መዉደድና ማድረግ ማለት ነዉ። እግሩ ከመሄዱ በፊት አይኑና ልቡ የኮበለለ ማለት ነዉ።

ይህ ሁሉ ሂደት በጣም ግልጽ ነዉ። ሰዉ በአንድ ምሽት ወደኋላ አይልም ለብዙ ቀናት መጸለይ ስታቆም፣ወይም ከጸሎት ህብረት ራስህን ስታገልል፣በእሁድ የአምልኮ ጊዜ አንተ ግን የምትተኛ ከሆነ፣ለዚህ እሁድ ብቻ አልሄድም በሚቀጥለዉ ግን እሄዳለሁ ብለህ ራስህን ስታሳምን፣ እነዚህ ሁሉ ወደኋላ የማለት መጀመሪያ ምልክት ሲሆን፤ ቀስ በቀስ እየተቆጣጠረህ ይወስድሃል።

ክርስቲያን ወደኋላ የማለቱ ዉጤት ሌላዉን ክርስቲያን አለማመመኑና ሌሎች ክርስቲያኖችን ሲጠራጠር ነዉ። በቤተክርስቲያን ስላለዉ ሕብረት የሚያጉረመርም ከሆነ የሌሎችን ክርስቲያኖች ጥረት የሚያጣጥል ከሆነ እነዚህ ምልክቶቹ ናቸዉ።

የእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅነት

ወደ ኋላ ማፈግፈግ ካባድ ችግር ሲሆን እንዲህ በሚያደርጉት ላይ እግዚአብሔር አይደሰትም። ዳቢሎስ ደግሞ ይደሰታል። ወደኋላ ያፈገፈጉት አሁንም ክርስቲያኖች ናቸዉ።ድነታቸዉንም አያጡም(ዮሐ10፡28-29) እግዚአብሔር አሁንም ይወደዋል። ዳዊት ወደኋላ በመመለስ የዳበረ ልምድ ነበረዉ።(መዝ 51)። ነፍሴን መለሳት ብሎ ሲናገር እናያለን።(መዝ 23፡3)። እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመዉደድ ወደኋላ አላለም።መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ሕዝቡን እንደሚወድድ ይናገራል።በዚህ ክፍል ዉስጥ ወደኋላ ያፈገፈገዉን ሕዝቡን እግዚአበሔር እንደሚፈልጋቸዉ እናያለን።

ሁለቱ ታዋቂ ነብያት እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚወድድ የተናገሩት ኤርምያስና ሆሴዕ ሲሆኑ በማስተዋልና በጸሎት ክፍሉን አንብቡት (ኤር3፡12-19) ወደ ሆሴዕ መጽሐፍ ስትመለሱ እግዚአብሔር ነብዩን ሄደህ ጋለሞታይቱን ጎሜርን አግባ ሲለዉ እንመለከታለን (1፡2-3)። ይህ የሚያሳየዉ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ፊቱን አዙሮ ጣኦትን በማምለክ ስራ በተጠመደ ጊዜ

ነበር፤(3፡1) ምዕራፍ 14፡1-4ን አንብብ፤ ይህ መለኮታዊ የሆነ ታላቅ ፍቅር ሲሆን ለኮበለለ ሕዝቡ ፍቅሩን የገለጸበትና ነፍስን እንደሚያድስ የሚናገርበት ነዉ፡፡

እግዚአብሔር በልዑላዊ ሐይሉ ያድነናል፤ነገር ግን በዚህ ሀይሉ እኛ ወደኋላ እንዳናፈገፍግ አይከለክለንም፤የተዋጀችዉ ነፍስ ነጻነት ያላት ነፍሰ ናት፤ ከድነት በፊት በባርነት ዉስጥ ነበረች (ኤፌ2፡1-3)፤ መዋጀት እኛን ነጻ ያደረገን በጌታ እንድንደሰትና እርሱን እንድንታዘዝ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ነጻ በሆነ ልብ እንድንወደዉ ይፈልጋል ነገር ግን የማንታዘዘዉ ከሆነ እርሱ እንደገና ፍቅሩን በጥልቀት እንድንረዳዉ፣ በፈቃዱ ይቅር ይለናል ያድሰናልም፡፡

ተሐድሶ

በንስሀ ዉስጥ ተሀደሶ ይኖራል ወደኋላ ያፈገፈጉ ሁሉ በይቅርታና በጸጸት ራሳቸዉን ይመለከታሉ፡፡ ያ ንስሀ አይደለም፤ ንስሀ ማለት ግለሰቡ ራሱ የሚያዉቀዉና ሌሎች ሰዎች የማያዉቁት ነዉ፤እግዚአብሔር ሐጢአትህን ያዉቃል በሀጢአትህም ታዝናለህ ምክንያቱም ፍቅር የሆነዉን እግዚአብሔርን በድለሃል፤ንስሐ ጸሎትን የሚያፈራ ነዉ፡፡ ለዚህም ማሳያ ዳዊት ነዉ (መዝ 51)፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንዲህ ያለዉን ጸሎት መስማት ይወድዳል፤ እግዚአብሔር ይመስገን ‹‹ነፍሴን መለሳት›› መዝ 23፡3 ::

ወደኋላ የተመለሱ ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባዉ ጉዳይ አንድ ነገር ሲሆን ይኸዉም ንስሐ ነዉ፡፡ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ያስፈልጋቸዋል፤ *‹‹ቍጣዬ ከእርሱ ዘንድ ተመልሶአልና ዓመፃቸውን እፈውሳለሁ፥ በገዛ ፈቃዴ እወድዳቸዋለሁ፡፡›› ሆሴዕ 14፡4፤ ተምችና ኩብኩባ የበላዉን ወራት እመልስላችኋለሁ (ኢዩኤል 2፡25)* ለብዙ አመታትና ወራት ወደ ኋላ የተመለሱ ሰዎች ልባቸዉን በማጠንከር ለጊዜዉ የጠፉ ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ለድነት ቀን ይታደሳሉ፤ ድነት በአንድ ቀን በቅጽበት የሚሆን አንጂ የሚታይ የሚባል ዘመን የለዉም፡፡

መንፈስህ ወደኋላ የተመለሰ መስሎህ ከታየህ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ተመለስ የት ጋ ስህተተ እንደሰራህ እንዲያሳይህ እግዚአበሔርን ጠይቅ፤ ሀጢአትህን ለእርሱ ተናዘዝ፤ እርሱ ሐጢአትህን ይቅር ይልሃል ያድስሀልም፡፡

16

ምሪት

የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዴት አወቃለሁ? እግዚአብሔር ምን እንዳደርግ ይፈልጋል? ብዙ ክርስቲያኖች እንዲህ አይነት ጥያቄ ይጠይቃሉ፤ ምሪት ዋናዉ ጥያቄ ነዉ።

ጥቂት ክርስቲያኖች በዚህ ጉዳይ ጥያቄ ያለባቸዉ ሲሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ከእነዚህም ዘዴዎች መካከል መጽሐፍ ቅዱስን በድንገት ጣትን በማስገባት እንደ እድል በመክፈት ጌታ ተናገረን ወይም ፈቃዱን አወቅሁ ይላሉ፤ ይህ የከተቱት ቦታ ግን የራሱ የሆነ አዉድ ያለዉ ሲሆን አዉዱን ሳያዩ ለእኔ ጌታ የተናገረዉ ስፍራ ነዉ ይላሉ፤ እንዲህ አይነቱን ዘዴ እንደ ቸነፈር ማስወገድ ያስፈልጋል፤ እንዲህ አይነት ታሪክ አለ አንዱ በድንገት መጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ ሲያነብብ ጣቱ በማቴ27፡5 ላይ ይከፍታል ‹‹ ይሁዳ...ታነቀ›› እንደገና ጸለየና አሁንም በድንገት ሲከፍት በሉቃስ 10፡37 ‹‹ አንተም እንዲሁ አድርግ›› የሚል ስፍራ አገኘ፤ ምን ያህል ይህ ታሪክ እዉነት ለመሆኑ ርግጠኛ አይደለሁም። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ዘዴ ተገቢ አይደለም፤ በርግጥ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በኩል ይናገራል፤ ይህ ማለት ጥቅሶችን ወደ አእምሮአችን በማምጣት እንጂ በድንገት ጥቅስ ከማዉጣት ጋር የተገናኘ አይደለም።

አንዳንድ ክርስቲያኖች ወደ ግል ስሜታቸዉ ላይ ይደገፋሉ፤ ብዙ ጊዜ ‹‹ጌታ ተናገረኝ›› ማለትን ይወዳሉ›› ጌታ በዚህ ጉዳይ ፈቃዱን ይገልጣል፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ለመግለጡ የሚደግፍ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ነገሮችን መመርመር ያስፈልጋል፤ የእዉነት መንፈስ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ የከለከለዉን ነገር እንድታደርግ አይፈቅድም።

የምሪት ሕጎች

መዝሙረኛዉ ሲናገር ‹‹ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው›› መዝ 119፡105፤ይህ የሚያስታዉሰን በየዕለቱ በሕይወታችን የሚገጥመን ነዉ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ይነግረናል፤መጽሐፍ ቅዱስ የከለከለዉን ነገር ለማወቅ ሌላ ምሪት አትፈልግ ነገር ግን ለቃሉ ታዘዝ፤ መጽሐፍ ቅዱስ አድርግ ያለህን ነገር

ያለማመቻመች ታዘዝ እንጂ ሌላ ምሪት አትፈልግ። በየቀኑ በታማኝነት መጽሐፍ ቅዱስን የምትታዘዝ ከሆነ በሕይወትህ በሚገጥምህ ከባዱ ነገር ለመወሰን አትቸገርም ቃሉ ይመራሃል። በየቀኑ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የምትገዛ ከሆነ ትናንሽ ውሳኔዎችን ለመወሰን ቀላል ነዉ። ይህን እያደረግህ ስትሄድ በትላልቅ ጉዳዮች ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትና መወሰን ከባድ አይሆንብህም።

በግል ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት በራሱ ችግር የለበትም። ምክንያቱም ምሪትን ከመንፈስ ቅዱስ መለየት አይቻልም። መንፈስ ቅዱስ መንፈሳችንን ይመራል ይህንን መለያየት አይቻልም። የዉስጣችን ፍላጎት ጠንካራ ሲሆን የስጋ ስራ እንጂ መንፈስ ቅዱስ ሊሆን አይችሉም። እነዚህን ነገሮች እንዴት መለየት ይቻላል? እነዚህን ጥያቄዎች ለራስህ ጠይቅ። ስለዚህ ጉዳይ ጸልዬ አዉቃለሁን? ስለ ራሴ ፍላጎት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እግዚአብሔር የሚፈልገዉን ነገር አደርጋለሁን? እነዚህ ነገሮች ለአንተ እዉነትና የምታምነዉ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ እየመራህ እንደሆነ ትገነዘባለህ።

ምሪትን በትክክል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካልተረዳህ አደጋ ሊሆን ይችላል። ልናደርግ ያለዉን ነገር መወሰን ያስፈልጋል። ሕሊናችንንም ማዳመጥ ያስፈልጋል። ክርስቲያን በመሆንህ በተለያዩ ችግሮች ላይ ሶስት ወይም አራት ጥቂዎችን ለራስህ ብትጠይቅ ሌሎችም ክርስቲያኖች እንዲሁ ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄዎችን ሊጠየቁ ይችላሉ። የእግዚአበሔርን ፈቃድ ለማወቅ ፍላጎቱ ከሌለህ አንተ የወሰንከዉን ነገር ለማድረግ ወደኋላ አትልም።

እግዚአብሔር በግልጽ ፈቃዱን ገልጦ ሳለ በጣም ከባዱ ጉዳይ ከስሜታችን የተነሳ የእርሱን ፈቃድ ለመረዳት እንቸገራለን። እነ አጋቦስ ሉቃስና ሌሎች አማኞችን ማየት ይቻላል (ሐዋ 21፡10-14) ለጳዉሎስ ትልቅ ፍቅር ስላለዉ እስር ቤት እንደሚገባ ነገረዉ። ስሜቶቻችን ጠንካራ ሆነዉ አድገዉ ፍርዱ ግን ስህተት ነዉ። ሁላችንም እንዲህ ማለት ያስፈልጋል ‹‹ የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን›› ለጌታ ፈቃድ የሚያስፈለገዉን ዋጋ መክፈል ካስፈለገም መከፈል ይገባል።

የምሪት ችግር ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ህብረት ችግር ነዉ።በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች እንኳ በዚህ ነገር ችግር ነበረባቸዉ።ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት ሲኖሩ የእርሱ ፈቃድ ግልጽ ይሆንላቸዋል። ስለዚህ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ነገራቸዉ ዝቅ ባለ ጊዜ ታላላቅ

የሆነ ዉሳኔዎችን መወሰን የለባቸዉም፤ ከወሰኑ ግን ወሳኝ በሆኑ የሕይወት ዘይቤያቸዉ ላይ የስህተት ዉሳኔ ሊወስኑ ይችላሉ፤

በጥርጣሬ ጊዜ

በሕይወታችን ከባድ ዉሳኔ በሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ለምሳሌ አምልኮ በሚያስፈልግ ጊዜ፣የት እንደምትኖርና ምን እንደምትሰራ፣ እናም ሌሎችን ከባድ የሆኑ ነገሮችን ለመወሰን ስታስብ የሚከተሉትን የዮሐንስ ፍላቨልን ምክር መስማቱ ጠቃሚ ነዉ፡-

በጥርጣሬ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈልግ ሕይወትህን በእነዚህ ድንጋጌዎች ምራ

- ልብህ በእዉነት እግዚአብሔርን ይፍራ እርሱን ከማሳዘን ተቆጠብ
- ቃሉን በጣም አጥና ለአለም ያለህ ፍላጎት በእጅጉ ቀንስ
- የምታዉቀዉን ነገር ተግብር፣የምትሰራዉን ነገር ዕወቅ
- ለአብርሆተ መንፈስ ቅዱስ ጸልይ ወደ ምትሄድበት ጎዳና እንዲመራህ ጸልይ
- ቃሉ ለሚልህ ነገር ታዘዝ ተስማማ ከዚያ በላይ አትሂድ

ዳዊት በመዝሙር 23 ላይ ያለዉን ማንበብ ተገቢ ነዉ፡፡ ‹‹በጽድቅ መንገድ መራኝ›› እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመራህ በጽድቅና እርሱን በመምሰል ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ትንሽ በመጸለይ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናትና በሕብረት በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር ሊመራህ አይችልም፤ እርሱ ሁልጊዜ በራሱ ሐሳብ ይመራሃል እንጂ እርሱን ከሚነጥል ሐሳብ አይመራህም፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድ ግልጽ ካልሆነልህ ግልጽ እስኪሆንልህ ድረስ በዝግታ ጠብቅ እንጂ በራስህ አትወስን፤ እግዚአብሔር በሮችህን በፊትህ ከዘጋብህ በምንም ሁኔታ ለመክፈት መታገልና ባለመታገስ ለመክፈት አትሞክር፤ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ትክክለኛ የሆነ በር በራሱ ጊዜ ይከፍታል፤ ይህን ሁልጊዜ ያደርገዋል (ሐዋ 16፡6-10)፤ አትቸኩል፤እግዚአብሔርን ታመን በዚህ ጊዜ ፈቃዱን ያስታዉቅሃል፡፡

ሌላዉ ማድረግ ያለብህ ብዙ ማመናፈስም ትክክል አይደለም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን ስትተገብር ብዙ ችግሮች የሚፈቱ ይሆናሉ፡፡

17

ራስን ማስገዛት

ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት ራስን ማስገዛት ማለት ቀላል ነገር ሊሆን ይችላል፤ ነገሮችን ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ ወደ ስራ መሄድ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መሄድ፤ ወይም ስፖርት መስራትና መዚቃ መጫወት ትወድድ ይሆናል። በሕይወታችን ራስን ማስገዛት በጣም ትንሽ የሆነ ስፍራ ሊሆን ይችላል፤ነገር ግን አንድ ሰዉ ክርስቲያን ሲሆን ነገሮች ይለወጣሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ራስን ስለመግዛት ይመክራል፤ በተደጋጋሚ ማንበብ ያለብን በ2ጴጥ 1፡5 ‹‹*ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ*›› ‹‹ ዳንኤል በልቡ እንዳይረክስ አሰበ››(ዳን1፡8) በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ(ፊሊ3፡14)፤ ‹‹...አሮጌውን ሰው አስወግዱ...›› ኤፌ 4፡22-25 እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ ስለ ራስን መግዛት የሚያስተምሩ ናቸዉ።

ጠቃሚነቱ

ምናልባት ራስን ማስገዛት ለመንፈሳዊነት ብዙ አይጠቅምም ልትል ትችላለህ በርግጥም እምነት አለን እምነት እጅግ አስፈላጊ ነዉ ራስን ካላስገዛህ እምነት ብቻዉን አያድግም።

‹‹*በቤተክርስቲያን ዘመን ዉስጥ ሁልጊዜ የቅዱሳንን ሕይወት እንድታነቡ አበረታታችኋለሁ፤ በቅዱሳኑ ሕይወት ዉስጥ ትልቁ ነገር ራስን መግዛት መቻላቸዉ ነዉ፤ በጣም ታላላቅ ሆኑ ወንዶችና ሴቶች የሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች የተለያዩ ባህርያት አላቸዉ፤ የእነ ሄነሪ ማርቲን፣ዳዊት ብረይነርድ፣ዮናታን ኤድዋረድ፣ ወንድማማቾቹን ዌስሊያኖቹን፣እና የዋይትፊልድን የሕይወት ታሪክ አንብቡ፤የትኛዉ ቤተክርስቲያን አባላት ናቸዉ የሚለዉን ሳይሆን እንዴት ሕይወታቸዉን እንዳስገዙና ይህን እንዳስፈለጋቸዉ ሲሆን ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ፍጹም አስፈላጊ ነዉ፤››።* (ዲ.ኤም ሊዮድ ጆንስ)

ጋዜጣ ላይ የሕይወት ታሪካቸዉን ልታነብብ ትችላለህ፤የልብ ወለድ መጽሐፍ ያለምንም ችግር ይኖራል፤ ነገር ግን ለ5 ወይም ለ10 ደቂቃ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ በዉስጥህ የሚፈጥረዉን

ስሜት ድካም ነዉ ወይስ መሰልቸት? ጸሎትም ተመሳሳይ ነዉ፤ ቴሌቪዥን ከ1 ሰዓት በላይ ስትመለከት አትደክምም **ነገር ግን** አጭር የጸሎት ጊዜ ሲኖር አእምሮህ መጨነቅ ይጀምራል፤ለምን ይህ ይሆናል? ይህ የዳቢሎስ ስራ ነዉ፤

ይህ በአጠቃላይ በዳቢሎስ የተሰራ የስንፍና ስራ ነዉ፤ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ስንመጣ ድካምን ስንፍናን ማሳየት ሳይሆን መነቃቃት ያስፈልጋል። ለተጠራንበት ዓለማዊ ስራም በንግድ፣በስራ ወይም በሌላ ስራ ተመሳሳይ የሆነ ባህርይ ነዉ የምናሳዉየዉ? (ዲኤም ሊዮድ ጆንስ)

በዚህ ጉዳይ በአንድ ነገር ብቻ ነዉ መነጋገር ያለብን ‹‹ዳቢሎስን ተቃወሙ›› (ያዕ.4፡7) ይህን ለማድረግ በመጀመሪያ ‹‹ለእግዚአብሔር መገዛት ያስፈልጋል›› ችግሩ ብቻዉን የሚሄድ አይደለም።

‹‹ያዕቆብ በመልዕክቱ ለፈጣን ቅድስና አይደለም፤ክርስቲያን በቀላሉ ድል እንደማያገኝ ያወቃል ከመጀመሪያዉ በዓለም እንደምንኖር አስጠንቅቆናል (1፡1) መጨረሻ ለሌለዉ ፈተና(1፡2) እግዚአብሔር ባሰመረለን ጎዳና እየተጓዝን ወደ ብስለት በማደግ ጠላትን መቃወም ያስፈልጋል (1፡3፣4) ይህ ጦርነት እና ይህ መንገዱ ነዉ፤ግጭቶችን በማስወገድ እና አክሊል መድፋት አይቻልም፤ ድል የእኛ የሆነ ወይም የምንወስደዉ ሳይሆን አሸናፊዎቹ የራሳቸዉ የሚያደርጉት ነዉ››። (ጄኤ ሞትየር)

ራስን ማስገዛት ማለት ስሜቶችህን በመቆጣጠር መልካም የሆነዉን ነገር ማድረግ ማለት ነዉ፤ ምንም ክፉ የሆነ ፍላጎት ቢኖርም ወይም የተፈጥሮ ፍላጎቶች ቢኖሩም ክፉ ነገርን ከማድረግ መቆጠብ ማለት ነዉ (ኤፌ 4፡17-32)።

ጥቅሞቹ

በየቀኑ በምናደርገዉ ራስን ማስገዛት ወዲያዉ ታላቅ የሆነ ጥቅም ልናገኝ አንችልም። ጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት አስፈላጊ ነዉ። ጊዜን ወስኖ ለዚያ ጊዜ ራስን መስጠት ማለት የሕግ ሰዉ መሆን ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ነገር ጥሩ የሆነ አቀራረብ ነዉ፤ለተለያየ ነገር ጊዜ ማጥፋት ቀላል ሆኖ ሳለ ነፍስን ለመመገብ ግን ጊዜ የለኝም ማለት ተገቢ አይደለም።

ራስን ማስገዛት ማለት ደስታን የሚወስድ አይደለም፤ ቀጣይነት ያለዉን ደስታ ሊያመጣ የሚችል ነዉ፤ በተቃራኒዉ ከጌታ ጋር ያለንን ሕብረት ያጠናክራል፣ደስታን የሚጨምር ነዉ ከሐዋርያዉ ጳዉሎስ በላይ ራሱን ያስገዛ ሰዉ አለ ብለህ ታስባለህ? ሰዉ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ የጌታ ደስታ በዉስጡ ይፈስሳል፤

‹‹ብዙ ሰዎች እንደሚሉት የሆነ ነገር እንዲኖርህ ስጥ ነገር ግን የቅዱሳን እዉቀት ያላቸዉ‹‹ ያንን ደስታ ካለኝ ለአለም ሁሉ እሰጣለሁ ለምንድን ነዉ? እንዲህ ያለ የሞቀ ልብ የሌለኝ? እንዲህም ይላሉ መልሱ እንዲህ ማሰብ የለብህም የሚል ነዉ፤ ራሳቸዉን ለጸሎትና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የሰጡትን ሰዎች የሕይወት ልምምድ ተመልከቱ፤ ራሳቸዉን ለባህልና ለመንፈሳዊ ሕይወት ያስገዙ ናቸዉ፤ እግዚአብሔርም ራሱን ለእነርሱ በመግለጽ ካሳቸዉ ይህ ታላቅ የሆነ ልምምድ ልብን የሚያሞቅ ነዉ፤›› (ዲ.ኤም ሊዮይድ-ጆንስ)

ማንኛዉም ሰራዊት ራሱን ሳያስገዛ ድልን ማሰብ የለበትም፤ ክርስቲያንም እንዲሁ ራሱን ለማስገዛት ዉሳኔን ካላደረገ ድልን ማሰብ የለበትም፡፡

18

ሥራ

የሚቀጥሉት ሶስት ርዕሰ ጉዳይ ላይ እናወራለን ይህም *ሥራ*፣ጋብቻ እና ሰንበት ሲሆኑ እነዚህም ‹‹የተፈጥሮ ሹመቶች/ትዕዛዛት ናቸዉ›› ምክንያቱም በመጀመሪያ እግዚአብሔር በምድር ላይ ለሰዎች የሰጣቸዉ ናቸዉ፤ዘፍጥረት 1 እና 2ን አንብቡ፡፡

አስተማሪ ብትሆን ወይም ተማሪ እርሱ ዋና ጉዳይ አይደለም፤ ሰራተኛዉ ይሁን አሰሪዉ ሁሉም መስራት አለበት፤ ጌታ ይህን በግልጽ ሲናገር ዘፍ 2፡15፤ አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ዉስጥ ብቸኛ ሆኖ እንዲኖር አልነበረም ነገር ግን ‹‹እንዲያበጁ››(ይህም እንዲሰራ ማለት ነዉ)፤ይህ ሐጢአት ወደዚህ ምድር ከመግባቱ በፊት ማለት ነዉ፤*ሥራ* ለሰዎች የተሰጠ ትዕዛዝ ነዉ፡፡

የክርስቲያን አመለካከት

በክርስቲያን አመለካከት በግልጽ እንደሚያስተምረዉ በ (ኤፌ 6፡5-9) እንደተነገረን ማድረግ (ቁ.5) በመፍራትና በመንቀጥቀጥ አድርጉ ባልተቀየጠ ስሜት (ቁ.5)፤ በምናየዉ እይታ ሀጢአት መስራት የለብንም፤ ሰዎች ሥራ እስካለ ድረስ መስራት አለባቸዉ ክፍያ ለማህበራዊ ጉዳይ አስፈላጊ ቢሆንም ሥራ አስፈላጊ ነዉ፡፡

ዛሬ ስለ ስራ ያለን አመለካከት ተቀይሯል በኤፌ 6፡7 ላይ ‹‹ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ›› ይላል ሥራህን በዚህ ጉዳይ ካልሰራህ ራስህን ቆም ብለህ መጠየቅ ይኖርብሃል፤እግዚአብሔር እንድትሰራዉ የፈለገዉን ስራ ስለመስራትህ ራስህን ጠይቅ፡፡

እግዚአብሔር በሚፈልገዉ ዓይነት በእዉቀትም በአካልም በሙሉ ልብህ ሥራን ልትሰራ ይገባሀል፡፡ እግዚአብሔር በሰጠህ ስጦታና በችሎታህ በሙሉ ልብህ መስራት ይጠበቅብሃል፡፡ የምትሰራዉ ስራ የመጽሐፍ ቅዱስን ድንጋጌ የሚሸር መሆን የለበትም፤ መንፈሳዊ ሕይወትህንም የሚያደክም መሆን የለበትም፤ ሁላችንም የሚያስደስትና ትልቅ ክፍያ የሚያስከፍለዉን ስራ መስራት እንፈልጋለን፤ ነገር ግን በጣም አስፈላጊዉ ነገር እግዚአብሔር በሚፈልገዉ ስፍራ ላይ ሆኜ እየሰራሁ ነዉ ወይ? ብለን መጠየቅ አለብን፡፡ ሥራ ሊናቅ አይገባም፤ሥራዉ አሰልቺና ከባድና የማያስደስት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን መስራት ‹‹ ጌታን እንደምታገለግሉ›› ይላልና ባህሪህን የሚቀይር ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ሰዉ የተጠቀመበትን ቆሻሻ በቅርጫት ዉስጥ የሚያደርግ ከሆነ ከተማዋን ከበሽታ ይጠብቃታል ይህም ከዶክተር የተሻለ አስተሳሰብ ነዉ፡፡

ትክክለኛ የሆነ ባሕርይ

ክርስቲያን ስልጡን ሠራተኛ ላይሆን ይችላል፤ ነገር ግን በሙሉ ልቡ ሊሰራ ይገባል፤ለምሳሌ ክርስቲያን በትምህርት ቤት ዉስጥ ሲማር ደካማ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን በትጋት በማጥናት የሚችለዉን ያህል መስራት አለበት ይህ ከባድ ስራ ነዉ፡፡ ሥራቸዉን በጊዜ የሚሰሩና በተቻለ መጠን መሥራትና መትጋት ይጠበቅባቸዋል፤አስተማሪዎችም ትሁትና ሊታመኑ የሚችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

ከሌሎች ስራ ይልቅ አብዛኛዉን ጊዜያችንን ማጥፋት ያለብን በስራ ላይ ነዉ። ስለዚህ ለስራ ያለን አመለካከትና ባህርይ በጣም አስፈላጊ ሲሆን ያላመኑ ሰዎች ሲመለከቱን እና በክርስቶስ ለመሆናችን ልዩነቱን ማየት አለባቸዉ። ቸልተኝነትና ስንፍና የክርስቲያን ባሕርይ ሊሆን አይገባም፤ በተቃራኒዉ ታማኝ፣ ጎበዝ፣እና ሰዓት አክባሪ መሆን አለበት፤ በተጨማሪም በኤፌ 6፡5-8 እና ቲቶ 2፡9-10 እና 1ጴጥ 2፡18-20፤ በዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ የትኩረት ምክር አይሰጥም፤ባሪያ የሚለዉን ቃል ሠራተኛ በሚለዉ መተካት አለብህ፤ ከዚያም በኋላ በስራህ ቦታ ምን እንደምትሰራ ማሰብ አለብህ፤ የተቀጠርከዉ ወንጌል ልታሰራጭ ሳይሆን ልትሰራ ነዉ፤መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠህን መመሪያ የምታፈርስ ከሆነ በስራህ ቦታ የምታደርገዉ የወንጌል ስርጭት ዉጤታማ አይሆንም፤ ክርስትናህ በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት፣ በተቀጠርክበት ቦታ ሁሉ የተሻለ ሠራተኛ ካላደረገህ ዉጤታማነትህ በጣም ዝቅተኛ ነዉ፤ በስራህ ስፍራ በተሰጠህ የሀላፊነት ቦታ ታማኝነትን ካላሳየህ በቤተክርስቲያን ዉስጥ ለተለየ አገልግሎት ሊጠራህ አይችልም።

በተሰጠህ የስራ ቦታ ላይ እግዚአብሔር በሰጠህ ችሎታ በሙሉ ሐይል መስራትና በተለያየ ምክንያት ሥራህን ለተለያየ አላማ መጠቀም ወይም ልዩ ትርፍ ለማግኘት ሌላ ዘዴ መጠቀም መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸዉ ትልቅ ችግር ዉስጥ አሉ፤ ስራ በመልቀቅና በቤታቸዉ በመሆን ምናልባትም አዲሱ ስራ ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ሊሆን ይገባል፤ ትልቅ ስራ መስራትና የተሻለ ገቢ ማግኘት በራሱ ክፉ አይደለም፤ ነገር ግን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ምሪት ተከተል።

ሥራህን መልቀቅ ማለት ቤተክርስቲያንን መልቀቅ ማለት ነዉ፤ በጣም *መጠንቀቅ የሚገባህ* የእግዚአብሔርን ቃል የምትማርበትና የምትካፈልበት ቤተክርስቲያን ሊኖርህ ይገባል፤ ከሌሎች ክርስቲያኖችም ጋር ሕብረት ይኑርህ።

19

የጌታ ቀን

በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነዉ የጌታ ቀን ተብሎ የተጻፈዉ፤ እርሱም በራዕይ (1፡10) ነገር ግን ስለ ሰንበት የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ፤

‹‹ የጌታ ቀን የሚለዉ ትርጉም ለሰንበት የተሰጠዉ ርዕስ ነዉ፤ ከብሉይ ኪዳኑ ቅዳሜ ወደ ከሳምንቱ መጀመሪያ ተደርጎ የተቀየረዉ በጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ ነዉ፤ ጌታ የሚለዉ ቃል ሥልጣንን የሚያሳይ ነዉ፤‹‹የሰዉ ልጅ የሰንበት ጌታ ነዉ››(ማር 2፡28) ይህ የሚያሳየዉ የቀን ለዉጥን ነዉ፤ዛሬ ለእኛ እሁድ ማለትና የጌታ ቀን ማለት እኩል ትርጉም ያለዉ ነዉ ‹‹የጌታ ቀን›› ወይም ‹‹ሰንበት›› (ኤ ደብሊዉ ፒንክ)

ጥያቄዉ ግን ብዙ ወጣት ክርስቲያኖች እና የቆዩት ክርስቲያኖች እንዴት ነዉ እሁድን የሚረዱት? ሁሉም የብሉይ ኪዳን ሕጎች አሁን በአዲስ ኪዳን ይተገበራሉን? ይህን ለመመለስ በመጀመሪያ አስሩን ትዕዛዛት ማንበብ ያስፈልጋል (ዘጸ 20፡1-17) በተለይም አራተኛዉ ትዕዛዝ (ቁ.8-11)

‹‹አስታዉስ በሚል ቃል በመጀመር እነዚህን አስሩን መመልከት አስፈላጊ ነዉ፤ ምክንያቱም የሰዉ ልጅ የመርሳት ባሕርይ አለበት፤ ይህን አስታዉስ የሚለዉ ንግግር አስፈላጊ የሆነዉ በተለይም የሰንበት ትዕዛዝ የተሰጠዉ በሲና በረሃ በሙሴ ሳይሆን ከዚያ በፊት ስለነበር ነዉ፤ አስታዉስ ከተባለ ከዚህ በፊት የሰማዉን ነገር ወደኋላ ሄዶ እንዲያስታዉስ እንጂ አዲስ ትዕዛዝ እንዳይደለ ማሳያ ነዉ፤ ኢሮኒየስ ያለዉን ነገር አሁን ማስታወሰ ይገባል ይኸዉም ሰንበት የተሰጠዉ ለአይሁድ ሲሆን በሙሴ ሕግ ዉስጥ የተጠቃለለ ነዉ የሚል ነዉ፤ ይህ ስህተት ነዉ›› (ኤ ደብሊዉ ፒንክ)

በሌላ ቋንቋ ሰንበትና አስርቱ ትዕዛዛት የተጀመረዉ በሙሴ አይደለም የሚል ሲሆን ከመጀመሪያም ፍጥረት ሲጀመር ከዘፍ 1-2 ጀምሮ አብሮ የተሰጠ ትዕዛዝ ነዉ፤ሦስቱ ትዕዛዛት ሥራ፣ጋብቻና ሰንበት በእግዚአብሔር ለሰዉ ልጆች ጥቅም ለሁል ጊዜ የተሰጡ ናቸዉ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ማር 2፡27 ‹‹ሰንበት ስለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ስለ ሰንበት አልተፈጠረም›› ኢየሱስ ያረጀዉን ስርዓት ሊቀይር እንደመጣ አያሳይም፤ ነገር ግን የፈሪሳዉያንን በሰንበት ላይ ያላቸዉን አመለካከት ነዉ የተቃወመዉ፤እርሱ እግዚአብሔርን ማምለክ ምን ማለት እንደሆነ የተዛባዉን አመለካከት ሚዛን በማስጠበቅ ሁልጊዜም በምሳሌ እንደሚናገረዉ‹‹ ሰንበት የተፈጠረዉ ለሰዉ ነዉ›› አለ፡፡

በአዲስ ኪዳን በግልጽነት ከኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ ክርስቲያኖች በእሁድ ለአምልኮ ይሰበሰቡ ነበር፤ በሳምንቱ መጀመሪያ የፋሲካ ዕለት ጌታ በታላቅ ክብር ስለተነሳ ቀኑ ሊቀየር ቻለ፤ ይህም ለመቀየር ነጻነት ኖሮአቸዉ ሳይሆን የተቀየሩት ከፍጥረት ትዕዛዝ የተነሳ ነዉ።

ክርስቲያኖች በእሁድ ምን መስራት አለባቸዉ?

በአድርግና አታድርግ ሕግ ዉስጥ ገብተዉ በፈሪሳዉያን ወጥመድ ዉስጥ መግባት የለባቸዉም፤አራተኛዉ ትዕዛዝ ፈርሷል ብለን ማሰብ የለብንም፤ በዘፍ 20፡8-11 ሁለት መሰረታዊ እዉነቶች አሉ።

አንደኛዉ ቀናትን ቅዱስ ብለን ማሰባችን ነዉ፤ ይህ ማለት ሰንበትን እግዚአብሔርን ለማምለክ መጠቀም አለብን፤ በርግጥ ሁልጊዜ ነዉ እግዚአብሔርን ማምለክ ያለብን፤ ነገር ግን በእሁድ ቀን በጋራ ተሰባስበን ማምለክ ይኖርብናል፤ በግል ሳይሆን በቤተክርስቲያን ማለት ነዉ፤ ለአምልኮ ጊዜን መስጠት አለብን፤ በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ያገኘነዉን መዳን እግዚአብሔርን ለማመስገን በእሁድ ቀን መሰባሰብ አለብን፤ የድል ቀን ነዉ ይስሀቅ ዋትስ የተባለ ሰዉ በመዝሙሩ እንዲህ ይላል‹‹ ይህቺ ቀን ጌታ የሰራት ቀን ናት››።

ዛሬ እርሱ ከሞት ተነስቷል

የሰይጣን መንግስት ፈርሷል

ቅዱሳን ድሉን ያሰራጫሉ

ተአምራቱንም ይነግራሉ፤

በቤተክርስቲያን ዉስጥ በእሁድ ሁለት አይነት አገልግሎት ካለ በአንዱ ፕሮግራም ላንረካ እንችላለን፤ብዙ ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወይም ክርስቲያናዊ መጽሐፍትን ለማንበብ ጊዜ የለኝም በማለት ሲያጉረመርሙ እንሰማለን፤ እሁድን በአግባቡ ብንጠቀም ብዙ ጊዜ ይኖረናል።

ሁለተኛዉ ክስራ የምናርፍበት ቀን ነዉ፤ ‹‹ሰንበት›› የሚለዉ ቃል ‹‹እረፍት›› ማለት ነዉ። እግዚአብሔር ሲፈጠረን በሰባተኛዉ ቀን እንድናርፍ ነዉ፤ ብዙ ሰዎች ግን ከፈጣሪ ይልቅ ጥበበኛ ለመሆን እርሱ ያዘጋጀዉን ነገር ችል ይላሉ፤ ሁል ጊዜ ለኋለኛዉ ሕይወት ዋጋ

ይከፍላሉ፤ በእሁድ ሊሰሩ የሚችሉ ጥቂት ስራዎች አሉ (ሉቃ 13፡11-16)፤ ዶክተሮችና የጤና ባለሙያዎች ይሰራሉ፤ጥቂት የቤተሰብ ስራዎችም እንዲሁ ይሰራሉ፤የጓሮ አትክልቶችን መቆፈር፣መኪና ማጠብ፣በትምህርት ቤት የተሰጠንን የቤት ስራ መስራት እና ወዘተ... ወደ ዚህ ክፍፍል ዉስጥ መግባት የለብህም፡፡

‹‹በጌታ ቀን ከእነዚህ ስራ ሁሉ ማረፍ ተገቢ ነዉ፤ ሶስቱ ስራዎች ግን ሊሰሩ ይገባል እነዚህም የቸርነት ስራዎች፣የጸሎትና አስፈላጊ የሆኑ ስራዎች ናቸዉ፤›› (ሕዝቅኤል ሆፕኪንስ)

‹‹በእርገቱ ቀን፣ከሞት የተነሳበት ቀን በሞትና ሲኦል ሁሉ ላይ ያለዉን ስልጣን ያሳያል፤ሰንበትን የክብር ደረጃ አደርገህ አስብ አሁን አሳልፈሃል እንደገናም ትመጣለች›› (ሪቻርድ ባክስተር)

እሁድ የጌታ ቀን ነዉ፤ጌታችንና አዳኛችንን የምናከብርበት ነዉ፤እሁድ ጌታን የምናመልክበት የምናርፍበትና የምንወድበት ቀን ነዉ፤ ጌታን ትወደዋለህ? የእርሱን ቀን አስታዉስ በቅድስና ጠብቀዉ፡፡

20

ጋብቻ

ጋብቻ ማለት በሕብረተሰብ የተፈጠረና ብዙ ዘመናት ካለፉ በኋላ ደግሞ ጊዜ ያለፈበት ፋሽን ነዉ ተብሎ በማህበረሰቡ የሚተዉ ነገር አይደለም፡፡ ወደ ኋላ ዞር ብለን ስናይ ጋብቻ በእግዚአብሔር የተፈጠረ መለኮታዊ ተቋም ነዉ፤(ዘፍ 2፡18፣21-25)፤ ጌታችን ኢየሱስ ሰለ ጋብቻ አስተምሮአል፤(ማቴ19፡3-9) ሐዋርያዉ ጳዉሎስም ተናግሮአል (ኤፌ 5፡21-33) ሁለቱም የሚናገሩት ከፍጥረት ጀምሮ ያለዉን ሐሳብ ነዉ፡፡

አንዱና ዋናዉ የጋብቻ አላማ የሕይወት ዘመን ጓደኝነት ነዉ፤‹‹ሰዉ ብቻዉን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም›› ያለዉ እግዚአብሔር ነዉ (ዘፍ 2፡18)፤ በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ይልቅ የሚጠጋጋ (አጥንት ከአጥንቱ ...ከሥጋዬ) የሚያስብል ነዉ፤ የምድር ሕይወትህ እስኪያበቃ ድረስ ሕብረቱ የሚቀጥል ነዉ (ቁ.23-24) ከሥጋ ዘመድ ይልቅ የሚጠጋጋ ነዉ፤ ምክንያቱም

ሰዉ እናቱንና አባቱን ይተዋል ከሚስቱም ይጣበቃል ይላል ቃሉ፣ ጌታችን ኢየሱስ ይህንን ሲያብራራ ጋብቻን ማፍረስ በጣም ከባድ እንደሆነ ነዉ፤(ማቴ 19፡3-6) ስለዚህም ተጋቢዎቹ አንዳቸዉ ለሌላቸዉ ታማኝ መሆን እንዳለባቸዉ ነዉ (ቁ.9)፡፡

ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር በምድር የሚኖሩት ሰዎች ሁሉ ማግባት አለባቸዉ የሚል ሀሳብ የለዉም፤ አንዳንዶች ማግባት አይፈልጉም፤ ሌሎቹ ደግሞ ከሁኔታዉ የተነሳ አበላሽተዉታል፤ አንዳንዶች ደግሞ እግዚአብሔርን ለማገልገል ብለዉ ያገባሉ፤ ብዙ ጊዜ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ያገባሉ፡፡

ከሚከተለዉ ጽሑፍ ምን ታስባለህ?

‹‹አንድ ሰዉ የሚከተሉትን ነገሮች ሳያሟላ ወላጅ መሆንን ማሰብ የለበትም ይሽዉም 1) ጥሩ ገንዘብ መያዝ ምክንያቱም ሚስቱን ይረዳል አለበለዚያ ግን በእጦት ይፈተናል ጌታንም ይፈታተናል፤2) በእግዚአበሔር ጸጋ የራሱን መንፈስ መግዛት መቻል አለበት (ምሳ25፡28) ይህ ካልሆነ ለትዳር አጋሩ አጋር መሆኑ ይቀርና መቅሰፍት ይሆናል፤3 ወደ ተክክለኛና ዳግም ወደ ተወለደችዉ ሴት ጌታ እስካልመራህ ድረስ ይህንን የትዳር ቀንበር መሸከም የምትችል ካልሆነች ማግባት የለብህም፤ ሚስት ስትፈልግ ጥሩ ስራ ያላትን ሴት እያልክ ገንዘብንና ዉበትን ስትፈልግ የመንፈሳዊ ሕይወትንና ባህሪን ወደ ኋላ የምታደርግ ከሆነ የዉጫዊ ዉበትና ገንዘብ ሲረግፍ ሁለት ኪሳራ ይሆንብሃል›› ኤ ደብሊዉ ፒንክ

ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያኖችን ብቻ ማግባት አለባቸዉ (2ቆሮ6፡14)፡፡ አንተ ክርስቲያን ሆነህ ልታገቢዉ ያሰብሽዉ ወይም ያሰብካት ሴት ክርስቲያን ካልሆነች አሳምነዋለሁ ወይም አሳምናታለሁ ከሚል አደገኛ ወጥመድ ልትጠበቅ ይገባል፤ እንዲህ አይነት አስተሳሰብ አልፎ አልፎ ሊከሰት ይችላል፤ ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ክርስቶስ ላይ መደራደር የለባቸዉም፤ ያላመነ ማግባት ማለት ያላመነዉ ወገን ወደ አንድ ጎን መጎተት ያመነዉ ወገን ደግሞ ወደሌላ ጎን መጓተት ይፈጠራል በትዳር ላይም አደገኛ የሆነ ችግር ያስከትላል፡፡

ጋብቻ ማለት ሁለት ሰዎች አንድ የሚሆኑበት ህብረት ነዉ፡፡ ጓደኝነት የሚለዉ ቃል ራሱ ይህንን ለመተንተን ደካማ ነዉ፡፡ ጳዉሎስ የክርስቲያንን ጋብቻ ያነጻጸረዉ ከክርስቶስና ቤተክርስቲያን ጋር ነዉ፤(ኤፌ 5፡21-33)፤ ክርስቲያን ጥንዶች ከመጋባታቸዉ በፊት በጋራ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ማጥናት አለባቸዉ፤ የዶ/ር ኤም ሊዮድ ጆንስን መጽሐፍ

‹‹ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ›› በጋብቻ፣ ቤትና ሥራ የሚሉትን መጽሐፍ እንድታነቡ አበረታታችኋለሁ።

የክርስቲያን ጋብቻ እንደሌሎቹ ጋብቻዎች ሁሉ የራሱ የሆነ ችግር አለበት። አንዳንድ ጊዜ እንደምንሰማዉ በትዳር ዓለም የቆዩ ሰዎች በጋብቻችን ሃምሳ አመት አስቆጥረናል እያሉ ይመሰክራሉ፤ ወይም ስለ መስቀሉ ቃል ለትዳር አጋራቸዉ ሳይነግሩ ማለት ነዉ፤ በጥቃቅን ምክንያቶች ይህ እዉነት ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ የማስታወስ ችሎታቸዉ አጭር ስለሆነ ሊሆን ይችላል፤ አንዳንድ ችግሮችና ክርክሮች ሊመጡ ይችላሉ የቆዩም ሰዎች አንዳንዴ የሚናገሩት ነገር እዉነት ነዉ፤‹‹ የሚጸልዩ ጥንዶች አብረዉ ይኖራሉ›› አብረዉ የሚጸልዩ ከሆነ ችግሮች በዘላቂነት አይቆዩም ማለት ነዉ።

ክርስቲያኖች ያላመኑትን ማግባት እንደሌለባቸዉ ተመልክተናል፤ነገር ግን ሁለቱም ሳያምኑ ተጋብተዉ አንደኛዉ ወገን ካመነ ጳዉሎስ በዚህ ጉዳይ የሚለዉን አንብቡ (1ቆሮ7፡12-16)።

በዚህ መኖርህን ካረጋገጥህ በጣም ጥንቃቄ አድርግ፤የአንተ ትልቁ ፍላጎት መሆን ያለበት ያላመነ የትዳር ጓደኛህን ማሳመን ማለት ነዉ፤ለትዳር ጓደኛህ መስበክ አትጀምር እንዲህ አይነት አካሄድ ብዙ ጊዜ መጥፎ ነዉ፤ነገር ግን በሕይወትህ ምን እንደተፈጠረ አስረዳ አብራራ፤ማሰብ ያለብህ የትዳር ጓደኛህ አሁንም በጨለማ ዉስጥ እንዳለ እና እንደማያስተዉል ነዉ፤በመጀመሪያ የአንተን/የአንቺን አዲሱን ሕይወት መታየት አለበት፣ ታገስ፣ በቀስታ አድርግ፣ ብዙ ጸልይ፤ ያላመነ የትዳር ጓደኛህን/ሽን/ የምታሸንፈዉ በቃላት ሳይሆን በተግባር ነዉ፤የአንተን/ቺን/ ደግነት፣ፍቅር፣እና ማስተዋል ያስፈልጋል። አማኝ ከመሆን/ሽ/ በፊት የነበረህ/ሽ/ አሁን መቀየር አለበት፤አስታዉስ ለስብሰባ እያልክ ብዙ ጊዜ እየወሰድህ ቤትህን ቸል እንዳትል ተጠንቀቅ፤ በጌታ ጸጋ ብዙ ጸልይ ተስፋ አትቁረጥ የትዳር ጓደኛህን ዉደድ።

21

ግንኙነት

አንድ ወንድና ሴት ልጅ እርስ በርስ በመፈላለግ ይቀራረባሉ ተቀራርቦም መጠናናት ጤናማ የሆነ ግንኙነት ነዉ፤ክርስቲያኖች ተስፋ ከቆረጡ በጣም አደገኛ ነዉ።

ጥቂት ወጣቶች በጣም በተክለ ቁመናቸዉ በጣም ቆንጆ እና አማላይ ናቸዉ፤ በጣም ቆንጆ መሆናቸዉ በራሱ ምንም ችግር የለበትም፤ ይህ ዝነኝነት በራሱ ጎጂም አይደለም፤ ለአንዳንድ ወጣቶች ችግር ነዉ ምክንያቱም የራሳቸዉን ስግብግብነት ስለሚያጎላ ነዉ፤ ለክርስቲያን እኔነት እና ትዕቢት በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ አደጋ የሚያመጣ ነዉ፤ በመቀጠልም ይህ ባህርይ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ትልቅ ችግርን የሚያመጣና የሚያበላሽ ነዉ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር ያለዉን ግንኙነት የሚያበላሽ ነዉ፡፡

ሰይጣን ደግሞ ዋና ስራዉ ወጣቶችን በዚህ ባህርይ መመላትና ግንኙነትን ማበላሸት ነዉ፡፡ አንዱን ወጣት በአንዱ ላይ በማነሳሳት እንዲቀና ማድረግ ስራዉ ነዉ፤ ይህ በህብረት ላይ አደጋን የሚፈጥር ነዉ ይህ በወጣቶች የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ አደጋን የሚፈጥር ነዉ፤ የእርስ በርስ ግንኙነታቸዉ ሲሰበር ትልቅ ቁስለትን የሚያስከትል ሲሆን ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይመጡ ሁሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ይህ በርግጥ ልክ አይደለም በሳል ያልሆኑ ክርስቲያኖች በሐይል በግንኙነት ዉስጥ ይገቡና እንዲህ ያለ ችግር ይፈጥራሉ፡፡ አላማችን ወንዶችና ሴቶች እርስ በርስ ይሳሳባሉ ስለዚህ ስህተት ነዉ ማለት አይደለም፤ አደገኛ የሚሆነዉን ነገሮች ማዉጣትና መምራት ያስፈልጋቸዋል፤ ክርስቲያኖች በሁሉም አቅጣጫዎች ከእግዚአብሔር ጋርና ከሌሎች ክርስቲያኖች ያላቸዉን ግንኙነት የሚያባላሹ ነገሮችን መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ጥቂት ምክሮችን እነሆ

- የወንድ/የሴት ጓደኛህ አማኝ መሆን አለበት፤ ይህ ስለ ጋብቻ በተነሳዉ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተነስቷል አሁን መድገም አያስፈልግም፤ በዚህ ጉዳይ ብሉይ ኪዳን በጣም ነዉ ማስጠንቀቂያ የሚሰጠዉ፤ (ዘጸ34፡14-16፣ 1ነገስት 11፡1-4) አዲስ ኪዳንም በግልጽ የሚያነሳዉ ጉዳይ ነዉ‹‹ ከማያምን ጋር በማይመች መንገድ አትጠመዱ ጽድቅ ከአመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለዉ?›› (2ቆሮ6፡14) ይህ መተዉ የሌለብን ሕግ ነዉ፤
- የሴት ወይም የወንድ ጓደኛህ ክርስቲያን መሆን አለበት፤ ይህንን ሁሉም ክርስቲያኖች ላያደርጉት ይችላሉ ስንቶች ወጣቶች ናቸዉ ከማይመቻቸዉ ሰዎች ጋር ጓደኝነት የጀመሩት? ራሳቸዉንና ፍላጎቶቻቸዉን መግዛት እያቃታቸዉ በግጭት ዉስጥ ገብተዉ ዉጤቱ ደግሞ ዉድቀትና እምባ ሲሆን በጣም ያሳዝናል፤

- የአንተ ሴት ወይም ወንድ ጓደኛ ሌላ ቤተክርስቲያን የሚሳተፍ ቢሆንስ? በዚህም ጉዳይ ቸኩለህ መጀመር የለብህም ምክንያቱም የአንተ/ቺ/ መጀመሪያ ታማኝነት ለቤተክርስቲያንህ ነዉ፤ ይህ ማለት አንዳችሁ የሌላችሁን ቤተክርስቲያን አትጎብኙ ማለት አይደለም፤ አልፎ አልፎ መጎበኛኘት ትችላላችሁ ነገር ግን በመደበኛነት መሆን የለበትም፤ግንኙነታችሁ ወደ እጮኝነት የሚያድግ ከሆነ ወደ ጋብቻ በፍጥነት መምጣት ይኖርባችኋል። ብዙ ጸሎትም ያስፈልጋችኋል ወደ አንድ ቤተክርስቲያን በመጠቅለል አብራችሁ ማምለክ ትችላላችሁ።
- በተለይ በአስራዎቹ የእድሜ ክልል ዉስጥ ፈጥናችሁ ወደ ግንኙነት መግባት የለባችሁም፤ ከተጀመረ ግን አንደኛዉ ሌለኛዉን ሊጎዳ ይችላል። ወደ ሃያዎቹ መጀመሪያ ስትደርስ ነገሮች ይቀየራሉ፤በጣም ጠቃሚዉ ጉዳይ አንዱ ለሌላዉ ጉዳይ የሌለዉ ሰዉ መሆን የለበትም፤ ጓደኝነታችሁን በጥንቃቄ ማስኬድ ይኖርባችኋል፤ ይህን ስታደርጉ ጥልቅ የሆነ ስሜት ሰለ ጓደኞቻችሁ ይኖራችኋል።

ጓደኝነት ማለት ፍቅር ማለት ነዉ። ሁለት የሚዋደዱ ወጣቶች ካሉ ወደ ጋብቻ እንዲመጡና ቀሪዉን ዘመናቸዉ አብረዉ እንዲያሳልፉ የጌታ ሐሳብ ነዉ፤ የእጮኝነት ጊዜ በጣም ከባድ ነዉ፤ ምክንያቱም ወሲብ በእጮኝነት ዘመን ትክክል ነዉ ተብሎ በሚታሰብበት በሚበረታታበት ዘመን እየኖርን ስለሆነ ነዉ። መዋደድ ጥሩ ነዉ መዋደዳችንን በወሲብ ማሳየት አለብን እየተባለ ይገኛል፤ ነገር ግን ወሲብ ከጋብቻ በፊት ልክ አይደለም ወሲብ ቆሻሻ ስለሆነ አይደለም በእግዚአብሔር የተፈጠረ መልካም ነገር ነዉ፤ ፍቅራችንን የምንገልጠዉ በጋብቻ ዉስጥ ነዉ፤ እግዚአብሔር ፈጠረዉ በዘፍ2፡24 ኢየሱስም ጠቀሰዉ በማቴ 19፡5 እና በሐዋርያዉ ጳዉሎስ ኤፌ5፡31፤ ሰዉ እናትና አባቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል አንድ ስጋ ይሆናሉ የሚለዉ በጋብቻ ነዉ። ዊሊያም ሂንደሪከሰን የተባለ ሰዉ በዚህ ጉዳይ ሲናገር ‹‹ አንድነት በአእምሮ፣ በልብና በአላማ ነዉ...›› አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለዉ በወሲብ አንድ መሆንን ነዉ (1ቆሮ 6፡16)፤ ያላመኑ ሰዎች ይህን ሲሰሙ ያሾፋሉ ያለፈ ፋሽን ነዉ ይላሉ፤ ክርስቲያን በዚህ መኖር ያለበት የእግዚአብሔር ቃል ነዉ። በሁኔታ ተታለህ መንዝ የለብህም በቃሉ እንጂ፤ ከጋብቻ ዉጭ ፍቅር በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፤ ነገር ግን ለወሲብ ፍላጎት ራስህን አሳልፈህ አትስጥ፤ ብታደርገዉ ግን በኋላ ታዝናለህ።

ከጋብቻ በፊት ያለዉ ሕይወት በግልጽነት አመለካከትህን ለትዳር ጓደኛህ የምትገልጽበት ነዉ፤ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ህብረት የምታደርግበት ጊዜ ነዉ፤ አብረህ መጸለይ መበረታታትና እርስ በርስ የመረዳዳት ጊዜ ነዉ።

‹‹ጥንዶች የእጮኝነት ጊዜያቸዉን እንዴት ይመለከቱታል? አንዳቸዉ የአንዳቸዉን አካል፣ልብ ወይም አእምሮ መበዝበዝ የለባቸዉም እንዴት ነዉ ስለ ትዳራቸዉ ግብ መወያየት ያለባቸዉ? ስለ ወደፊት ትዳራቸዉ ስለሚገጥማቸዉና ተስፋ ስለሚያደርጉት ጉዳይ፣ስለ ስራ፣ስለ ገንዘብ አጠቃቀም፣የክርስቲያን ባህርይ በቤት ዉስጥ፣ልጆችን ስለማሳደግ፣ እነዚህ ጉዳዮች በኮምፒዉተር ጌም ላይ እንደተጫነዉ ካርድ እንደመምዘዝ ቀላል አይደሉም፤ ጥንዶቹ ጥልቅ ስለሆነዉ ስሜቶቻቸዉ ማዉራትና ማካፈል አለባቸዉ፤ የሚወዱትንና የማይወዱትን ነገር መወያየት አለባቸዉ፤›› *(ዮሐንስ ዋይት)*

22

ወላጅነትና የቤት ዉስጥ ሕይወት

ብዙ ወጣቶች ጌታን በተቀበሉ ማግስት ከወላጆቻቸዉ ጋር የተለያዩ ግጭቶችን ያደርጋሉ። ይህም ወላጆቻቸዉን ለመቀበል ስለሚከብዳቸዉ ነዉ፤መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እየተናገረ ብዙ ሰዎች ግን ከዉድቀታቸዉ ነዉ የሚማሩት፤መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የወላጆች ባሕርይ ምን መምሰል እንዳለበት ይመክረናል።

ከአስርቱ ተዕዛዛት አምስተኛዉ እንዲህ የሚል ነዉ ‹‹ አክብር›› ዘጸ20፡12፤ ታላቅ የሆነ የአክብሮት መንፈስ ለወላጅ ያስፈልጋል፤ ማክበር ማለት ፍቅርና መታዘዝ ማለት ነዉ፤ ከፍቅር ያለፈ ሐላፊነት ያለበት ትዕዛዝ ነዉ።

በዘሌ19፡3 ላይ እግዚአብሔር አምላክ እናትና አባታችንን እንድንፈራ ይነግረናል፤ መፍራት ማለት ከጥልቅ ስሜት የሚወጣ አክብሮት ነዉ፤ እናት በመጀመሪያ መከበር እንዳለባት አባትም በመጀመሪያ መከበር እንዳለበት ይናገራል ዘጸ20፡12፤ ብዙ ጊዜ እናቶች ከጸታዎቻቸዉ የተነሳ አክብሮትን አያገኙም፤ ወጣቶች ይህን ነገር የሚረዱትና የሚመልሱት አባቶች ሲሆኑ

ነዉ።ማክበርና መታዘዝ የሚለዉ ቃል ለሁለቱም የሚሰራ ነዉ።ማክበር በጨዋነት መንፈስ መሆን አለበት።

ክርስቲያኖች አክብሮትን ለእነርሱና ለሌሎች ሰዎች መግለጽ ያለባቸዉ በጥንቃቄ በመናገርና በመመለስ ነዉ። ወላጆች ከእግዚአብሔር ቀጥለዉ የእኛ የበላይ ናቸዉ። ድካማቸዉ ከሌሎች ጋር የሚገናኝ አይደለም። ድካማቸዉና ዉድቀታቸዉ ከቤተሰብ ዉጭ የሆኑት ላይ እያየነዉ ያለዉ ምስክር ነዉ። የክርስቲያን ልጆች ባህሪያቸዉን መግራት አለባቸዉ ‹‹ፍቅር የሐጢአትን ብዛት ይሸፍናል›› (1ጴጥ 4፡8)።

በብሉይ ኪዳን የልጆች ባህርይ ለወላጆቻቸዉ ምን መሆን እንዳለበት በግልጽ ይናገራል። ለምሳሌ በዘዳ 27፡16 ላይ አለማክበር ማለት ማሳነስ ማለት ነዉ። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ጌታችን ኢየሱስ የተናገረዉ ምሳሌ ግልጽ ነዉ። ለሰላሳ አመታት ተራ በሆኑ ማርያምና ዮሴፍ ቤት ኖረ። ከወንድሞቹና እህቶቹ ጋር ሲኖር በቤተሰብ ዉስጥ ያለዉን ደስታና ሐዘን ምን እንደሆነ ያዉቀዋል። ይህም ሆኖ የክብር ጌታ ለምድራዊ ወላጆቹ ይገዛ ነበር (ሉቃ 2፡51)። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ለእናቱ ያስብ ነበር ለተወዳጁ ሐዋርያዉ ዮሐንስ እንዲወስዳትና እንዲጦራት ነገረዉ። ዮሐንስም ወደ ቤቱ ወስዶ እንደ እናቱ አድርጎ ተንከባከባት።(ዮሐ 19፡26-27) በአዲስ ኪዳንም ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ ብሎ ሲናገር እናያለን (ኤፌ6፡1-3)።

ሐዋርቱ እንደሚነገሩን ልጆች ለወላጆቻቸዉ መታዘዝ እንዳለባቸዉ ነዉ መታዘዝ የሚመጣዉ ከፍቅር የተነሳ ብቻ ሳይሆን ለማንነታቸዉ ነዉ ይህ ተግባር በጣም አስፈላጊ ነዉ በተለይ ጌታ ኢየሱስን ከመፍራት የመነጨ መሆን አለበት።ለጌታ እንደመትታዘዙ ይህ መታዘዝ ልክ ነዉ።ልጆች ለወላጆቻቸዉ መታዘዝ አለባቸዉ ለወላጆቼ መታዘዝ አለብኝ ምክንያቱም ጌታ እንዳደርግ ስላዘዘኝ ነዉ (ዊሊያም ሄንድሪክሰን)

መሠረቱን መፈተሽ

አንድ ሰዉ ክርስቲያን ለመሆኑ መሰረቱ የራሱ ቤት ነዉ።ወላጆቻችን አማኞች ይሁኑም አይሁኑም የልባችንን ተፈጥሮ የወረስነዉ ከእነርሱ ነዉ። እስኪ ቁጭ በልና ለሃያ አራት ሰዓት ከቤተሰብህ ጋር ያለህን ግንኙነት ምን እንደሚመስል ወደ ኋላ ዞር ብለህ አስብ። ጥሩ በሚባል ቤተሰብ ዉስጥ ዳቢሎስ ከፍተኛ ዉጊያ በማድረግ ይዋጋል። በሌላ መልኩ የወላጆች ልምምድ

አሁን ላለዉ የሕይወት ልምምድ መሰረታችን ነዉ። የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ለማፍራት ምርጡ ቦታ ነዉ (ገላ5፡22-23)።

ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች የሆኑ ወላጆች ካሉህ ምን ያህል ዕድለኛ መሆንህን አስተዉለሃልን? ብዙ ክርስቲያን ወጣቶች በወላጆቻቸዉ ላይ ያጉረመርማሉ። የሚያጉረመርሙቱ በስልጣናቸዉ ላይ ነዉ። አንዳንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እንዳታዩ ከልክለዉ ይሆናል። በትምህርት ቤት ያሉ ጓደኞቻችሁ ምናልባት እንዲያዩ ይፈቀድላቸዉ ይሆናል። አእምሮህ ስላልበሰለ እነዚህን ነገሮች ወላጆችህ ስላልፈቀዱ ያረጀ ፋሽን ይከተላሉ እያልክ ታጉረመርም ይሆናል።

ወላጆችህ እንዲህ ያደረጉህ ምክንያት ስለሚወዱህ ነዉ።እነርሱ አንተን ሲያዩህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ አድርገዉና ለአእምሮህ፣አካልህና መንፈስህ ሁሉ ሀላፊነት እንዳለባቸዉ አድርገዉ ነዉ። ይህን ሐላፊነት በትክክል ይወስዳሉ።አንተ የማታዉቀዉ ከሕይወት ልምዳቸዉ አንተን ሊጎዳ የሚችል ነገር እንዳለ ብዙ ዕዉቀት አላቸዉ። ክርስቲያን ያልሆኑ ወላጆች ግን እናንተን የሚጎዳ ነገር እንድታደርጉ ይፈቅዳሉ።

ወላጆቻችሁ ክርስቲያን ካልሆኑ ስለ ጌታ ፍቅር ሊነግሩአችሁ አይችሉም። ይህ ደግሞ አንዳንድ ከባድ ነገሮች እንዲገጥሙአችሁ አደረገ። ቤተክርስቲያን እንድትሄድ ብዙ ጊዜ ላይፈቅዱ ይችላሉ። መጠንቀቅ ያለባችሁ ነገር ቢኖር በቁጣና በምሬት አትመልሱላቸዉ። ይህን አምስተኛዉ ትዕዛዝ አሁን እየተተገበረ ነዉ። ለወላጆች መልሶ መናገር ተገቢ እንዳይደለ በቤተክርስቲያን ተምረህ ይሆናል። በዚህ ጊዜ በክርስቶስ ዳግም የተወለደዉ ማንነትህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እንዳለና በዉስጥህ እንደሆነ ያስታዉስሃል። ይህ በቤት ዉስጥ የሚደረገዉ ጠቃሚ የሆነ ቃል ነዉ።ራስን ያለመዉደድና ለሌላዉ ማሰብ ነዉ። ክርስትናችሁ በቤት ይታይ ማሚየ ወይም ባቢየ በሚለዉ በቃል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በሚታይ ፍቅርና ተግባር ሲሆን ከቃል በላይ ይሰማል።

ይህ ሁኔታ በጣም ከባድ ነዉ የሚለዉ አመጸኝነትና አንገተ ደንዳናነት ነዉ። ክርስቲያን ከሆንክ በተግባር አሳይ። ጸሎትና ትዕግስትን መለማመድ ያስፈልጋል።ዕድሜህ አስራ ስምንት ቢሆንም አምስተኛዉ ትዕዛዝ ይከበራል። ወላጆችህን ስለ ምክራቸዉና እንክብካቤያቸዉ አመስግን። ክርስቶስን በዝግታ መከተል ይገባሃል።

23

ገንዘብ

ከአመታት በፊት ‹‹ ገንዘብ የሀጢአት ሁሉ ስር ነዉ›› የሚል መዝሙር ይዘመር ነበር፤ በዓለም ላይ ብዙ ከሚዘመሩት መዝሙሮች መካከል ነበር ነገር ግን መዝሙሩ ስህተት አለበት፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለዉ ‹‹ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ (1ጢሞ6፡10)፤ ገንዘብ በራሱ ጥሩም መጥፎም አይደለም፤ የሰዉ ባህርይ ነዉ ክፉም ጥሩም የሚያደርገዉ ነዉ፡፡

የክርስቲያን ባህርይ በገንዘብ ጉዳይ እንዴት መሆን አለበት? 1ጢሞ6፡7-19 አንብቡ፤ ገንዘብን መዉደድ የለብንም ወይም ገንዘብን ክፉ ነዉ ብለን እንዳናስብ ያለ ገንዘብ ቤተክርስቲያን የወንጌሉን ስራ መስራት አትችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሰጠን ነገር ሁሉ ገንዘብን ጨምሮ ላይ ባለአደራ እንደሆንን ይናገራል፡፡ ብዙም ይሁን ጥቂት ጌታ የሰጠንን ነገር በጥበብ መጠቀም አለብን፤ ሀብታም ወይም ድሀ መሆናችን ሳይሆን የባለአደራ ስራችንን መስራት አለብን፡፡ የገንዘብ አጠቃቀማችን ድሀም ባለጠጋም ሊያደርገን እንደሚችል መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

እንዴት ነዉ ገንዘባችንን መጠቀም ያለብን? ለቤተሰቦቻችን ማዋል አለብን ይህም ለምግብ፣ ልብስ ወዘተ… ይህን ማድረግ እንዳለብን የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል (1ጢሞ5፡8)፡፡ ገንዘብን ለደስታና ለመዝናናት መጠቀም ይቻላል (ለመጽሐፍት፣በዓላትና ወዘተ…)፡፡ እግዚአብሔር በፈጠራት በዚህ ዓለም እንድንደሰት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነዉ፤ነገር ግን ክርስቲያን መጠንቀቅ ያለበት ገንዘቡን በመዝናናት ብቻ እንዳያባክን መጠንቀቅ ይገባል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚናገረዉ ክርስቲያን ገንዘቡን በቸርነት እና በቋሚነት መስጠት አለበት (1ቆሮ 16፡1-3፣2ቆሮ 9፡7)፡፡ አጠቃላይ መስጠት ማለት ሶስት አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ሲሆን መስጠት ያለብን ሀ) ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን ነዉ ለ) ለሚሲዮናዉያን ስራ ሐ) በቸርነት፤ ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን ሲሰጥ ይህንን ሶስት ጉዳዮች ማድረግ ይገባል፤ ቤተክርስቲያን የተቀበለችዉን ገንዘብ ማሰራጨት አለባት፤ መስጠት ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ያሳያል፤ሌላዉ ሥልጣን ለዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትም ‹‹ምጽዋት›› ብሎ

ይናገራል፤(ሉቃስ 12፡33፣ሐዋ 9፡36፣10፡2) ይህ ማለት በችግር ላይ ላለ ግለሰብ፣ ለቤተሰብ (ማቴ6፡1-4) በሥጦታ መርዳት ያስፈልጋል፤ሥጦታ ለሰጪዉ ትልቅ ደስታን የሚሰጥ ነዉ፤ (ሐዋ 20፡35) ምጽዋት ማድረግ ርካታን የሚሰጥ ነዉ፡፡

አሥራት

ብዙ ሰዎች የሚጠይቁት ጥያቄ ቢኖር ምን ያህል ገንዘብ ልስጥ? የሚል ነዉ፤ የብሉይ ኪዳን የመስጠት መሰረቱ አስራት ነዉ፡፡ ዘሌዋዉያን 27፡30-33፤ዘዳ 12፡6-18፣14፡22-29 2ዜና 31፡5ነህምያ 10፡37፤ ይሄ ማለት ሰዉ ከሚያገኘዉ ሀብቱ 10 በመቶ ለእግዚአብሔር መስጠት እንዳለበት ነዉ፤ በአዲስ ኪዳን እያንዳንዱ ክርስቲያን አስራት መስጠት አለበት፤ ነገር ግን ትኩረት መደረግ ያለበት ከአስራት በላይ በሆነ መስጠት ላይ ነዉ፤ ይህ ማለት ግን አስራት በክርስቲያን ሕይወት ዉስጥ ፍሬ ያፈራል ማለት አይደለም፡፡ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት አስራታቸዉን ለጌታ ይሰጡ ነበር አሁን ክርስቶስ በሙላት ከተገለጠ በኋላ መሰጠት ያለበት አስራት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በላይ ነዉ መሰጠት ያለበት፡፡

‹‹ያለህ ገንዘብ ሁሉ የእግዚአብሔር ነዉ፤ከአስር አንዱን ለእግዚአበሔር መስጠት አስፈላጊ ነዉ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ስራ መስመሩን ለመዘርጋት ጥሩ ጅማሬ ነዉ፤ነገር ግን ነገሮቸን እንዲህ መረዳት አስፈላጊ አይደለም ነገር ግን ሁሉም ሀብታችንና ያለን ነገር ሁሉ የጌታ ነዉ›› ኢ ኤፍ ሔቫን

አንድ አስረኛ ለጌታ መስጠት ለጅማሮ አስፈላጊ ነዉ፤ ስንሰጥ የሕግ ሰዉ ሆነን ሳይሆን መንፈሳዊ ሰዉ በመሆን ነዉ፡፡ የምንሰጠዉ መስጠት ስላለብን ሳይሆን ከፍቅር የተነሳ መሆን አለበት፡፡ ‹‹ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ፡፡›› (1ቆሮ16፡2)፤ ሐዋርያዉ ጳዉሎስ ገንዘብ እንዴት መስጠት እንዳለብን መልስ ሰጥቶናል፤ የእግዚአብሔርን ስጦታ አስተዋዉቆናል፤ ‹‹ጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ፡፡›› (2ቆሮ 8፡9) ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን፡፡(2ቆሮ9፡15)

መስጠት ያለብን በእግዚአብሔር የፍቅር ዕዉቀት ተሞልተን ነዉ፤ መስጠት ያለብን እንደተረዳነዉ መጠን እና ስጦታችን ለእግዚአብሔር የምንሰጠዉ ምላሽ ነዉ፤ ‹‹በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ›› (ማቴ 10፡8)

ዓለሙም ሁሉ የእኔ ነዉ

ለአንተ የምሰጠዉ ግን ጥቂቱን ነዉ

መለኮታዊ ፍቅር ድንቅ ነዉ

ነፍሴም ሕይወቴም ትፈልግሃለች

(ይስሐቅ ዋትስ)

ገንዘብን ለእግዚአብሔር መስጠት የአምልኮ አንዱ ማሳያ ስለሆነ ገንዘባችንን ከመስጠታችን በፊት ራሳችንን ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን (2ቆሮ8፡5)፡፡

ከዚህ በታች ያለዉን ጽሑፍ በጄ ሲ ሪሌ የተጻፈ ሲሆን በጸሎት ሆናችሁ አንብቡት፡፡

ክርስቲያን ነን ብለዉ ራሳቸዉን ለሚገልጡ በነጻነት ቸርነትና ምህረት ማድረግ አለባቸዉ፡፡ የእግዚአብሔር ባለአደራ መሆንህን አስታዉስ ገንዘብህን ነጻ ሆነህ፣ ያለ ስስት ስጥ ምክንያቱም ዕድለኛ ስለሆንክ ነዉ፤ ገንዘብህን ለዘላለም መጠበቅ አትችልም፤ ዓይንህ በዘላለማዊዉ ላይ በማድረግ ጌታ ለአንተ ባደረገዉ ነገር ላይ መሰረት አድርገህ ስጥ፡፡

በእንግሊዝ ሁሉም ሐይማኖቶች ለልግስና አገልግሎት ስራ በመስጠት በአስር እጥፍ አድገዋል፤ ክርስቲያን እንግሊዞች ከገቢያቸዉ ላይ እንዲህ የሚሰጡ ከሆነ የልግስናን ስራ መርዳት ያስፈልጋል፤ ስንሰጥ ጌታ በሚፈልገዉ አይነት ሐሳብ ሆነን መሆን አለበት፤ ያልጀመራችሁ ሰዎች ካላችሁ አሁን በመስጠት ጀምሩ መስጠት የጀመራችሁ ደግሞ አጠናክራችሁና ጨምራችሁ ስጡ፡፡

24

ዉርጃ

ዛሬ በእንግሊዝ ዉርጃ ማለት የማህበረሰቡ ቀዉስ እየሆነ መጥቷል፡፡ አንድም ክርስቲያን ይህንን መቋቋም አልቻለም በዉርጃ ብቻ ከ1967 ጀምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕጻናት ዉርጃ

ተካሂዶባቸዋል። ዛሬ በአለም ላይ በአንድ አመት ዉስጥ 43 ሚሊዮን የሚሆኑ ልጆች የሚሞቱ ሲሆን ወይም በየቀኑ 118,000 ልጆች ዉርጃ ይካሄደባቸዋል፤ ይህ በብሉይ ኪዳን ሆኖ ቢሆን ኤርምያስ ወይም ኢሳይያስ ዝም የሚል ይመስላችኋል፤ ከ700 ዓመታት በፊት በኢሳ 59 ላይ የተናገረዉ ነገር ዛሬ ከእና ጋር ሲዋሀድ እንመለከታለን። *‹‹እጃችሁ በደም ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፥ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሮአል፥ ምላሳችሁም ኃጢአትን አሰምቶአል። በጽድቅ የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፤ በምናምንቴ ነገር ታምነዋል ሐሰትንም ተናግረዋል፤ ጕዳትን ፀንሰዋል በደልንም ወልደዋል፤እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ፥ ንጹሑን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፤ አሳባቸው የኃጢአት አሳብ ነው፥ ጕስቍልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ።ፍርድም ወደ ኋላ ተመልሶአል፥ ጽድቅም በሩቅ ቆሞአል፤ እውነትም በአደባባይ ላይ ወድቆአልና፥ ቅንነትም ሊገባ አልቻለምና።እውነትም ታጥቶአል፥ ከክፋትም የራቀ ሰው ለብዝበዛ ሆኖአል። እግዚአብሔርም አየ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ።(ቁ.3፣4፣7፣14-15)*

ዉርጃ የሰዉ ልጅ ለእግዚአብሔር ያለዉን ምላሽ የሚያሳይ ነዉ። እግዚአብሔር የሰጠዉ ሕይወት ነዉ፤ በአሜሪካ እና እንግሊዝ አገር ከሶስት ወይም አራት ከተጸነሱት ዉስጥ በእናት ማህጸን እንዳሉ መግደል ይፈቀዳል፤ በየአመቱ በአሜሪካ አሁን የሚገደሉት በሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት ጊዜ የአሜሪካ ሰራዊት ከሞተባት ከሶስት ጊዜ በላይ ልጆች ይገደላሉ፤ ከጦር ሜዳ ይልቅ አሁን በማሕጸን ዉስጥ የሚሞቱት ይበልጣሉ። ጆን ስቶት በጽሑፋቸዉ እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹መዝገበ ቃላታችንን መከለስ ይኖርብናል፤አብዛኛዉ ሕዝብ የሚናገረዉ ነገር እዉነት እየመሰለን ነዉ፤ ጽንሰ ማስወረድ የሰዉን ሕይወት ማጥፋት ከሚለዉ ትርጉም በላይ ምን ሊባል ይችላል? ትክክለኛዉን ቋንቋ ልንጠቀም ይገባል፤ ዉርጃ ማለት ያልተወለዱ ልጆችን ማጥፋት ማለት ነዉ››

የዘመኑ ሁኔታ

በ1967 በወጣዉ ሕግ ላይ ሁለት ዶክተሮች ስለ ጽንሱ መዉረድ ከተስማሙ በአራት ምክንያቶች ሕጋዊ ሊደረግ ይገባል፤ በዚህ ምክንያት በአንድ አመት ዉስጥ በሕጋዊ ዉርጃ ምክንያት 170,000 ዉርጃዎች በአንድ አመት ዉስጥ ብቻ ይካሄዳል።

ወርቃ የሚደረገዉ ስለ ሕጻኑ ሳይሆን እናትየዉን ከማዳን አንጻር ነዉ የሚሉ ናቸዉ። ይህ እንኳ አልፎ አልፎ የሚካሄድ ነዉ፤ ከአጠቃላይ ሁኔታዉ ግን ስንመለከት ወርቃ አስፈላጊ መሆኑን ነዉ፤ ሶስተኛዉ ምክንያት እናትየዉ ከመብት የተነሳ ሲሆን አካሌ ስለሆነ በአካሌ ላይ የፈለግሁትን ነገር የማድረግ መብት አለኝ ከሚል ነዉ። ወርቃን ለማድረግ የሚቀርበዉ ምክንያት ምንም የማያሳምንና ዉሃ የማያነሳ ምክንያት ነዉ። ከዛያ አንድ ቀን በኋላ ሴቶች እርጉዝ መሆናቸዉን ያዉቃሉ፤ የሕጻኑ ልብ መምታት ይጀምራል።

- በአንድ ወር ዉስጥ -ሕጻኑ ራስ፣አይኖች፣አፍንጫ፣አፍና አእምሮ ይኖረዋል፤
- በ6 ሳምንት ዉስጥ --አእምሮቹ ስራ መስራት ይጀምራሉ፤
- በ2 ወር ዉስጥ በእጆቹ አንዳንድ ነገሮችን መዳሰስ ይጀምራል፤
- በ9 ሳምንታት ዉስጥ---መሳብ ይጀምራል፤
- በ3 ወራት ዉስጥ---ሕጻኑ በእጁና በእግሩ መምታት ይጀምራል በእንግዴ ልጅ በኩል መተንፈስ ይጀምራል፤

በ 9 ወራት ዉስጥ ሕያዉና ሙሉ ሰዉ ሆኖ ይወለዳል፤ ወርቃን ማህበረሰባችን እንደ ጤነኛ አድርጎ አስቧል፤ አሸባሪዎች በቦምብ ንጹሐን ዜጋዎችን እንደሚጎዱ ሁሉ እንዲሁ በቀን በወርቃ ምክንያት 170,000 ሰዉ መግደል ማለት እነዚህ ተመሳሳይ ናቸዉ። በጣም የሚገርመዉ ፍርድ ቤቶቻችን ላልተወለደ ልጅ በመኪና አደጋ ለሞተ ካሳ ያስከፍላል ነገር ግን በየቀኑ በወርቃ ለሚገደለዉ ልጅ የሚለዉ ነገር የለም፤ ምን አይነት ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ያለነዉ! የ16 ሳምንት ሕጻን በእናቱ ማሕጸን ዉስጥ ነፍስን የማዳን ስራ የሚሰራ ነዉ። ይኸዉም ኩላሊት እንዳይወድቅ ያደርጋል፤ እኛ ግን እንደዚህ አይነቱን የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ እንገድላለን፤ ጆን ስቶት ሲናገሩ

‹‹ዋናዉ ነገር የሥነ ምግባርና የሥነ መለኮት ጉዳይ ነዉ የጽንስን ተፈጥሮ ማወቅ ያስፈልጋል ትርጉሙ ዘር ማለት ነዉ፤ በማሕጸን ዉስጥ ያለዉን ጽንስ እንዴት ነዉ የምናየዉ? የእኛ ለጽንስ ያለን አመለካከት ወርቃ ላይ ያለንን አቋም ይወስናል፤በአጠቃላይ ጽንስ ማስወረድ ተገቢ አይደለም ልክ እንደ ተበላሸ ጥርስ ወይም ቶንሲል ጽንስን እንደዛ አስቦ ማስወረድ ትክክል አይደለም››።

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

የሰዉ ሕይወት ማለት ዉድ የእግዚአብሔር ስጦታ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዉ ምዕራፍ ይህንን ይናገራል፤ ሰዉ የተፈጠረዉ በእግዚአብሔር አምሳል ሲሆን በአጠቃላይ እርሱ የሕይወት ምንጭ ነዉ፤ ዉርጃ ክፉ ነዉ፤ ሕይወት የሚጀምረዉ መቼ ነዉ? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረዉ ሕይወት የሚጀምረዉ በመወለድ ጊዜ አይደለም ነገር ግን በጽንስ ጊዜ ነዉ፤ ሩት 4፡13 ላይ ጽንስ የእግዚአብሔር ስጦታ ነዉ፤ እስኪ የመዝሙር 139፡13-16ን ዉበት እንመልከት፤

አቤቱ፥ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረሃልና፥ በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛልግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፤ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች፤እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ፥ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፤ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ፤

በዘጸ 21፡22-25 ነፍሰ ጡርን ሴት ማክበር እንደሚገባ ይናገራል በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ያልተወለደ ልጅ እንደ ሰዉ ነዉ የሚታየዉ ይንቀሳቀሳልም (ሉቃ 1፡41)፤ ለእግዚአብሔር ተለየ (ኤር 1፡15) እነዚህ ጥቅሶች እንደሚነግሩን በማሕጸን ዉስጥ ሕይወት እንዳለ ነዉ፤ ይህን ሕይወት ማጥፋት ማለት ሰዉን መግደል ማለት ነዉ።

ክርስቲያን ማድረግ ያለበት ምንድን ነዉ?

በ1967 ዓ.ም ጽንስ ማስወረድ ሕጋዊ ሆኖ ሲነገር መንግሥት ያደረገዉ ነገር ቢሆንም ከብዙ ሰዎች ግን መበረታታትን አላገኘም። የፖለቲካ ዉሳኔ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ልባችን ተስፋ አልቆረጠም። ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲህ ብሏል ‹‹*ሥነ ምግባር ሕጋዊ ባይሆንም ነገር ግን ባህርይ ሕጋዊ ሊሆን ይችላል፤የፍርድ ቤት አዋጆች የሰዉን ሕይወት አይቀይሩም ነገር ግን ልብ የሌላቸዉን ሰዎች ሊወስኑ ይችላሉ፤*›› ሕጉን መቀየር ባንችልም እንደዜጋ መብታችንን ተጠቅመን ይህን ማህበራዊ ቀዉስ መቃወም እንችላለን፤ በግል ዉርጃ ክፉ እንደሆነ ማሳመን እንችላለን። ይህን የምናደርገዉ እኛ ኖረነዉ ነዉ ለነፍሰ ጡሮችና አካለ ጎዶሎ ልጆች እንክብካቤ ሳናደርግ መቃወማችን ብቻዉን ትርጉም አይሰጥም። ለበለጠ መረጃ በወንጌላዉያን ለሕይወት የሚሉ ጽሑፎችን አንብብ፤ (ላይፍ ሀዉስ፣ኒዉቦልድ ቴራስ፣ላሚንግተን ስፓ፣(ሲቪ 32 4 ኢ ኤ)።

በዚህ ዘመን ክርስቲያን መሆን በጣም ከባድ ነዉ። ለክርስቶስ መቆምና መኖር በማህበረሰቡ ዉስጥ እና በአገር ዉስጥ ንጽሕናን ይጠይቃል፤ዓለማዊ እሴቶች በሚዲያ ላይ በትምህርትና በማህበረሰብ ዉስጥ አገልግሎት ይሰጣሉም ይገለጻሉም፤ ሰዉ ግን የእግዚአበሔርን የሞራል ሕግ መተዉ የለበትም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ‹‹ ሰዉ የዘራዉን ያንኑ ያጭዳል›› (ገላ 6፡7)፤ ተግባር ዉጤት አለዉ፤ ዛሬ በእንግሊዝ የምናየዉ ዉጤት ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቤተሰብ ሕግ፣ስለ ወሲብ እና ሕክምና የሚለዉን ነገር ችላ ከማለታቸዉ የተነሳ የመጣ ነዉ።

የክርስቲያን እምነት በተግባር የሚሰራ ነዉ ምናልባት ሕግ አዉጭዎች መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ነዉ ብለዉ ላያምኑ ይችላሉ። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፋቸዉ ዉጤት አለዉ፤ በአለማዊዉ ማህበራዊ ጥናት ላይ እንደሚያሳየዉ የ1960 አብዮት የክርስቲያኖችን ልጆች ሕይወት፣ጤናና አዋቂዎች ላይ ሳይቀር ጉዳትን አድርሷል። ጉዳዩም ግልጽና ዉስብስብ ነዉ፤ ትክክለኛዉን ነገር ለመናገር የብዙዎችን ሰዎች ተስፋ አስቆርጧል፤ ስለሞራላዊ ሕጎችና ከተማ አቀፍ ሕጎች ድምጽን ከፍ አድርጎ መናገር ያስፈልጋል፤ (የክርስቲያን ደርጅት)።

25

ዕፆች

እንደገና ስንመጣ በትምህርት ቤቶች ዉስጥ ዕጾች አሉ፣በጋዜጣ ላይ እና በቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ አለ፤ ለምን? ለምን? ለምን?

በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣዉ ሪፖርት ላይ በክፉ ዕፆች አለም እንደተያዘች ሲናገር ለእኛ ይህ ትልቅ ተግዳሮት ነዉ።

‹‹ከአለም ዳር እስከዳር ድረስ ዲሞክራሲ በሚል ሰበብ ሰዎች በዕጽ መድሀኒት ተበላሽተዋል፤ የፋብሪካ ሰራተኞች በተለየ መልኩ ለዚህ ተጋላጭ ናቸዉ፤ ዕፅ የሚወሰደዉ ለጊዜያዊ ችግር ማስታገሻ ተብሎ ነዉ። በሽታን ለማከም፣ ሁኔታን ለመቀየር፣ራስን ለማጥፋት፣ ለመርሳትና ለመበዝበዝ ነዉ፤ አእምሮ በዚህ ዕጽ ሱስ ይያዝና ባጣ ጊዜ ባለመታገስ ወደ ጽንፈኝነት

ይገባል፤ሳይንስ ላስተማረን ነገር እስካሁን ድረስ ማን ባሪና ማን ጌታ መሆኑን ነዉ፤›› (የአለም የዕፆች ሪፖርት የተባበሩት መንግስታት መቆጣጠር ፕሮግራም)፡፡

የትኛዉ ነዉ እዉነት? ዕጽ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነዉን? ወይስ የሰዎች የክፉ ችሎታ ዉጤት ነዉ?

ብዙ ሰዎች በተደጋጋሚ የተጎዱበትን ምክንያት ብዙም ስላይደለ መልካም ተስፋ መስጠት ያስፈልጋል፤ የረኸርም ጊዜ ጥናት እና ዉጤት ይህን ቢያሳዩም ዶክተሮች አሁን ያላቸዉ አመለካከት ተቀይሯል፤ ለሁሉም ግልጽ ሊሆን የሚገባዉ ጉዳይ የጤና ባለሙያ የሚነግረንን ምክር በአግባቡ መጠቀም ለራስ ጥቅም ነዉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዘመናዊ መድሐኒት የሚነግረን ነገር የለም፤ ምክንያቱም ብዙዎቹ የተገኙት በቅርብ ዘመን ስለሆነ ነዉ፤መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን የነበረዉ መድሐኒት ቢኖር አንድ ሲሆን እርሱም አልኮል ነዉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ከወይን ይገኛል፤ በጣም ጠንቃቃና ጥበበኛ መሆን ይጠይቃል፤ ምክንያቱም ብዙዎች አዲሱን ወይን ከመከር ጋር ያገናኙታል፡፡ በእኛ ዘመን ካለዉ የፍራፍሬ ጭማቂ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፤ ይህንን በነህምያ 10፡39 ላይ እናገኛለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የመጠጥን አስቸጋሪ ዉጤት ይነግረናል፡፡ ከሀላፊነት አንጻር ካህናትና ነገስታት አልኮል አይጠጡም (ምሳ 31፡4)፤ የምሳሌ መጽሐፍን በደንብ አድርገን ስናነብ ጠንቃቃ ሊያደርጉን የሚችሉትን ብዙ ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን እናገኛለን፡፡ ምሳሌ 4፡17፣20፡1፣21፡17 እና 23፡21ን ተመልከቱ፡፡

ከመጀመሪያዉ ሰዉ በአልኮል ተበላሽቷል፤ ይህንን ከኖህ ታሪክ ማግኘት እንችላለን (ዘፍ 9፡20-27) ይህ ለዉጥ አደጋ ያለበት ሲሆን ወደ ጸጸትና ዕፍረት መርቷል፤ ከምሳሌ መጽሐፍ 23፡29-35) በጥንቃቄ አንብቡ፡፡

ዋይታ ለማን ነው? ኀዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለ ምክንያት መቊሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው?የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን?ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል።ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ፥ ልብህም ጠማማ ነገርን

ይናገራል።በባሕር ውስጥ እንደ ተኛ ትሆናለህ፥ በደቀልም ላይ እንደ ተኛ።መቱኝ፥ ያውም አልተሰማኝም፤ ጐሰሙኝ፥ አላወቅሁምም። መቼ እነሣለሁ? ደግሞ ጨምሬ እሻታለሁ ትላለህ።

ክፍሉን ካነበባችሁ በኋላ ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፤ እነዚህን ነገር ምን ያህል አይቻለሁ? ቃሉ ከተጻፈት በዚህ በ2000 ዓመታት ዉስጥ ምን ያህል ተቀይረዋል? የሰዉ ሞራል/ሥነምግባር/ ወይስ አልኮሉ ተቀይሯል?

ከዚህ ቀደም እንዳልነዉ ስለሌሎች መድሐኒት መጽሐፍ ቀዱስ የሚነግረን ነገር የለም፤ ነገር ግን አልኮል መድሐኒት ነዉ። በርግጥ ይህ ለሌቹ ሰዎች አልኮል መድሐኒትነት አለዉ፤ የመድሐኒት ትርጉሙ ሰዉነታችን በትክክለኛዉ ሁኔታ እንዲሰራ ማድረግ ነዉ። ሕገ ወጥ መድሐኒት ግን ይህንን ያዛባል፤ ሕገወጥ ዕጾች አእምሮን ሁሉ የማዛባት አቅም ያላቸዉ ናቸዉ። ጥቂት ዕጽ የሚወስዱ ሰዎችን ስንመለከት እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት ትመልሳለህ?

- ብዙ የሚናገር ሰዉ ዝቅተኛ ሰዉ ያሰኝዋልን? ስትናገር ለምትናገረዉ ነገር ጥንቃቄ ታደርጋለህን?
- ቸልተኛ ከሆንህ ግልጽ ነዉ መንዳት የለብህም አደጋ ዉስጥ ብትገባ ምን ይሰማሀል?
- ስብዕናህ ዘገምተኛ ወይም ፈጣን ከሆነ ራስህን እንዴት ትገዛለህ? እንዴት ነዉ ትዕግስትን ወይም መልካምን ለማድረግ የምትችለዉ?
- በአንድ ጉዳይ ሱሰኛ ከሆንክ ወደ ያ ሱስ ወደ ባርነት ይወስድሃልን? መልካም ሊሆን ይችላልን?
- የሕይወትህን ሚዛን ለማስጠበቅ ባደረግህ መጠን ገንዘብ እና ጊዜ ይጠይቃል፤ ራስን ስለ አለመግዛት እና የማሰብ ችሎታህ ሁለቱ ቃላቶች ምንን የሚገልጹ ናቸዉ?
- ጤንነትህ ላይ አደጋ የሚጥል ከሆነ ከቤተሰብህና ከጓደኞችህ ጋር ባለህ ግንኙነት ሶስቱን ቃላቶች እንዴት ትገልጻለህ?
- ሕይወትህን አደጋ ላይ የሚጥል ነገርና ወደ ስደት እና እፍረት ይመራል ለዚህ ጉዳይ የአንተ መልስ ምንድን ነዉ?
- ገንዘብ ለወንጀለኞች ምግባቸዉ ነዉ፤ ለሰዎች ጤናና ድነት ምንም ግድ የላቸዉም፤የማህበረሰቡ ሕይወት ጥራት ያለዉ እንዲሆን ያስፈልጋል ይህ ለክርስትና አስፈላጊ ነዉን?

እነዚህ በቂ ጥያቄዎች ናቸዉ፤ ብዙ ዕጾች አሁን በገበያ ላይ አሉ፤ አዳዲስ መድኃኒቶች በገበያ ላይ በፍጥነት ይመጣሉ፤ ብዙዎች ከዚህ የሚጠቀሙ ሲሆን ለማመስገን ጥሩ ምክንያት ይኑርህ፡፡

ዕጾች ለአደጋ ያጋልጣሉ ሊቀጥልም አይገባዉም ብዙ የሚያስደነግጡ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ብልሆች ስንሆን ጥቅሞቹን ተቀብለን ጉዳትን መቀነስ ይገባል፤ ወይም አደጋ የሚፈጥሩትን በጋራ መከላከል ያስፈልጋል፤ አስታዉሱ ጠቃሚ የሆነዉን መድሐኒት ሊያዝልን የሚችለዉ የህክምና ዶክተሮች ብቻ መሆን አለባቸዉ፡፡

በሕይወታችን የተለያዩ ነገሮች ያስፈልጉናል፤ አካላዊ እንቅስቃሴ፣ በጥበብ መብላት፣ ጥሩ መተኛት፣ መልካም ግንኙነት እና ተግዳሮቶችን መጋፈጥ ጸሎትንና ምስጋና ጨምር፤ እግዚአብሔርን የምትወድድ ከሆነ አካልህን መጠበቅ አለብህ፤ ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነዉና፤(1ቆሮ3፡16)፤የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ማለት የዕፅ ወሳጆች ፍሬ የተለያየ ነዉ፤ ምክንያቱም የመንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ሠላም፣ የዉሃትና ራስን መግዛት የሚያጠቃልል ነዉ፡፡

የኢየሱስን ምሪት ስንከተል ለሌሎች ማሰናከያ መሆን አይገባም (1ቆሮ8፡13 ለዚህ ድንጋጌ) እንደ ደጉ ሳምራዊ ለመርዳት፣ለማዳንና በመስዋዕትነት ለማገልገል ወስን፤

አንዲት በዕድሜ የገፉች ክርስቲያን ሴት እንደሰማችዉ ሌላዉን የሚጎዳ ነገር ሥራዋ ከሆነ እንደ በግል ለእግዚአብሔር የሚያቀርብ መስዋዕት ነጻነትዋን መስዋዕት አድርጋ ማየት የለባትም፤ ብዙ ወጣቶችም ተመሳሳይ የሆነ ድርጊትና አላስፈላጊ ነገሮችና አደገኛ የሆኑ ዕጾችን ይጠቀማሉ፤ በጣም ከባድ ቢሆንም ብዙ ወጣቶች ከመልካም ጎን መቆም አለባቸዉ፡፡

ትኩረታችን ንጹህ የሆነዉን፣ፍቅርና መልካም ነገር ያለበትን፣ትክክለኛ የሆነዉን ነገር ማድረግ አለብን፤ ኢየሱስም አለ ‹‹በኋላዬ ይምጣ ለራስህ አትኑር መስቀሉን ተሸክሞ ዕለት ዕለት ይከተለኝ›› ይህ ደስ የሚያሰኝና ተግዳሮት ያለበት ነዉ፡፡

ይህን ምዕራፍ ስናጠቃልል በዕፅ ጉዳይ ርካታን ለማግኘት፣አበረታች መድኃኒትና በሌሎችም ነገሮች ተበላሽተናል፤ ከዚህ ምዕራፍ ዉስጥ ለአንተ ጠቃሚ የሆነዉ ርዕሰ ጉዳይ የትኛዉ ነዉ? ከክፉ ሁሉ ሊጠብቀን የሚችል ዓለም አለችን፤በራሳችን ምንም ማድረግ አንችልም መልካሙ ዜና ደግሞ እንዲህ ያለ ዓለም ልትኖረን አትችልም፡፡ ሌሎች ደግሞ የሰላምን እና የጥበብን

መንገድ ይዘን እንጓዛለን የሚሉ ከእኛ ጋር ናቸዉ። ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል በልጽገናል ሽልማትም ይጠብቀናል፤ እግዚአብሔር ይመስገን!

26

የአቻ ቡድን ግፊት

የአቻ ቡድን ግፊት ዛሬ የብዙ ሰዎችን ሕይወት ጎድቷል፤ ወጣቶች በትምህርት ቤት በክፍል ዉስጥ እናጠናለን በሚል ሰበብ በጓደኞቻቸዉ ግፊት ችግር ዉስጥ ገብተዋል። በዚህም ተስፋ መቁረጥ ዉስጥ ተዘፍቀዋል፤ በሥራ ላይ ያሉ ከአሰሪዎቻቸዉ ዕቃዎችን እየሰረቁ የተለያየ ነገርን ያደርጋሉ፤ አሰሪዎችም ድርጅታቸዉ ዉጤታማና ፍሬያማ እንዲሆን ሠራተኞቻቸዉን በጥሩ እንክብካቤና ክፍያ መያዝ አለባቸዉ።

ክርስቲያኖች በዚህ አቻ ግፊት ይጋለጣሉ፤ በተለይም በትምህርት ቤት ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ማለት ነዉ፤ እዉነተኛ ክርስቲያኖች በብዙ ክርስቲያኖች መካከል ይቆማሉ፤የተለየ ዓላማና እሴት ያላቸዉ ናቸዉ፤ በሳምንቱ መጨረሻ ላይ አልኮል ለመጠጣት እና ወደ ዕጽ አይሄዱም፤ ሰዉነታቸዉ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ቤተመቅደስ እንደሆነ ያዉቃሉ(1ቆሮ6፡19) ስለዚህ ከዝሙት ሀጢአት ራሳቸዉን መጠበቅ አለባቸዉ።

ክርስቲያኖች ልዩ ናቸዉ አቻ ቡድናቸዉን የመሳብ ሐይል ሊኖራቸዉ ይገባል። በዩኒቨርሲቲ ሕይወታቸዉ ጓደኞቻቸዉ በሚያዘጋጁት የጭፈራ ምሽትና ዝሙት ስራ ሌሎቹ እንደሚያደርጉት እነዚህም ተጋላጭ ይሆናሉ፤ በሥራ ቦታቸዉም እንዲሁ በአጉል የፌዘኝነት ስራ ዉስጥ ካልተባበሩ ይቀለድባቸዋል።

እንዴት ነዉ ክርስቲያኖች ይህን የአቻ ግፊት በመቋቋምና ለኢየሱስ ታማኝ ሆነዉ የሚኖሩት? በመጀመሪያ ክርስቲያኖች ምርጫ ሊኖራቸዉ ይገባል። በቡድኑ ዉስጥ ለእርሱ ታማኝ ሆኖ

መቀጠል አይቻልም፤የጌታችን ሕይወት በአንድም በሌላም መንገድ ቡድኑ ከያዘዉ አቋም የተለየ ነበር፤ ይህንን ኢየሱስ ግልጽ ሲያደርገዉ *‹‹ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል ›› (ዮሐ 15፡18-19)* ፤ ሁሉም ነገር ግልጽ ነዉን? ክርስቲያን ምርጫ አለዉ፤ክርስቶስ በኖረዉ የሕይወት ዘይቤ መኖር አለባቸዉ፤ ነገር ግን ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ማድረግ አንችልም፡፡

ሁለተኛዉ ክርስቲያን የአቻ ግፊትን መቋቋም የሚችለዉ ዕለት ዕለት ከእግዚአብሔር ጋር ባለዉ ጥልቅ ግንኙነት ነዉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና በማሰላሰል በመንፈስ ቅዱስ ሐይል በመጸለይ ጌታ እንዳደረገዉ ማስተማር ያስፈልጋል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይህቺ ዓለም የሐሰት እንደሆነች ይነግረናል፤ ምንድን ነዉ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚገባቸዉ ባህርይ? (1ጢሞ6፡6-10) ዓለም በራስዋ ዘይቤ በአቻ ቡድን ግፊት ዉስጥ አስገብታ መጭመቅ የለባትም፡፡ አእምሮአችን እለት ተእለት ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት እየታደሰ መለወጥ አለበት፡፡

ሦስተኛ ክርስቲያኖች የቡድን የአቻን ግፊት ከሌሎች የቤተክርስቲያን አቻዎቹ ጋር በመሆን መቃወም አለበት፡፡ በእነዚህ ቡድን ዉስጥ ሲታቀፍ ክርስቲያን ድጋፍ፣ምሪት እና መበረታታትን ያገኛል፤እርስዋ ብርታትን ከጸሎት እና ማደግን ከሕብረት ታገኛለች፤ እዉቀት፣ተቀባይነት ማግኘትንና ርዳታ የሕያዉ ክርስቲያኖች መገለጫ ናቸዉ፡፡

የዋዛ ንግግሮች በክርስቲያን ቡድኖች ዉስጥ አይገኝም (ኤፌ4፡29) ነገር ግን የሚያንጽ ንግግር ብቻ ይሆናል፡፡

በመጨረሻም ክርስቲያኖች ከእነርሱ ቀደም ብለዉ ያሉ ክርስቲያኖች የአቻ ግፊትን እንዴት ተቋቁመዉ እንዳለፉ መማር አለባቸዉ፡፡ ለምሳሌ ሶስቱ ወጣቶች ናቡከደነጾር ላቆመዉ የወርቅ ምስል አንሰግድም ብለዉ የንጉሱን ትዕዛዝ ተቃወሙ፤ በትህትናም እንዲህ ብለዉ መለሱ *‹‹የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት (ዳን 3፡17-18)* በእግዚአብሔር ርዳታ ሲድራቅ፣ሚሳቅና አብድናጎ ለጌታ በጽናት ቆሙ፡፡